# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 163 የካቲት 13 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# አህጉራዊ አጀንዳን

## ሊያጠናክር የሚችል የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ እንደሚያስፈልግ ተገለጸ



ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ

ፎቶ - እዮብ ተፈራ



ዶክተር ምሕረት ደበበ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- አህጉራዊ አጀንዳን ሊያጠናክር በሚችል እሳቤ ፓን አፍሪካኒዝምን እንደገና የማደስና የማዳበር ቁመና እንደሚያስፈልግ ተገለጸ::የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ የመጀመሪያውን የፓን አፍሪካኒዝም ፎረም አካሂዷል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ በ36ኛው የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤ ተከትሎ ባዘጋጀው የመጀመሪያው የፓን አፍሪካኒዝም ፎረም ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ወቅቱ የአፍሪካ ህብረትን 60ኛ ዓመት የምስረታ በዓልና 10ኛ ዓመት የአጀንዳ 2063 የትግበራ ጊዜ ላይ መሆናችንን በማሰብ አህጉራዊ አጀንዳን ሊያጠናክር በሚችል እሳቤ ፓን አፍሪካኒዝምን እንደገና የማደስና የማዳበር ቁመና ላይ መሆን አለብን ሲሉ ገልጸዋል::

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ኢትዮጵያ ፓን አፍሪካኒዝምን ከፍ ለማድረግ የወሰደችውን ቁርጠኝነት ማሳያ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አፍሪካዊያን የፖለቲካ አስተሳሰቦችና ድንበር ሳያግዳቸው አህጉሪቷን በጋራ ከፍ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል:: ተተኪው አመራር ቀና አሳቢና መፍትሄ አፈላላጊ ሆኖ እንዲፈጠር መስራት እንደሚገባ በመጥቀስ፤ አካዳሚው ይህንን ኃላፊነት ወስዶ እየተወጣ እንዳለ አመላክተዋል::

ዓለምአቀፋዊ ተወዳዳሪነትና ሰላማዊ መግባባትን ያማከለ፤ የአፍሪካ ወጣቶችና ሴት አመራሮችን በልማት ያሳተፈ የፓን አፍካኒዝም ውህደት እንደሚያስፈልግም ገልጸዋል:: ነባሩና አዲሱ ትውልድ አንዱ ከአንዱ በመማር፤ የአመራር ብቃትን በማጎልበት ወቅቱን የዋጀ እንዲሁም አህጉራዊ አጀንዳን የሚያጠናክር የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ማድረግ እንደሚገባ ገልፀዋል::

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በፓን አፍሪካኒዝም ባለፉት ዘመናት በርካታ ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም በቂ አለመሆናቸውን አንስተው፤ ከባለፈው በመማር እየተለዋወጠ የመጣውን ወቅታዊ ዓለማቀፋዊ


አህጉራዊ አጀንዳን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## የአረንጓዴ አሻራ

### መርሀ ግብር አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ፋይዳው የጎላ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ ፡- የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ትውልዱ በስፋት ሊያስቀጥለው እንደሚገባ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ገለፁ።


የአረንጓዴ አሻራ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## ትውልዱ የተከፈለለትን መስዋዕትነት እያሰበ ለሀገር እድገት መስራት አለበት

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የአሁኑ ትውልድ የተከፈለለትን የደም መስዋዕትነት እያሰበ ለአገር ሁለንተናዊ እድገት ብዙ መስራት እንዳለበት ተገለፀ።

በትናንትናው ዕለት ስድስት ኪሎ በሚገኘው የሰማዕታት መታሰቢያ ሀውልት በተከበረው 86ኛው የሰማዕታት ቀን ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፤ ጀግኖች አባቶቻችን በከፈሉት መስዋዕትነት ዛሬ አገራችን ጸንታ ቆማለች፤ በአፍሪካ የነጻነት አርማነት ተደርጋ የምትጠራ ብትሆንም የአሁኑ ትውልድ የተከፈለለትን መስዋዕትነት እያሰበ ብዙ መስራት ይገባዋል::

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በዚህ ወቅት ከ86 ዓመታት በፊት ፋሺስት የጣሊያን ሰራዊት ቂም ይዞ ከሰላሳ ሺህ በላይ ዜጎቻችንን



በአዲስ አበባ መጨፍጨፉን የሚታወስበት ይህን ቀን ስናከብር የአባቶቻችንን አኩሪ ገድልን በመዘከር ነው ብለዋል::

ምንም እንኳን በዛ በበቀል ዱላ የደረሰው መከራ ኢትዮጵያዊያን


ትውልዱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




















የአረንጓዴ አሻራ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







አቶ ሑስማን ሱሩር

# በክልሉ የተጀመረው የሌማት ትሩፋት ስራ ውጤታማ ሆኗል

በሪሁ አረጋ

አዲስ አበባ ፡- በደቡብ ክልል የተጀመረው የሌማት ትሩፋት እንቅስቃሴ በህብረተሰቡ ዘንድ መነሳሳትን የፈጠረና ትልቅ ተስፋ የሚጣልበት መሆኑን የደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ።

በክልሉ በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የገጠር ልማት ክላስተር አስተባባሪና የደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ኡስማን ሱሩር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፣በክልሉ የተጀመረው የሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር በቤተሰብ ደረጃ ብልፅግናን ለማምጣት ትልቅ አስተዋጸኦ ያለው ነው፡፡በክልሉ የተጀመረው የሌማት ትሩፋት እንቅስቃሴም በህብረተሰቡ መነሳሳትን የፈጠረና ትልቅ ተስፋ የሚጣልበት ነው፡፡

የሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር የምግብና ስርዓተ ምግብ ዋስትናን በማረጋገጥና ከድህነት ለመውጣት ለወጣቶችና ለሴቶች የስራ እድል በመፍጠር ገቢን በማሳደግ የበርካታ ሰዎችን ኑሮ እየቀየረ ይገኛል ብለዋል።

በክልሉ በሌማት ትሩፋት መርሀ ግብር ከሚሰሩ ስራዎች የእንስሳትና እንስሳት ሃብት ልማት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ ስራስርና የእንሰት ልማትንም የሚጨምር መሆኑን ተናግረዋል።

በክልሉ የወተትና የወተት ተዋፅኦ እንዲሁም የዶሮ ስጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ዝርያ የማሻሻል ስራ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ነው ያሉት ኃላፊው፤ የማር እና የዓሳ ልማት ምርትና ምርታማነት ለማሳዳግም ተስፋ ሰጪ ስራዎች መጀመራቸውን አመልክተዋል፡፡

በጅምር ላይ ያሉት የሌማት ትሩፋት ስራዎችም ክልላዊ ፍጆታን በመሸፈን የተመጣጠነ የስነ-ምግብ ፍላጎትን በማሟላት ዜጎችን በፕሮቲን እጥረት ከሚከሰቱ በሽታዎች በመጠበቅ፣ የአእምሮ መቀጨጭና መቀንጨርን የተሻገረ ትውልድ ለመገንባት ያለመ ነው ብለዋል።

በክልሉ ያለው ዓመታዊ የወተት ፍላጎት ሁለት ነጥብ 8 ቢሊዮን ሊትር መሆኑን አመልክተው፤ ባለፈው ዓመት የተገኘው ዓመታዊ የወተት ምርትም ከ 771 ሚሊዮን ሊትር በላይ ነው፡፡ ዘንድሮ ከባለፈው ዓመት የተሻለ የወተት ምርት እንዲገኝ ታስቦ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን አቶ ኡስማን ገልጸዋል ።

የዶሮ እርባታን በተመለከተ በክልሉ አንድ ቤተሰብ በትንሹ እስከ አምስት ዶሮዎች እንዲኖረው በማድረግ ለቤተሰቡ ከሚውል የእንቁላልና ስጋ ፍጆታ በዘለለ ትርፉን በመሸጥ የገቢ ምንጭ ለማድረግም እየተሰራ ነው ያሉት ኃላፊው፤ እንደ ደቡብ ክልል ባለፈው ዓመት ከ5 ሚሊዮን በላይ ጫጩቶች ተሰራጭተዋል፤የባለፈው ዓመት ዓመታዊ የእንቁላል ምርትም ከ 21 ሺህ ቶን በላይ መድረሱን ጠቁመዋል፡፡

የእንቁላል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግም የዶሮዎች ጤና፣ የአመጋገብና የዝርያ ማሻሻል ስራ በተጠናከረ መልኩ እየተሰራ እንደሚገኝም አቶ ኡስማን ገልፀዋል።

# በአፍሪካ 250 ሚሊዮን ህጻናት የትምህርት ዕድል አላገኙም

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በአፍሪካ 250 ሚሊዮን ህጻናት የትምህርት እድል እንዳላገኙ በአፍሪካ ህብረት የትምህርት፣ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መሀመድ ቤልሆሲን ገለጹ።

ፕሮፌሰር መሀመድ ቤልሆሲን እንደተናገሩት፤ በአፍሪካ 250 ሚሊዮን ህጻናት የትምህርት እድል አላገኙም ማለት ለአፍሪካ እድገት እንቅፋት ነው። ከዚህም ባለፈ ልጆች የመማር እና ከሌሎች እኩል የማደግ መብታቸውን እንደመንካት ነው የሚቆጠረው።

ስለዚህ በትምህርት ላይ ኢንቨስት ማድረግ እና የኢኖቬሽን እና የሳይንስ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት እንዲሁም አፍሪካውያን ህጻናትን ወደ ትምህርት ቤት መመለስ የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን የ2024 አጀንዳ ይሆናል ብለዋል።

እንደ ፕሮፌሰር መሀመድ ገለጻ፤ የአፍሪካ ህብረት የትምህርት፣ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ኮሚሽን ትምህርትን የአፍሪካ መሪዎች ቀዳሚ ጉዳይ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት በርካታ ህጻናት በተለያዩ ምክንያቶች ከትምህርት ገበታቸው ውጪ ናቸው እናም እዚህ አፍሪካ ውስጥ ያለው ትምህርት ልዩ ትኩረት ያስፈልገዋል። በአህጉሪቱ የትምህርት ተደራሽነትን ለማሻሻል የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተቀርጸዋል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአፍሪካን የትምህርት ደረጃ በመንግስት መሪዎች ደረጃ ገምግሟል ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ጉዳዩ የአለምን ትኩረት ስቧል። የአፍሪካ ኅብረት በተለያዩ የአህጉሪቱ ክፍሎች ያለውን የትምህርት ሥርዓት ገምግሞ፣ የትምህርት ጥራት በብዙ ነገሮች ተጎድቷል ብሏል። የመምህራን ገቢ የትምህርት ጥራትን ይጎዳል ብለዋል።



ፕሮፌሰር መሀመድ ቤልሆሲን

ፕሮፌሰር መሀመድ አክለውም፤ ተማሪዎች ሳይንስን፣ ቴክኖሎጂን፣ ምህንድስናን እና ሂሳብን ማወቅ አለባቸው። በዚህ ረገድ በበርካታ የአፍሪካ አገሮች የሚደረጉ ጥናቶች ጥሩ እየሠሩ እንዳልሆነ እየታየ ነው። ስለዚህ በእንደዚህ ዓይነት ክፍሎች ውስጥ ትምህርትን ማሻሻል በቅርብ ጊዜ ውስጥ ግባችን ነው።

ኮሚሽኑ እየታዩ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ እያደረገ ያለውን ተሳትፎ በመጥቀስ ደካማ የመሰረተ ልማት እና ኢንቨስትመንት፣ ውስን የሰው ሃይል ጥረታቸውን እንዳስተጓጎለባቸው አጽንኦት ሰጥተዋል። እነዚህን አዝማሚያዎች የማሻሻል አጀንዳ ከዓለም አቀፍ ጥናትና ምርምር እና ከአፍሪካ 2063 አጀንዳ የመነጨ ነው ብለዋል ኮሚሽነሩ።

በአለም ላይ ድህነት ለትምህርት እንቅፋት ሲሆን፤ ብዙውን ጊዜ ህጻናት ትምህርት እንዳይማሩ ያደርጋል። ከዚህም ባለፈ ባለፉት ዓመታት በኮቪድ እና በተለያዩ ሀገራት በተፈጠሩ ጦርነት ምክንያት የትምህርት እድል ያላገኙ ህጻናት ቁጥራቸው ሊጨምር ችሏል።

ስለዚህ በአፍሪካ ያሉ ህጻናት የተሟላ ትምህርት እንዲያገኙ ህብረቱ ከአፍሪካ ሀገራት እና ከሀገር አቀፍ የትምህርት ኃላፊዎች ጋር በመተባበር ብዙ ህጻናት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ እየሰራን ነው።

እንደ ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መሀመድ ገለጻ፣ በአፍሪካ 250 ሚሊዮን ሰዎች ትምህርት አላገኙም። ለዚህም በርካታ መምህራንና በርካታ ትምህርት ቤቶች ያስፈልጋሉ። ስለዚህ ሁሉም የአፍሪካ ሀገራት መንግስታት ይህንን ታሳቢ ማድረግ አለባቸው።

በትምህርት ቤት ምገባ ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ለመመለስ እየተሰራ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ በየትኛውም ቦታ ያሉ ልጆች ጥራት ያለው ትምህርት የማግኘት መብት እንዳላቸው ሁሉ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ እና በፈጠራ ሀገራቸውን ማሳደግ አለባቸው ብለዋል።

በኮቪድ እና በተለያዩ ሀገራት በተፈጠሩ ጦርነት ምክንያት የትምህርት እድል ያላገኙ ህጻናትን በድጋሚ ትምህርታቸውን መከታተል አለባቸው። በተጨማሪም የተሻለ የትምህርት፣ መሠረተ ልማት፣ በትምህርት አስፈላጊነት ላይ ግንዛቤን ማሳደግ፣የማህበራዊ ደህንነትን በተመለከተ የጥራት መጨመር፣ በጤና እና የአስተማሪ ክፍተቶችን መሙላት ወሳኝ ነው ብለዋል።



# በመኸር ግብርና ከ110 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ተገኝቷል

አማን ረሺድ

አዲስ አበባ፡- በመኸር ወቅት የግብርና ስራዎች ከ110 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ምርት ማግኘት መቻሉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የእርሻና ሆርቲካልቸር ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር መለስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመኸር ወቅት የስንዴ ልማት ስራ 110 ሚሊን ኩንታል ለማግኘት ታቅዶ እቅዱን መቶ በመቶ ማሳካት ተችሏል።

ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ስንዴን ከውጪ ለማስገባት ከ700 ሚሊዮን ዶላር እስከ አንድ ቢሊዮን ዶላር ለግዢ ታውል እንደነበር ያስታወሱት ዶክተር መለስ፤ ለግብርና ምቹ የሆነ መሬትና የውሃ ሀብትን በመጠቀም የስንዴ ምርቱን በሀገር ውስጥ ማምረት መጀመራችን ለግዢ የሚወጣውን ገንዘብ ማስቀረት አስችሏል ብለዋል።

የስንዴ ምርት ካለፉት ዓመታት ጋር ሲነጻጸር በሰብል ሽፋንና በምርታማነት ከፍተኛ ጭማሪ እንዳለው ጠቁመው፤ ስንዴን ለሀገር ፍጆታ ከማዋል ባለፈ ለጎረቤት ሀገራት የማቅረብ አቅም መፈጠሩን ገልጸዋል።



ዶክተር መለስ መኮንን

በዚህም በ2015 ዓም በመኸር ወቅት ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በስንዴ ለመሸፈን ታቅዶ ስድስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሄክታር መሬት መሸፈኑን ዶክተር መለስ አስታውቀዋል።

እንደ ሀገር በአጠቃላይ 400 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ምርት ለማግኘት የተያዘውን እቅድ የሚያሳካ ስራ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

የክልሎችን አቅም በመለየት ስንዴን ጨምሮ 12 ዋና ዋና ሰብሎችን በክላስተር እየለማ ነው ያሉት ዶክተር መለስ ፤በስንዴ ልማት ስራ ባለሀብቶችና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በስፋት እየተሳተፉ መሆናቸውን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ምርት በብዛት ቢመረትም የኮንትሮባንድ ሁኔታው ግን ፈተና ሆኗል ሲሉ ተናግረዋል።

ከስንዴ የሚገኘውን ገቢ በአግባቡ ለመጠቀም በህገወጥ መንገድ ወደ ውጪ የሚወጣውን ምርት ማስቀረት ይገባል፡፡ለሀገር ውስጥ በቂ የስንዴ ፍጆታን ማቅረብና የገበያ ዋጋ ንረትን ማረጋጋት እንደሚቻልም ጠቁመዋል።

በተጨማሪም ስንዴን በህጋዊ መንገድ ወደ ውጪ በመላክ ኢትዮጵያ ከውጪ ምንዛሪ የምታገኘውን ገቢ ማሳደግ የሚያስችል ዕድል ተፈጥሯል ያሉት ዶክተር መለስ፤ አጠቃላይ ከግብርና ጋር የተያያዙ ምርቶች ላይ ያለውን ህገወጥ ንግድ ስርዓት መቆጣጠርና የገበያ ስርዓቱን ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ግብርና ሚኒስቴር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

# የታክስ መሰረትን ማስፋት የሀገርን ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለማፋጠን ያስችላል

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- የታክስ መሰረትን የማስፋት ስራ የሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማፋጠን ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ተገለጸ፡፡

በገቢዎች ሚኒስቴር የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ አዲስ ይርጋ እንደገለጹት፣ በሀገር ደረጃ የታክስ መሰረትን ማስፋት የሀገር ኢኮኖሚያዊ እድገትን ማፋጠን ነው፡፡

እንደ አቶ አዲስ ገለጻ፣ በሀገር ደረጃ የታክስ መሰረትን የማስፋት ስራን መስራት ተጨማሪ የገቢ አማራጮችን መፍጠር ያስችላል፤ ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ሲገኝ ተጨማሪ ሀገራዊ ገቢ በታክስ ስርዓቱ መሰረት ይሰበሰባል፣ ሀገራዊ ገቢውም አብሮ ያድጋል፡ ፡ይህ ሲሆን ተጨማሪ ሀገራዊ ልማቶች ይከናወናሉ ብለዋል፡፡

የታክስ መሰረትን ከማስፋት ባሻገር ታክስ እንዲሰበሰብባቸው የተወሰኑት ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ዜጎች በወቅቱና በህጉ መሰረት መክፈላቸው ለሀገር ልማት መፋጠን ጉልህ ድርሻ እንዳለው መገንዘብ ይኖርባቸዋል ሲሉ አቶ አዲስ ተናግረዋል፡፡

ከነበሩት የታክስ መሰረቶች በተጨማሪ አዳዲስ መሰረቶች ሊኖሩ እንደሚገባ የተናገሩት ዳይሬክተሩ፤ በቅርቡ ወደ ታክስ ስርዓቱ የተካተቱትን የንብረት ባለቤትና ባለይዞታ፣ ከመጠቀሚያ ክፍያ እና ከመሬት ኪራይ ክፍያ በቀጣይ እንዲሰበሰብ በሁለቱ ምክር ቤቶች መወሰኑን አስታውሰዋል፡፡

እንደ አቶ አዲስ ገለፃ፤የታክስ ሥርዓትና ህግ ዓላማ ለልማትና ለአገራዊ በጀት የሚያስፈልገውን ወጪ በታክስ ገቢ መሸፈን ቢሆንም ሌሎች በርካታ ጠቀሜታዎችም እንዳሉት ያብራሩት ዳይሬክተሩ፤ ከጠቀሜታዎቹ ውስጥ የፊሲካል ፖሊሲው መሣሪያ መሆን ነው፡፡ ይህ ደግሞ የመንግስትን ሁለንተናዊ አቅም ይገነባል፣ ሀገራዊ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ኢኮኖሚውን ያሳድጋል፣ የሥራ ዕድል መፍጠር ያስችላል፣ የሀገርን ሁለንተናዊ ልማትና ዕድገትን በማሳካት እንደ ሀገር የተያዘውን የብልፅግና ጉዞ ለማፋጠን ያስችላል፡፡

ከንብረት ታክስ ከፍተኛ ሀብት መሰብሰብ የሚቻል ሲሆን በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች ግን ከንብረት ታክስ የሚሰበስቡት ገቢ ከዓመታዊ ጠቅላላ ምርታቸው በአማካኝ ከ0.6 በመቶ አይበልጥም፡፡

በኢትዮጵያ በከተሞች የሚፈጠረው ቋሚ ንብረት ከጊዜ ወደ ጊዜ ከከተሞቹ ዕድገት ጋር እየጨመረ በመሄድ ላይ የሚገኝ ቢሆንም መንግሥት ተገቢውን ድርሻ በታክስ አማካኝነት እየሰበሰበ አይደለም፡፡ ተመጣጣኝ የሆነ የንብረት ታክስ የሚከፍሉበት አግባብ አለመኖሩም ተገልጿል፡፡

በአገራችን ባለፉት ዓመታት በተፈጠረው የኢኮኖሚ ዕድገት ምክንያት ከተሞች በፍጥነት በማደግ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው በከተሞች ከሚገኘው ሀብት እያደገ የመጣውን የመንግሥት የወጪ ፍላጐት በተወሰነ ደረጃ ለመሸፈን የሚያስችል የተሻለ ሀብት ማሰባሰብ እንዲቻል ዘመናዊ የንብረት ታክስ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑንም ዳይሬክተሩ አመላክተዋል፡፡

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 99 ለፌዴራል ወይም ለክልል ተለይቶ ያልተሰጠ ታክስ የመጣል ሥልጣን ላይ ውሣኔ የሚሰጠው በፌዴሬሽንና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለት ሦስተኛ ድምፅ መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ በንብረት ላይ የሚጣለው ታክስ ባለቤት እንዲወሰን የገንዘብ ሚኒስቴር ለሁለቱ ምክር ቤቶች ባቀረበው የውሣኔ ሀሳብ መሰረት ጥር 3/2015 ዓ.ም የንብረት ታክስ በክልሎች ባለቤትነት ተግባራዊ እንዲሆን መወሰኑ ይታወሳል፡፡



**አቶ አዲስ ይርጋ**




# በክልሉ 200 ሚሊዮን የደንና የፍራፍሬ ችግኞች ይተከላሉ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከዘንድሮው የተፋሰስ ልማት ስራ በተጓዳኝነት 200 ሚሊዮን የሚጠጉ የደንና የፍራፍሬ ችግኞች ሊተከሉ መሆኑን የክልሉ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ አቶ የሺዋስ አለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የ2015 ዓ.ም የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ስራና የችግኝ ተከላ መርሃግብር መከናወን ጀምሯል።

በቤንች ሸኮ ዞን በሰሜን ቤንች ወረዳ የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት በይፋ የተፋሰስ ልማት ስራው በጥር ወር 2015 ዓ.ም ተጀምሯል ያሉት አቶ የሺዋስ፤ ህብረተሰቡን ያሳተፉ ስራዎች በመከናወን ላይ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ክልሉ በግብርናው ዘርፍ ያለውን እምቅ አቅም መጠቀም እንዲቻል ከደን ችግኞች ባለፈ ለምግብነት የሚውሉ ፍራፍሬዎች በብዛት ይተከላሉ። በተለይ የሙዝ፣ የአቮካዶ፣ የማንጎ፣ የፓፓያና የተለያዩ ከአካባቢው የአየር ንብረት ጋር ተስማሚ የሆኑ 200 ሚሊዮን የሚጠጉ የደንና የፍራፍሬ ችግኞች ተከላ ስራ ተጀምሯል ብለዋል።

የተፋሰስና የችግኝ ተከላ ስራው የሚከናወነው የአረንጓዴ እጥረት ባለባቸውና ከዚህ ቀደም ለእርሻ አገልግሎት በማይውሉ ስፍራዎች ላይ እንደሚከናወን ገልጸዋል።



**አቶ የሺዋስ ዓለሙ**

አቶ የሺዋስ እንዳስታወቁት፤ የክልሉን ህዝብ በተለያዩ አደረጃጀቶች እንዲዋቀር በማድረግ በዘንድሮው የተፋሰስ ልማት ስራ 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሰዎች እየተሳተፉ ይገኛሉ።

የተፋሰስ ልማት ስራው በክልሉ ግብርና ቢሮ አማካኝነት በ220 ሺህ 800 ሄክታር በላይ መሬት ላይ የሚከናወን መሆኑን የጠቆሙት አቶ የሺዋስ፤ እስከአሁን በተከናወኑ የተፋሰስ ልማት ስራዎች የአፈር ለምነትን በማሳደግ፣ አካባቢዎችን ከጎርፍና ተጓዳኝ ችግሮች በመጠበቅና የተራቆቱ መሬቶችን ወደ አረንጓዴነት በመቀየር ረገድ ውጤት መገኘቱን አስረድተዋል።

በ2015 ዓ.ም 426 አዲስና 639 ነባር በድምሩ 1ሺህ65 ንዑስ ተፋሰሶች ተለይተው እንደሚለሙም አቶ የሺዋስ አብራርተዋል።

የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃን መሠረት ያደረጉ ስራዎችን በመስራት የተፈጥሮ ሀብታችንን በዘላቂነት የማስጠበቅ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ አስታውቀዋል።

በክልሉ የሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎችን ለማልማት ምቹ አጋጣሚዎችን በተገቢው መንገድ በመጠቀምና ልማትን በማረጋገጥ ህብረተሰቡን ከልማቱ ተጠቃሚ በማድረግ እራሱን መመገብ እንዲችል የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛል ብለዋል።

የተፋሰስ ልማት ሥራው ለምርታማነትና የአካባቢን የአየር ንብረት ለማስጠበቅ ያለውን ጠቀሜታ በመረዳት ህብረተሰቡም ሆነ በየደረጃው የሚገኘው የመንግስት አመራር የእኔነት ስሜትን በመላበስ በይበልጥ እንዲሳተፍ ጥሪ አቅርበዋል።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል የተፋሰስ ልማት ስራ ለተከታታይ 45 ቀናት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አቶ የሺዋስ አስታውቀዋል።

# ኢንስቲትዩቱ ከእንስሳት ስጋና ወተት ምርቶች 59 ሚሊዮን ዶላር አገኘ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሰባት ወራት ከስጋና ወተት ማቀነባበር፣በተረፈ ምርት፣ በማር፣ በግመል ወተት ማቀነባበር ከወጪ ንግድ 59 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን የእንስሳት ሃብት ኢንስቲትዩት ገለጸ።

በእንስሳት ሃብት ኢንስቲትዩት የሶሺዮ ኢኮኖሚክስና እሴት ሰንሰለት አስተዳደር ምርምር ዘርፍ አስተባባሪ ዶክተር ሳህሉ ሙሉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከተገኘው 59 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላር ውስጥ ስጋና እርድ ተረፈ ምርት 57 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ዶላር በመሆን የእቅዱን 99 በመቶ ይሸፍናል።

ዘጠኝ ሺህ 630 ቶን ስጋ ወደ ውጭ በመላክ ባለፉት ሰባት ወራት 57 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል። በአጠቃላይ የእንስሳት ምርቱ ሲታይ 10 ሺህ 434 ቶን በመላክ 59 ነጥብ አንድ ዶላር ገቢ ተገኝቷል።

እንደዶክተር ሳህሉ ማብራሪያ፤76 በመቶ ገደማ ከስጋ ምርት ገቢ ከፍተኛ ድርሻውን የሚይዘው የፍየል ስጋ ወጪ ንግድ ነው። 50 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዶላሩ የተገኘው ከፍየል ስጋ ወጪ ንግድ ነው። ከስጋም ሆነ ከእንስሳት ምርት ወጪ ንግድ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል።

ከምርት መዳረሻ ገበያ ትልቅ ድርሻ ያለው በበግ፣ በፍየል ስጋ እና በዳልጋ ከብት የገልፍ አገራት ላይ ነው። ከነዚህም አገራት የተባበሩት አረብ ኤምሬት ዱባይና ሳውዲ አረቢያ ገበያ ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ። ኳታር እና ባህሬንም ለኢትዮጵያ ገበያ መዳረሻዎች ናቸው።

የእርድ ተረፈ ምርት ተቀባይ ነባር ደንበኞች ወደሆኑት የገልፍ አገራት እና ሩቅ ምስራቅ አገራት ቬየትናም፣ ሆንግ ኮንግ እና አንዳንድ የአፍሪካ አገራት እየተላከ መሆኑንም ነው የጠቆሙት።

ወተትን በተመለከተ ለውጭ ገበያ የሚላከው የግመል ወተት መሆኑን የጠቆሙት ዶክተር ሳህሉ፤ በዋነኝነትም እየተላከ የሚገኘው ሱማሌ ላንድ፣ ጂቡቲና ሶማሊያ መሆኑን ጠቁመዋል። የማር ምርትም ወደ አውሮፓና ሩቅ ምስራቅ አገራት እንደሚላክም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ካላት የእንስሳት ሃብት አንጻር እጅግ በጣም ብዙ ስራ መሰራት ይኖርበታል። በተለይም እርባታውን ከማዘመን፣ ገበያ ተኮር ከማድረግ፣ የምርት ጥራትና ደህንነትን ከመጠበቅ፣ የተሳለጠ የንግድ ስርዓት ከማስፈን እና ህገ ወጥ ንግድን ከማስቆም አንጻር ብዙ ስራ ሊሰራ ይገባል ብለዋል።

የምግብ ደህንነትና ጥራትን በማሻሻል የመዳረሻ ገበያን ለማስፋት በዋናነት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው።

የምግብ ደህንነትና ጥራት ሁኔታ ከተሻሻለ፣ የአረባብ ስርዓቱ ከዘመነ፣ የእንስሳት ጤና ስርዓቱ በተገቢው መንገድ ተግባራዊ በማድረግ ተቀባይ አገራትን የማስፋፋት ስራ መስራት እንደሚቻልም ነው የተናገሩት።

ተቀባይ አገራት ከእንስሳት ምርት ጥራትና ደህንነት አንጻር የምርት መቀበያ መስፈርት አላቸው። መስፈርቱን ለማሟላት የተጀመሩ ስራዎችን በማስፋፋት መሰራት የሚገባው ስራ ሊሰራ ይገባል ሲሉ ዶክተር ሳህሉ ተናግረዋል።

ከእንስሳት ምርት ጥራትና ደህንነት በኩል ተገቢውን ስራ በመስራት ማቅረብ ከተቻለ ምርቶቻችንን የሚቀበሉ ሰፋፊ ገበያዎች አሉ። ለዚህም ከእንስሳት ምርት ጥራትና ደህንነት በኩል የተጀመረውን ስራ ዳር ማድረስ ይጠበቃል ነው ያሉት።

# ሚኒስቴሩ በ6 ወራት ለ901 ባለጉዳዮች ነጻ ጥብቅና አገልግሎት ሰጥቷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በስድስት ወራት በተለያዩ ምክንያቶች አቅም ላነሳቸው ለ901 ዜጎች የነፃ ጥብቅና አገልግሎት መስጠቱን የፍትሕ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በፍትሕ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አወል ሱልጣን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በስድስት ወር ውስጥ በራሳቸው አቅም ተከራክረው ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ማስከበር ላልቻሉ 901 ሰዎች የነጻ ጥብቅና አገልግሎት ተሰጥቷል።

ነፃ አገልግሎቱ ከተሰጣቸው 901 ሰዎች መካከል 588ቱ ሴቶች ሲሆኑ 3013ቱ ወንዶች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ከአጠቃላዩ ነጻ ጥብቅና አገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል 77ቱ ሕጻናት፣ 46ቱ አረጋውያን፣ 19ኙ አካል ጉዳተኞች እንዲሁም 5ቱ ደግሞ ኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው የሚገኝና የፋይናስ አቅማቸው ደካማ የሆኑ ሰዎች ናቸው ሲሉ አስረድተዋል።

ነፃ የጥብቅና አገልግሎት የተሰጣቸው ሰዎች በ2014 በጀት ዓመት የፍርድ ሂደቶቻቸው ሳያልቁ የመጡና በ2015 አዲስ የፍርድ ሂደታቸው የተጀመሩ መሆናቸውን ተናግረዋል።

አገልግሎቶቹ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች በሚገኙ 11 ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች አማካኝነት የተሰጠ ሲሆን፤ አገልግሎቱ የሕግ ምክር፣ የፍርድ ቤት ጥብቅና፣ የፍታብሔር ክስ ዝግጅትና ክርክሮችን ያካተተ መሆኑን አስታውቀዋል።

የፍትሕ ሚኒስቴር የጥብቅና ፈቃድ አስተዳደርና የነፃ ሕግ ድጋፍ አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ፍቃዱ ደምሴ በበኩላቸው፤ ሪፖርቱ እንደሚያመለክተው የነጻ ጥብቅና አገልግሎት አሰጣጡ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ43 በመቶ ብልጫ አለው።

የአገልግሎት ተጠቃሚው ቁጥርም ሆነ የአገልግሎት ስፋቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን የተናገሩት አቶ ፈቃዱ፤ ከ901 የነጻ ጥብቅና አገልግሎት ውስጥ በዳይሬክተሩ ስር ብቻ ለ418 ሰዎች ነፃ የህግ ከለላ አገልግሎት ሰጥተናል ብለዋል፡፡

በተለያዩ ሁኔታዎች ተከራክረው ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን ማስከበር ለማይችሉ ዜጎች ነፃ ጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለብን ያሉት ዳይሬክተሩ፤ አገልግሎቱን በትክክል ተረድተው በመልካም ስነ-ምግባር የሚያገለግሉ ባለሙያዎች እንዳሉ ሁሉ አልፎ አልፎ የተወሰኑ ባለሙያዎች ስራቸውን በአግባቡ መወጣት የማይፈልጉም ያጋጥማሉ ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ አቶ ፍቃዱ ገለጻ፤ ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ከሚፈልጉ ሰዎች በኩል ደግሞ ስለራሳቸውና ስለጉዳዩ የሚገልጽ በቂ መረጃ አለማቅረብ፣ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች እንደ አዲስ እንዲንቀሳቀስላቸው የመፈለግ እንዲሁም ከተመደበላቸው ጠበቃ ጋር ተስማምቶ ያለ መስራት ችግሮች ይስተዋላል።

አቶ ፍቃዱ አክለውም፤ በሕገወጥ መንገድ ተጠቃሚ ለመሆን የሀሰት መረጃ ይዘው ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ይሰጠን የሚሉ አካላት ስላሉ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ቁጥር ከፍተኛ ነው። ይሁንና በቂ ማጣራት ተደርጎ አገልግሎቱ ይሰጣል።

ነፃ የሕግ አገልግሎት በሚሰጥበት ጊዜ አዛውንቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ ሕፃናትና የኢኮኖሚ አቅም የሌላቸው ወጣቶች ተብለው በልየታ ምዝገባ ስለሚካሄድ ሁሉንም አካታች ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

አገልግሎቱ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብት ጥሰቶችን ለመቀነስ ያስችላል ያሉት አቶ ፈቃዱ፤ በትላልቅ ከተማዎች ያለው አገልግሎት ጥሩ የሚባል ቢሆንም እስከ ታችኛው እርከን ድረስ አገልግሎቱን በሰፊው ለመስጠት እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

# ዩኒቨርሲቲው ማህበረሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እያከናወነ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ በግብርና፣ በማዕድንና ቱሪዝም ላይ ያተኮሩ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ገለጸ፡፡

የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የምርምር፣ የማህበረሰብ አገልግሎትና ኢንዱስትሪ ትስስር ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ጋትሉዋክ ጋትኮስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው ከሚያከናውነው የመማር ማስተማር ሥራ በተጨማሪ የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ግብርና፣ ማዕድንና ቱሪዝም የዩኒቨርሲቲው የጥናትና ምርምር ትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸውን ጠቁመው፤ እየተሰሩ ያሉት ጥናትና ምርምር ሥራዎችም በእነዚህ ዘርፎች ላይ የሚያተኩሩ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

የተለያዩ የዶሮ ዝርያዎችን በማዳቀል የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎችን ለማህበረሰቡ እንዲቀርብ መደረጉን ያስታወሱት ዶክተር ጋትሉዋክ፤ ከዚህም በተጨማሪ ከጋምቤላ ክልል ጋር በመተባበር በዓሣ እርባታ ላይ የተሠሩ ምርምሮችን ወደ ፕሮጀክት እንዲቀየሩ በማድረግ በክልሉ ሦስት ቦታዎች ላይ የፓይለት ፕሮጀክት ትግበራ መጀመሩን ጠቅሰዋል፡፡

በዚህም በመረብ ሥራ፣ በመኖ ዝግጅትና በዓሣ ማስገር ላይ በአጠቃላይ 550 የሚደርሱ ወጣቶች በማህበር ተደራጅተው ወደ ሥራ እንዲገቡ መደረጉን ጨምረው ገልጸዋል፡፡

በቱሪዝም ዘርፍ ያሉ ሀብቶችን በምን መልኩ መልማት እንዳለባቸው የሚያመላክቱና በምን መልኩ እንክብካቤ መደረግ አለበት በሚለው ላይም የጥናትና ምርምር ሥራዎች መሰራቱን ጠቅሰው፤ የማዕድን ሀብቶች ላይ ያተኮሩ የተለያዩ ምርምሮች መከናወናቸውንም ገልጸዋል፡፡

በቀጣይነትም በሦስቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ አተኩሮ የግብርናውን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የግብርና ሜካናይዜሽን ሥራና የመስኖ ልማት ላይ ያተኮሩ ሥራዎችን እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ ክልሉ በቱሪዝምና ማዕድን ዘርፎች ላይ ያለውን እምቅ አቅም በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋልና የሕብረተሰቡ ተጠቃሚነት እንዲጨምር የሚያግዙ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ከተጀመሩበት እ.አ.አ ከ2018 ጀምሮ እስካሁን ድረስ 191 የሚደርሱ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ የሚሠሩ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በኢንተርኔት ጆርናሎች እንዲታተሙ፣ በዓመታዊ የጥናትና ምርምር ኮንፈረንሶች ላይ እንዲቀርቡ እና የማህበረሰቡን ችግር እንዲፈቱ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

## ትውልዱ የተከፈለለትን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከሚያደርጉት የነጻነት ተጋድሎ ሊመልሳቸው እና ሊበግራቸው አልቻለም::ኢትዮጵያ ነጻነቷን ጠብቃ የምትዘልቅ አገር እንድትሆን ይበልጥ ተጋድሏቸውን አጠናከሩት ያሉት ከንቲባዋ፤ ይሄም ትውልድ ሊያስቀጥል የሚገባው ብዙ የራሱን ታሪክ በመጻፍ ነው ሲሉ ገልጸዋል::

ወጣቱ ትውልድ አገራችን ከድህነት እንድትወጣ፣ አንድነቷ እና ሰላሟ እንዲጠበቅ በጥቃቅን ነገር የሚረበሽና በደም የተገነባን ታሪክ ለማፍረስ የሚቻኮል ከመሆን ይልቅ፤ አንዱ የሚገጥመውን ችግር ለመፍታት የሚወያይ፣የሚነጋገር እና በጋራ ትልቅ ታሪክ የሚጽፍ መሆን አለበት ሲሉ ተናግረዋል::

አንድነታችንን ከዚህም በላይ እናጠናክር፤ የጀግኖች አባቶቻንን ታሪክ እናክብር፤እንማርበት ሲሉም ከንቲባዋ አሳስበዋል::

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ በበኩላቸው፤ የሰማዕታቱን ቀን የምናስበው ለወጣቱ ትውልድ የአባቶችን የጀግንነት ታሪክ ለማውረስ መሆኑን ጠቁመዋል::

በንጉሱ ዘመን ይህ በአል በሰፊው የሚከበር ቢሆንም ጊዜው እየቆ እና መንግስት እየተቀየረ በመጣ ቁጥር ለበአሉ አከባበር እየተሰጠ ያለው ትኩረት በመቀነሱ ትውልዱ የአገሩን ታሪክ እረሳው መጥቷል ብለዋል::

የአሁኑ ትውልድ የአገሩን ታሪክ በመርሳት የውጮችን ታሪክ እየተከለ ነው ያሉት ልጅ ዳንኤል፤ በአላቱን መንግስት ተረክቦ ለህብረተሰቡ እና ለወጣቱ እስካላስተማረ ድረስ የአገሪቱ ታሪክ እየጠፋ ይሄዳል ሲሉ ገልጸዋል::

የወደፊት ኢትዮጵያን ሰላም ለማስቀጠል የሚቻለው የአገራችንን ታሪክ ተንከባክበን ለወጣቱ ትውልድ በጀግኖች አባቶች የተከፈለለትን የደም መስዋእትነት ስናከብርና ስናስጠብቅ ነው ሲሉ አስረድተዋል::

በመታሰቢያ ስነ-ስርዓቱ ላይ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር አባላት፣ የሃይማኖት አባቶች፣ ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች፣ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር አባላትና በርካታ ነዋሪዎች ተሳታፊ ሆነዋል::

## አህጉራዊ አጀንዳን ሲያጠናክር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሁኔታዎችን ያገናዘበ፤ አረንጓዴ ከባቢን የመፍጠር፣ ምርትን የማሳደግና መሰል ጠቃሚ አጀንዳዎች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ይገባል ነው ያሉት::

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ርዕሰ አካዳሚ ዶክተር ምሕረት ደበበ በበኩላቸው፤ “ምንም እንኳን የመጀመሪያው የፓን አፍሪካን እንቅስቃሴ አፍሪካን ከቅኝ ግዛት ማላላቀቅና ነፃነቷ ላይ ያተኮረ ቢሆንም፤ አዲሱ የፓን አፍሪካን መንፈስ አህጉራችን ሰላማዊና የበለፀገች እንድትሆን ማድረግ እንደሆነ አምናለሁ” ሲሉ ተናግረዋል::

አካዳሚው በአመራር ብቃት ግንባታ፣ የፖሊሲ ጥናቶችንና የማማከር ስራዎች ላይ ያተኮሩ በርካታ ስልጠናዎችን እንደሚሰጥ ዶክተር ምህረት ጠቅሰዋል::

ለከፍተኛ የመንግስት፣ የግልና ማሕበረሰብ ተቋማት አመራሮች የአመራር ክህሎት ስልጠናዎችን የመስጠት፤ ወደ ከፍተኛ አመራርነት ያልደረሱ ወጣት መሪዎች የአመራር ክህሎት ስልጠናዎች የመስጠትና ለውሳኔ ሰጪዎች በአመራር ዙሪያ የፖሊሲ ጥናት የማካሄድና የማማከር አገልግሎቶችን ሲሰጥ መቆየቱን አንስተዋል::

የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ፤ እድገት ተኮር አስተሳሰብ በፓን አፍሪካኒዝም እሳቤ የተቃኘ እንዲሆንና የአመራር አቅሞችን በመንግስትና የግሉ ዘርፍ በማጎልበት ተመራጭ እንዲሆን የተቋቋመ መሆኑንም ጠቁመዋል::

ለተለዋዋጭ ዓለም ፓን አፍሪካኒዝምን መልሶ ማነቃቃት በሚል ርዕስ በተካሄደው የመጀመሪያው የፓን አፍሪካኒዝም ፎረም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፣ የአፍሪካ መሪዎች ፣ ፖሊሲ አውጪዎች ፣ ምሁራን ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት እንዲሁም የወጣትና ሴቶች ተወካዮች በተገኙበት ትናንት ተካሂዷል::

## የአረንጓዴ አሻራ

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ በተካሄደው የመጀመሪያው የፓን አፍሪካኒዝም ፎረም ላይ የተገኙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ፓንአፍሪካኒዝም በ21ኛው ክፍለዘመን ትርጉሙ የኢኮኖሚ ጥገኝነትን ማስቀረት ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን ለመቻልና የበለፀገች አገር እንድትሆን በርትታ እየሰራች መሆኑን የገለፁት አቶ ደመቀ፤ ባለፉት ዓመታት ለአረንጓዴ አሻራ ትኩረት ሰጥታ መስራቷን ገልፀዋል።

እንደ አቶ ደመቀ ገለፃ፤ የአረንጓዴ አሻራ መርሀግብር አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ፋይዳ አለው፡፡የደን ጥበቃና የደን መልሶ ማቋቋም ፣የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ለአፈርና ውሃ ጥበቃ፣እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥን መከላከል ያስችላል፡፡

አፍሪካ የመሬት መሸርሸር እንዲሁም ድርቅና ርሀብ የጋራ ችግሮቿ ናቸው ያሉት አቶ ደመቀ፤ ለዚህም ትውልዱ የአረንጓዴ አሻራን ጥቅም ተገንዝቦ በስፋት ሊያስቀጥለው እንደሚገባ መክረዋል።

በመድረኩ ላይ ጥናታዊ ጽሁፍ ያቀረቡት የኢትዮጵያ የደን ልማት እና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሙያ የሆኑት ዶክተር አደፍርስ ወርቁ፤ በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር እንደተቻለ የተናገሩ ሲሆን፤ በተለይ ወጣቶችና ሴቶች ችግኝ በማፍላትና በመንከባከብ በስፋት ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በ2011 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ሲጀመር በአራት አመት ውስጥ 20 ቢሊዮን ችግኝ መትከልን አላማ አድርጎ የጀመረ ቢሆንም ከእቅዱ በላይ 25 ቢሊዮን ችግኞች መተከላቸውን ገልፀዋል።

ኢትዮጵያ በአረንጓዴ አሻራ መርሀግብር በውጭ ገበያ ተፈላጊ የሆኑ እንደ ቡናና መሰል ተክሎችን በስፋት ተክላለች።

ከዚህም በተጨማሪ በመርሀግብሩ የተለያዩ ፍራፍሬዎች ተተክለው ለውጭ ገበያ ማቅረብ መቻሉን ጥናታዊ ፅሁፍ አቅራቢው አስረድተዋል፡፡የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባለፈ የካርቦን ልቀትን በመቀነስ የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል ትልቅ ሚና እንደሚኖረውም ጠቅሰዋል።

በተጨማሪም መርሃ ግብሩ አገሪቱን አረንጓዴ ገጽታ በማላበስ፣ የገጠሩን ማህበረሰብ ህይወት በማሻሻል፣ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋም መልክዓ ምድር በመገንባት በኩል የተሳካ ውጤት ማስገኘቱንም ገልጸዋል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ከኢትዮጵያ ባለፈ ለሌሎች አፍሪካ ሀገራትም ጠቃሚ ነው ያሉ ሲሆን፤ ሀገራቶች፣ ድርጅቶች፣አመራሮች በዚህ ዘርፍ በትኩረት እንዲሰሩ የደን ልማት እና የአየር ንብረት ለውጥ ባለሙያ መክረዋል።

መርሃ ግብሩ ጎረቤት ሀገራት ለጋራ ተጠቃሚነት በጋራ እንዲሰሩ ለማድረግ አስፈላጊ ነው ያሉት ዶክተር አደፍርስ፤ የግጦሽ መሬት፣ የውሃና የደን ሃብት እጥረት ችግሮችን ለመፍታት አስችሏል፡፡

በተያያዘም በአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ በተካሄደው የፓን አፍሪካኒዝም ፎርም የተሳተፉ የሀገራት መሪዎች፤እንዲሁም በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የተመራው ልኡክ በአካዳሚው ችግኞችን ተክሏል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ችግሮችን በድርድርና በውይይት መፍታት-የለውጡ ዘመን ትሩፋት!

አምስተኛ ዓመቱን እያስቆጠረ ያለው ሀገራዊ ለውጥ በብዙ ፈተናዎች እየተናጠ ቢሆንም፤ እንደ ሃገር አዳዲስ እውነታዎችን እንድንለማመድ እድል እየሰጠን ነው። ከነዚህም ውስጥ አለመግባባቶችን በውይይትና በድርድር መፍታት መቻል መምጣታችን አንዱና ዋነኛው ነው።

የለውጥ ወቅት ካለው ውስብስብ ባሕሪያት አንጻር፤ ለብዙ አለመግባባቶች፤ ከዚህ በሚመነጩ ግጭቶችና ሁከቶች የሚጨናነቅበት ሁኔታ ብዙም አዲስ/ እንግዳ ነገር አይደለም፤ በየትኛውም የለውጥ ንቅናቄ በታየባቸው ሀገራት የተስተዋለና የሚስተዋል ነው።

ለውጥ በራሱ በአስተሳሰቦች ተቃርኖ/ በአሮጌ፤በቆየው እና በአዲስ አስተሳሰብ መካከል/ የሚፈጠር፤ የሚያድግና አቅም ገዝቶ ማኅበረሰብን የሚወርስ ከመሆኑ አንጻር የለውጥ /የአስተሳሰብ ሽግግሩ አልጋ በአልጋ የሚሆንበት አጋጣሚ አይኖርም። ይልቁኑ ብዙ ውጣውረዶች ይጠብቁታል።

በአንድ በኩል የለውጡ አስተሳሰብ የቀደመውን ያለአግባብ ተጠቃሚነቴን ያሳጣኛል በሚል በጠላትነት ፈርጆ የሚንቀሳቀስ ቡድንና/ኃይል መኖሩ፤በሌላ በኩል በለውጡ ወቅት ግራ መጋባቶችን ሥራዬ ብለው በመፍጠር አጋጣሚውን ወደ ሥልጣን መረማመጃ አቋራጭ መንገድ አድርገው ለመጠቀም የሚተጉ ኃይሎች መኖር ለለውጡ ዋነኛ ተግዳሮት ናቸው።

ከዚህ ባለፈም አጠቃላይ ስለሆነው የለውጡ አስተሳሰብና ለውጡ ይዞት ሊመጣ ስለሚችለው ትሩፋት ተገቢውን ግንዛቤ መያዝ ያልቻሉ፤ተገቢውን ግንዛቤ ለመያዝም ፈቃደኝነት የሌላቸው፤ሁሉንም በጥድፊያና በሩጫ ጀምረው ለመጨረስ የሚመክሩ ተጨማሪ ኃይሎች መኖራቸው ለለውጡ ስኬት በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ያደርጋቸዋል።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚያልፍ ለውጥ የቱንም ያህል ከፍያለ ማኅበራዊ ትሩፋት ይዞ ቢመጣም፤ እያንዳንዷን እንቅስቃሴ ከስሜትና ከእልህ በወጣ መንገድ፤በስክነት መምራት ያስፈልጋል። ይህንን ማድረግ አለመቻል ሊያስከትል የሚችለው አደጋ የከፋና ሃገርንና ሕዝብን ሊፈትን የሚችል ነው።

የለውጡን የአስተሳሰብ መሠረት በማኅበረሰብ ውስጥ እንዲሰርጽ ከማድረግ ጀምሮ ፤የለውጡ ትርክት "ከአሸናፊ ተሸናፊ "የቡድን ጩኸት ወጥቶ ሃገርንና ሕዝብን አሸናፊ ወደ ሚያደርግ አስተሳሰባዊ መሠረት መሸጋገር ይኖርበታል።

ይህ አይነቱ የለውጥ ጉዞ በባሕርይው/ከተገዛበት የአስተሳሰብ መሠረት/ብዙ ዋጋ መክፈልን፤ በተጨባጭም ሕዝባዊነትን የሚጠይቅ ነው። ከራስና ከቡድን ፍላጎት ወጥቶ ሀገርና ሕዝብን ማስቀደም የሚያስችል እውነተኛ ተቆርቋሪነት የሚፈተንበትም ነው ።

በተለይ እንደኛ አይነት "በአሸናፊ ተሸናፊ" ትርክት ረጅም ዘመን ላሳለፉ፤ትርክቱ የፖለቲካ ባህላቸው አልፋና ኦሜጋ ሆኖ ለሚሰማቸው ፖለቲከኞች፤ ሃገርንና ሕዝብን አሸናፊ ወደሚያደርግ አዲስ የፖለቲካ ባህል የሚደረግ ሽግግር ግራ መጋባትና ግርምት መፍጠሩ የማይቀር ነው።

በተለይም በለውጥ ወቅት የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በኃይል ከመድፈቅ ይልቅ በድርድርና በውይይት በመፍታት ፤ ለውጡን ዘላቂ አድርጎ ለማስቀጠል የሚወሰዱ እርምጃዎች፤ የለውጥ ኃይሉ ለለውጡ ያለውን ቁርጠኛነት በተጨባጭ አመላካች ናቸው።

በእኛም ሀገር የለውጥ ኃይሉ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ፤የሚያጋጥሙ ችግሮችን በድርድርና በውይይት ለመፍታት የሄደባቸው ርቀቶች በመላው ሕዝባችን፤ ከዚያም አልፎ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከፍ ያለ ተቀባይነትንና ከበሬታን አትርፏል።

የተፈጠሩ ዕድሎችን በአግባቡ ካለመረዳትና እና ቀደም ባለው ወቅት ለድርድርና ለውይይት ከነበረው የተዛባ አመለካከት የተነሳ አንዳንድ ወገኖች ዕድሉን መጠቀም እንዳይቻል በማድረጋቸው ሃገርና ሕዝብ ብዙ ዋጋ እንዲከፍሉ ሆኗል።

ይህም ሆኖ ግን የለውጥ ኃይሉ እያጋጠሙ ያሉ ሃገርን እንደ ሃገር የሚፈትኑ ከባባድ ጉዳዮችንና ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ በውይይት እና በድርድር እየፈታበት ያለው መንገድ ፤ሃገርና ሕዝብ አላስፈላጊ ዋጋ እንዳይከፍሉ ትልቅ ሀገራዊ አቅም መሆን ችሏል።

ችግር ፈጣሪዎች ሆኑ የችግር ነጋዴዎች በተናበበ ሁኔታ ሃገርን በማተራመስ ፤በሕዝብ ጭንቀት ፤ የልብ ስብራት ፤መከራና ስቃይ ለመቆመር የሚያደርጉትን ጥረት፤ ምኞትና ሟርታቸው ፍሬ እንዳያፈራ አድርጓል። ሕዝባችን በእያንዳንዱ የሴራ ትርክት የተሸከመውን ሸክም እንዲያራግፍ እና እፎይ እንዲል አስችሎታል ።

ከሁሉም በላይ እንደሃገር "ከአሸናፊ ተሸናፊ" ትርክት ወጥተን በውይይት እና በድርድር ችግሮቻችንን እየፈታን ወደ ምንመኛቸው ነገዎች መሻገር እንደምንችል ዓይናችን ተከፍቶ ማየት እንድንችል የተሻለ እድል ፈጥሯል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኢትዮጵያዊነት ከፍ እንዲል!

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ስለ ሀገር የተጠበቡ ጠቢባን ሀገርና ሰውነትን በአንድ መርፌና ክር ይሰፉታል:: እውነት ነው ሀገርና ሰውነት ከዚህ የተሻለ እውነት የላቸውም:: ሰውነት ከሀገር ጋር ሀገር ከሰውነት ጋር የተቆራኙ የአንድ ማንነት ሁለት መልኮች ናቸው:: ሰው ከሌለበት ሀገር ትርጉም የለውም:: ፍቅር ከሌለበት ሀገር ሙቀት የለውም:: ሰላም ከሌለበት ሀገር ጣዕም የለውም:: ሀገርን ሀገር ያደረጉት ሰው እና ከሰውነት ቀጥለው የሚመጡ የአብሮነት መንፈሶች ናቸው::

ከዚህ ጽንሰ ሀሳብ በመነሳት አብሮነታችን ለኢትዮጵያ ያለውን ዋጋ መቃኘት እንችላለን:: ልክ እንደ ዓድዋ የአንድነታችን ዋጋ የሚገለጽበት ብዙ ሀገራዊ ኩነቶች አሉ :: ልክ እንደ ዓባይ ግድባቸው ብዙሀነታችን የሚያስፈልግበት ምዕራፍ አለ:: እንደ ሀገር ተስፋ ሰንቀን እየኖርን ነው..የመልማትም ሆነ የማደግ ተስፋዎቻችን ፍሬ የሚያፈሩት በአንድነት ስንቆም ነው:: ለዘመናት ከተዋረድንበት የድህነት ነቀርሳ ለመሻር በእኔ ውስጥ እናተ፣ በእናተ ውስጥ እኔ መብቀል አለብን::

በተናጠል የቆመች ሀገር የለችም:: ተያይዘንና ተደጋግፈን ነው ከትናንት ዛሬን ያየነው:: በእኔ ውስጥ እናንተ በእናተ ውስጥ እኔ በቅዬ ነው ኢትዮጵያዊ የተባልነው:: ይሄን እውነት ለመረዳት አሁን ያለችውን ኢትዮጵያ ማየቱ በቂ ነው:: ኢትዮጵያ የቆመችው በብዙ እጆች ተደግፋ ነው:: ኢትዮጵያ ያማረችው በብዙ መልኮች ተውባ ነው:: ይሄ ውበት፣ ይሄ ድምቀት ደግሞ በጋራ የመቆም ውጤታችን ነው::

በችግሯ ሰአት ሆ ብለን የምንነሳው የኢትዮጵያ ጉዳት የእኛም ጉዳት ስለሆነ ነው:: እንደ ህዝብ ተነካክተንና ተጠጋግተን ተሳስረንም እየኖርን የብቻ ሰርግና መርዶ የለንም:: ደስታና ሀዘናችን የጋራችን ነው:: በጋራ እየኖርን እኔ ላይ ካልደረሰ የምንለው ነገር የለም:: ጉዳያችን ሰላም ከሆነ ሰላም ለማምጣት የአንድነት ሀሳብ ያስፈልገናል:: ጉዳያችን ዲሞክራሲ ከሆነ ከመንግስት ጋር ተቆራኝተን ዲሞክራሲን ሕያው ማድረግ ይጠበቅብናል::

ኢትዮጵያ ለአንድ ወገን የምንተዋት አይደለችም:: መንግስት ብቻውን ምንም አያደርጋትም:: አንድ ሰው..አንድ ቡድን ..አንድ ፓርቲ አይችላትም:: በጋራ ካልሆነ፣ በአብሮነት ካልሆነ ጥያቄዎቻችንን መመለስ አንችልም:: በመነጋገር ካልሆነ፣ በመተሳሰብ ካልሆነ ህልሞቻችንን መውለድ አንችልም:: አሁን ላይ በሰላም እጦት እየተሰቃየች ያለችው ለብቻ የተውናት ኢትዮጵያ ናት::

እንደ አብሮነታችን ሁሉ ሰላማችንን የምንመልሰው በአብሮነት ነው:: በመልካሙ ጊዜ አብረን ቆመን በችግር ጊዜ የምንለያይ ከሆነ ሀገርና ሰውነት ያልኳችሁ የአብሮነት ቅኔ ልክ አይመጣም:: ሀገር በእኛ ውስጥ፣ እኛም በሀገር ውስጥ ነው ልክ የምንሆነው:: ኢትዮጵያ የሚል..ከተናጠልነትና ከእኔነት የራቀ የጋራ ስም አለን::

በዚህ ስም ስንጠራ ለዘመናት ኖረናል:: ይሄን ስም ከፊት አድርገን ብዙ መሰናክሎችን ተራምደናል:: አሁንም ሰላማችን እንዲመለስ ከአፋችን ላይ የጠፋውን ይሄን ስም መመለስ አለብን:: ውበታችን የሚደበዝዘው ስንራራቅ ነው:: አንድነታችን የሚላላው ኢትዮጵያዊነትን ስንተው ነው።

ይብዛም ይነስም አለም ላይ የተነሱ ግጭቶች መነሻቸው እኔነት ነው:: መነሻቸው ከሀገር በላቁ ስሜቶች የመጣ ነው:: እኛም ሀገር በአብዛኛው ያጋጠሙን የሰላም እጦቶች ምክንያታቸው ይሄው ነው:: የሚያምርብን አድዋን የፈጠረ የአንድነት ስማችን ነው:: የሚያምርብን አባይን የገደበ የኢትዮጵያዊነት መልካችን ነው:: አድዋ የማን ታሪክ ነው?..የህዳሴ ግድብ የማን አሻራ ነው? የሁሉም ኢትዮጵያውያን እንደምትሉኝ ተስፋ አደርጋለው::

አድዋም ሆነ የህዳሴ ግድብ ኢትዮጵያዊነት የፈጠሩት..የጋራ እጆቻችን ናቸው :: ህብረትና አንድነት የፈጠሩት የኢትጵያዊነት መልክ ነው:: ከዚህ ውጪ ስም የለውም:: ሰላምም..ልማትም እንዲህ ነው..የእኔ የአንተ እየተባባልን የምንፈጥረው ሰላም፣ የምናመጣው ለውጥና ብልጽግና የለም::

የእኔ የአንተ እየተባባልን የምንፈጥራት የጋራ ኢትዮጵያ የለችም:: በእኔ በአንተ መባባል ውስጥ ልዩነት እንጂ አንድነት የለም:: "የፉክክር ቤት ሳየዘጋ ያድራል" እንደሚባለው በተፎካከርን ቁጥር ኢትዮጵያን እያራቆትናት፤ በተፎካከርን ቁጥር ድህነትን እየተለማመድነው ነው እንሄዳለን::

ለነገሩ ድህነትን ከተለማመድነው ቆየን..ከመለማመድም አልፈን ድህነት ሲነሳ አብሮ ስማችን የሚነሳባቸው ብዙ አጋጣሚዎችን አስተናግደናል:: ይሄ የማይገባ ማንነት ከሀገር በፊት ባስቀደምናቸው ድሪቶ ጉዳዮቻችን የተፈጠረ ነው:: ይሄ ነውር በፉክክር ሳንዘጋው ያሳሰርነው የኢትዮጵያ ጉዳይ የወለደው ነው:: ከድህነትም ሆነ ከኋላ ቀርነት ለመውጣት አንድ አቋራጭ መንገድ ብቻ አለን እርሱም ኢትዮጵያን ማስቀደም ነው::

በዚህች ምድር ከሀገር በላይ ትልቅ ነገር የለንም:: ከሀገር የበለጠ ውብ ነገር አልተሰጠንም:: ኢትዮጵያ ለሁላችንም እኩል፣ ለሁላችንም አንድ አይነት መልክ ያላት ነች:: ፖለቲካችን ውስጥ የሚፈጠረው የሀሳብ ልዩነት ኢትዮጵያን የሚያደምቅ እንጂ የሚያደበዝዝ መሆን የለበትም:: ማህበራዊ መስተጋብራችን ውስጥ የሚፈጠሩ የሀሳብ ልዩነቶች በኃላፊነት ስሜት ለኢትዮጵያ ከመቆርቆር የመነጩ መሆን ይገባቸዋል::

እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያን ያደመቀ የፖለቲካ ስርአት ጠምቶናል:: እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያን የጠቀመ የፖለቲከኞች ውህደትም እንፈልጋለን:: ሁሉም ስርአት፣ ሁሉም ውህደት ኢትዮጵያ ልትኖርበት የሚገባ ነው:: ይሄ አካሄድ ፖለቲካችንን ለውጥ ፈጣሪ፣ ማህበረሰባችንን ደግሞ ሰላም ፈላጊ ያደርጋቸዋል:: ይሄ አካሄድ ኅብረ ብሄራዊ ኢትዮጵያዊነትን ያለመልማል::

መቼም የትም ኢትዮጵያ ያለችበት ፖለቲካና ሀሳብ ነው የሚያስፈልገን:: ህዝብ የቀደመበት፣ ትውልድ የታሰበበት ስርአትና ውህደት ነው የሚጠቅመን:: ሰላሞቻችን የሚመጡት፣ ተስፋዎቻችን የሚሰምሩት በዚህ መንገድ ላይ ስንራመድ ብቻ ነው:: በድምቀቷ ውስጥ እንዳለን ሁሉ በኢትዮጵያ መደበዘዝ ውስጥ ሁላችንም እንጸልማለን:: ከጽልመት የሚያወጡን ደግሞ ከግላዊነት የራቁ የአንድነት ታሪኮች ናቸው:: ልክ እንደ አድዋና፣ እንደ አንባላጌ፣ እንደ ካራማራና እንደ ኡጋዴን አይነት የጋራ ታሪኮች::

አንድ ነን..በየትኛውም አጉሊ መነጽር እዩት ከአንድነት ውጪ ሌላ ትርጉም የለንም:: ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአንድ ገመድ የታሰረ ብዙ ፍልጥ ነው:: ያ ሁሉ ብዙ አይነት ፍልጥ በአንድ ልጥ ነው የታሰረው:: ፍልጡ እኛ ነን..ፍልጡ ብዙሃነታችን ነው:: ፍልጡ መልክ፣ ቋንቋ፣ ብሄራችን ነው:: ፍልጡ ወግ ባህል ስርአታችን ነው:: ፍልጡ ታሪክ ትውፊታችን ነው:: ይሄ ሁሉ ድብልቅልቅ ማንነት ደግሞ ኢትዮጵያዊ በሚባል በአንድ ልጥ ታስሯል::

ከዚህ ማንነታችን ውጪ እኔና እናንተ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ትርጉም የለውም:: ከሀገር ግለኝነትን ስናስበልጥ፣ ከአንድነት መለያየትን ስናስቀድም የታሰርንበትን የኢትዮጵያዊነት ልጥ እያላላን ነው:: ስንፎካከር፣ በራስ ወዳድነት ስንቆም የታሰርንበትን የኢትዮጵያነት ልጥ እየገዘገዝን ነው:: የታሰርንበት ገመድ ተፈታ ማለት ኢትዮጵያዊነት ተበተነ ማለት ነው:: እንዳንበተን ተፋቅሮ መኖርን እንልመድ:: ልጣችን እንዳይላላ በሰላምና በእርቅ መኖርን ባህል እናድርግ::

እኔ እናተን ነኝ..እናተም እኔን ናችሁ:: የሆነ ነገራችሁ እኔጋ አለ..የኔም የሆነ ነገሬ እናተ ጋ አለ:: ተወራርሰን..ተዋህደን የቆምን ህዝቦች ነን:: ይሄ ማንነት ሰላምን የፈጠረ፣ አንድነትን የጸነሰ ማንነት ነው:: ይሄ ማንነት ለአለም ኩራት የሆነች፣ ለአፍሪካ መድህን የሆነችን ኢትዮጵያ የፈጠረ ነው:: እናም በእኛ ውስጥ.. እናም በእኔና በእናተ ውስጥ የሚያምርብን ሰላምና አንድነት ብቻ ነው::

ሰላም እንደ እኔና እንደ እናንተ የሚያምርበት የለም:: ፍቅር እንደ ኢትዮጵያዊነት የሚደምቅበት የለም:: አንድነት እንደ ሀበሻ የሚዋብበት የለም:: መለያየት በጣም ያስጠላል.. እኛ ላይ ደግሞ እጅግ በጣም ያስጠላል:: ምክንያቱም ተዋደን የቆምን፣ ተፋቅረን ከዛ እዚህ የመጣን ህዝቦች ስለሆንን::

ሀገር ከእኔና ከእናንተ ውጪ ትርጉም የላትም:: የሀገር ህልውና በእኛ ፍቅር ውስጥ ነው ያለው:: የእኛ ህልውና ደግሞ በሀገር ሉአላዊነት ውስጥ የሚገለጥ ነው:: እኛና ኢትዮጵያ ላንለያይ የተጨባበጥን፣ ላንለያይ የተዋሃድን ነን:: ይሄ ውህደታችን ትናንት ላይ ባለታሪክ እንዳደረገን ዛሬም ያስፈልገናል:: ይሄ መጨባበጣችን ትናንት ላይ ሰላም ፈጣሪዎች እንዳደረገን ዛሬም ሰላም ላጣነው ለእኛ ያስፈልገናል::

ሀገር የእንጀራ ሌማት ናት..ሰንበሌጥና ስንደዶ፣ አለላና አክርማ ያሳመሯት:: ብዙ አይነት መልኮች፣ ብዙ አይነት ውበቶች ያቆነጇት:: ሀገር የወርቅ ሙዳይ ናት..ደማቅ ቀለሞች የቀለሟት:: እኛም የሀገራችን ውበቶች ነን:: ኢትዮጵያ የቆነጀችው በእኔና በእናተ በሌላውም ሰው ኅብረ ብሄራዊ ባህልና ወግ፣ ልማድና ስርአት ነው::

የእኛ ባህልና ወግ፣ ልማድና እምነት የኢትዮጵያ ውበቶች ናቸው:: እንደ እንጀራ ሌማት በውበትና በደም ግባት ያቆነጀናት እኛ ነን:: ብዙሀነታችን ሀገራችንን ደግፎ ያቆመ የመሰረት ድንጋይ ነው:: በብዙነታችን ውስጥ የሚፈጠር ማንኛውም ልዩነት ሀገራችንን የሚነቀንቅ ነው:: የአንዳችን አለመኖር ኢትዮጵያን ያደበዝዛታል:: የአንዳችን መጉደል ኢትዮጵያዊነትን ያጠይሙታል::

እነሆ ታላቅ እውነት..ሀገር ማለት እኔ፣ እናተና ሌላውም ሰው ነው:: እንሆ ታላቅ ጥያቄ..ሀገር ማለት እኔ አንተና ሌላው ሰው ከሆነ እኔ በአንተ ውስጥ፣ አንተ በኔ ውስጥ መኖር እንዴት አቃተን? ሀገር ማለት እኔ አንተና ሌላው ሰው ከሆነ በተወራረስናቸው ባህልና ወግ፣ ልማድና ስርአት ፍቅርን መስበክ እንዴት ተሳነን? በእኔ ውስጥ አንተ በአንተ ውስጥ እኔ ከጎደልን እኮ ሙሉዎች አይደለንም::

እኔ ባለ ሀገር የሆንኩት በአንተ መኖር፣ በአንተ ወንድምነት ነው:: እናንተም፣ ባለሀገር የሆናችሁት በእኔ መኖር፣ በእኔ ወንድምነት ነው:: እኔና አንተ ከሌለን ኢትዮጵያ አትኖርም:: በአጉል እምነት ኢትዮጵያዊነት ከግለኝነት እንዳያንስ ለስሜታችን ልጓም እናብጅለት:: በአጉል እምነት ራስወዳድነታችን ከወንድማማችነታችን እንዳይገዝፍ ልከኛ እንሁን::

በተጓዝነው ስር የሰደደ የእኔነት ልክፍት ሰላማችንን ተነጥቀናል:: እንደ ሀገር ጠውልገናል:: እንደ ሕዝብ ብዙ ነገር አጥተናል:: ትውልዱ የሚያርፍበትን የአዲስ ዘመን ስፍራ ነፍገነዋል:: ተጠያቂዎች ነን:: ስለሆነም ሃሳብ ያስፈልገናል ሃሳቡም የአንድነት ፣ የእርቅ፣ የሰላምና የፍቅር ሊሆን ይገባል!

# ዘመናዊ ፋሽኖቻችን

## በአንጋፋዎቹ ሲቃኙ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

አራት ኪሎ ቱሪስት ሆቴል በግምት በስልሳዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ አንድ አዛውንት ማኪያቷቸውን አዘው በረንዳው ላይ ቁጭ ብለዋል። ሽበት ጣል ጣል ባደረገበት አፍሮ ጸጉራቸው ላይ ኮፍያ ደፍተውበታል። በነጭ ሸሚዝ ላይ ከረባታቸውን አስረው፣ ጥቁር ካቦርታቸውን ደርበው ከግራጫ ካኪ ሱሪያቸው ጋር ሲታዩ ዘናጭ ስለመሆናቸው አያጠራጥርም። ወንበር ስቤ አጠገባቸው ቁጭ አልኩ። ሰውዬው እንደ አለባበሳቸውም ንግግራቸው የሚጣፍጥና ጨዋታ አዋቂ ናቸው። ቁጭ ብለን ስንጨዋወት ድንገት አንዲት ወጣት ሴት እርቃኗን ለመሆን እሩብ ጉዳይ የሆነ አጭር ስስ ጉርድ ቀሚስ፣ እንብርቷን ከሚያሳይ አጭር ቲሸርት ጋር ለብሳ በታኮ ጫማዋ መሬቱን እየደቃች ስትገባ ድንገት አይናችንን ሳበችው፡፡ ወደ ውስጥ ከገባች በኋላ.. ወደኔ ዞር አሉና “አዬ ይሄ ትውልድ..በቃ ፋሽኑ እንዲህ ሆነ” ብለው ዝም አሉ። እኔም በከፈቱልኝ ቀዳዳ ሰተት ብዬ ገባሁና ፋሽን ድሮና ዘንድሮ ምን መልክ አለው ስል ላወጋቸው ወደዱኩኝ። “የፊት ጥርሴ አለመውለቁን እንዳታይ ጊዜ መቼም ጥሎ የሚነጉድ ባዳ ነውና እኔም በወጣትነቴ አራዳ ነበርኩኝ” አሉ ገና ጨዋታዬን ስጀምር።

**እንዲያው ፋሽን በናንተ ጊዜ እንዴት ነበር?**

“በእኛ ጊዜማ ከስር ቦላሌ ሱሩያችንን ታጥቀን፣ በሸሚዙ ላይ የሳሪያን ኮቷን ጣል አድርገን፣ አፍሮ ጸጉራችንን በጠር በጠር እናደርጋትና በከተማው ላይ ጎምለል እያልን በኩራት ነበር የምንሄደው። ግርማ ሞገሱም የተለየ ነበር። ሴቷም ብትሆን በረዥም ሽንሽን ቀሚሷ በእጇቿ አምባሮቹን ደርድራ፣ ከጆሮዋ ሎቲዋን አንጠልጥላ፣ ሽር እያለች ስትሄድ ውበቷን እያደነቀ ከዓይን ያውጣሽ የሚል እንጂ እንደ ዘንድሮው እንዲህ ማንነትን የሚያስገምት አለባበስ ከየት መጥቶ” አሉ ከፊታቸው ላይ ትዝታ እየተነበበ።

ሁለተኛውን ጥያቄ አስከተልኩኝ፤ አራዳነት በእናንተ ጊዜ እንዴት ነበር የሚገለጸው? “አራዳነት ማለትማ የራስህና የሀገርህ በሆነ ፋሽን እራስህን መስልህ ሌሎችም አንተን እንዲመስሉ ማድረግ እንጂ ያልሆንከውን ሆነህ መገኘት አይደለም። ከባሕልና ሥርዓት ውጭ የሆነ አራዳነት ትርፉ የሰው ዓይን ውስጥ መግባት ብቻ ነው።”

ፋሽን ጠቃሚነቱ ወይም ጎጂነቱ ለሁሉም በእኩል ይገለጻል? ለምሳሌ ያህል ስለፋሽን ምንነት የማይረዱ ታዳጊ ወጣቶች ጭምር በዚህ ነገር ተጠምደው ይገኛሉ ይህንን እንዴት ይመለከቱታል?

“ልጆች በባሕሪያቸው በሌላ ያዩትን ሁሉ ለመሆን ይፈልጋሉ። ጥሩነቱም ሆነ መጥፎነቱ አይታያቸውም። ለዚህ ጉዳይ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉም ወላጆቻቸውን ከአቅማቸው በላይ ያስጨንቋቸዋል። የፋሽንን ምንነት በቅጡ ስለማያውቁት ዓይኖቻቸው ያረፈበት ነገር ሁሉ ልባቸውም ይወደዋል። የእነርሱ ዓለምም እሱ ብቻ መስሎ ይታያቸዋል። በልጆች ላይ ሲሆን ከጥቅሙ ይልቅ ጎጂነቱ ያመዝናል።

ምናልባት ይሄ የቴክኖሎጂውና ዘመናዊነቱ የፈጠረው ነገር ነው ብለው ያስባሉ? ቀጣዩ ጥያቄ ነበር፤ “ቴክኖሎጂው ጥሩ ነገር ሆኖ ሳለ በሌላ በኩል ደግሞ ትውልዱ ማንነቱን እያስረሳውም ነው። አሁን አሁን ጫማ ለማሰር እንኳን ኢንተርኔት ነው የሚያዩት። ፋሽን ወይም ዘመናዊነት በራሱ መጥፎ አይደለም፣ ችግሩ ፋሽንን የምናሳይበት መንገድ ነው። እሳት ያበስላልም ያቃጥላልም። ሁሉም ነገር እንደ አያያዙ ይወሰናል። ፋሽን የሕይወታችን የመጀመሪያ ዓላማ አድርገን ልንቆጥረው አይገባም።”

**በእናንተ ትውልድ የሚነቀፍና ነገር ግን በዚህኛው ትውልድ እንደ ፋሽን ከሚታዩ ነገሮች ምን አስተዋሉ?**

“ትላንትና አዲስ ሱሪ ገዝተው ዛሬ ጉልበቱን እየቆራረጡ ይቦጫጭቁታል። መጀመሪያ አካባቢ አጥተው ወይ ተቸግረው ይመስለኝ ነበር። የኋላ ኋላ ነገሩ ሲገባኝ ለካስ ፋሽን መሆኑ ነው። በዚያ ላይ ደግሞ ለውሻም የማይሆን ሰንሰለት ከአንገታቸው ላይ ተሸክመው፣ ሱሪውም ከታች እየወረደባቸው እንደ እብድ በአንድ እጅ አንጠልጥለውት ሲሄዱ እመለከታለሁ። ሴቷም ከለበሰችው ቀሚስ እጥረት የተነሳ ስልኳ እንኳን ጎንበስ ብላ ለማንሳት ጭንቅ ይሆንባታል። ፋሽን እኮ ነፃነትን፣ ውበትን፣ ግርማ ሞገስን የሚሰጥና የሚያኮራ እንጂ እንደዚህ መላ ቅጣ አሳጥቶ የሚያሳብድ አይደለም። ወንዱ ከወንድነት፣ ሴቷም ከሴትነት ተራ ወጥታ ስመለከት ብዙ ነገሮች እንዳልገባን እገነዘባለሁ። ያገኘነውን ሁሉ መከተል የለብንም እንዲህ ካደረግን የሌላውን እየሰረቅን የራሳችንንም እናጣለን።”

ከአለባበስና የጸጉር ፋሽኖች ባሻገር ሙዚቃና ዳንሱ እንዲሁም የመዝናኛ ስፍራዎችም ጭምር አብረው የሚነሱና በየዘመናቱም ከፋሽኑ ዓለም ጋር ተጣምረው የሚሄዱ ናቸው። ታዲያ እነዚህ ነገሮችስ ከዛሬው ጋር እንዴት ያዩታል የናንተ ዘመን ትዝታስ እንዴት ያስታውሱታል ስል ጠየኳቸው።

“ በእኛ ዘመን እንደ አሁኑ የትየለሌ ፋሽኖች ያልበዙበት ሰዓት ነበር። ከምንም በላይ ግን የእኛ ዘመን ትልቁ ፋሽን ሙዚቃው ነበር። ሁሉም ሙዚቃ ይወዳል። ከአልባሳቱ ይልቅ የምናተኩረውም በሙዚቃው ውስጥ የሚኖረንን ተዝናኖት ነው። ከአመሻሹ ላይ ባሉን ፋሽኖች በተቻለን መጠን ቆንጆ ሆነን እንወጣና ከጓደኞቻችን ጋር ለአምስት ለስድስት ሆነን ከውቤ በረሃ አሊያም ከንፋስ ስልክ እንሄዳለን። እዚያ ታዲያ ሙዚቃው ሁሉ ቻቺና ቡጊ ነው። ሀገራዊ ዳንስና ጭፈራው ሁሉ ፍቅርና ደስታ ነበር የሚዘራብን። ስለገንዘብ አንጨነቅም። የአንዱ ለሌላውም ጭምር ይተርፋል። ጥቂት ገንዘብ ይዘን ለምኑም ሳናስብ በጋራ እስኪበቃን ተዝናንተን እንወጣለን። አሁንማ ለመዝናናት ወጥተህ እንኳን ስለ ገንዘብ እያሰብክ ከምኑም ሳትሆን እቤትህ ትመለሳለህ። ሁሉም ነገር ተቀይሯል። አለባበሱ ፈረንጂኛ፣ ሙዚቃው ፈረንጂኛ፣ ዳንሱም ተቀይሮ ከማንነት የወጣ ሆኗል።”

**ትውልዱ የራሱና የሀገሩን ባሕልና ፋሽን ተከታይ እንዲሆን ምን መደረግ አለበት?**

“ እርግጥ ነው በዚህ ዘመን ልጆችን የሚለብሰውን እኛ ላንመርጥ እንችላለን። ነገር ግን ምርጫው ያማረና ባሕሉን የሚመስል እንዲሆን አስቀድመን ልናስተምረው ይገባል። የትኛውም ሃይማኖትና እምነት ከማኅበረሰብ ያፈነገጠን ፋሽን አይቀበልምና ከማንም በላይ እነርሱ ቢመክሩ ተሰሚነታቸው ከፍ ያለ ነው።” በማለት የመጨረሻውን ምክረ ሀሳባቸውን አስቀመጡ።



# ታላቅ ቅናሽ ወይስ ....?

**ቦጋስ አበበ**

ኢትዮ ቴሌኮም ከቅርብ ቀናት ወዲህ ለደንበኞቹ በሚያቀርባቸው የተለያዩ ጥቅል አገልግሎቶች ላይ ተጨማሪ ጉርሻ እንደሚሰጥ ይታወቃል። ለምሳሌ 50 ሜጋባይት የኢንተርኔት ጥቅል የሚገዛ ደንበኛ ተጨማሪ 50 ሜጋባይት ይመረቅለታል። ያም ሆኖ በርካቶች ተጨማሪ ጉርሻው ትክክል እንዳልሆነና የገዙት ጥቅልና ጉርሻው ብዙም ሳይጠቀሙበት እያለቀባቸው መሆኑን ሲያማርሩ ይሰማል። ቅሬታው ትክክል ይሁን አይሁን ጉዳዩን ለኢትዮ ቴሌኮም ልተወውና ይህ የቅናሽ ጉዳይ ወዳስታወሰኝ ትዝብት ልግባ።

ከሰሞኑ ወቅታዊ ጉዳይ ልጀምር። ባለፈው የካቲት 07/2015 የፍቅረኛሞች ቀን(ቫላንታይን ደይ) በተለያዩ ሀገራት እንደወትሮው መከበሩ ይታወቃል። በኢትዮጵያም ይህ በዓል በተለይም በከተማ ወጣቶች ዘንድ በስፋት መከበር ከጀመረ ቆይቷል። ታዲያ ይህን በዓል አስመልክቶ በየቡቲኮች ለበዓሉ ዋነኛ ድምቀት የሆኑ ቀይ አልባሳት ላይ ታላቅ ቅናሽ በሚል ተለጥፎባቸው ማየት የተለመደ ነው። በዓሉ ከምዕራባውያን የመጣ በመሆኑ በሀገራችን መከበር አለመከበሩ ብዙ ክርክሮችን የሚያስነሳ ጉዳይ በመሆኑ ወደሱ ጉዳይ አልገባም። ግን በርካቶች ይህን በዓል አስመልክቶ ቀይ አልባሳት ላይ ታላቅ ቅናሽ ከሚደረግ ይልቅ እንደ ቀይ ሽንኩርትና ቀይ ጤፍ ላይ ቅናሽ ቢደረግ ለሰፊው ሕዝብ እንደሚጠቅም የሚሰጡት አስተያየት አዝናኝ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ወደ ቁም ነገሩ ስገባ በዚህ ወቅት በየቡቲኮቹ ታላቅ ቅናሽ ተብሎ የሚቸበቸቡ አልባሳት እውነት ታላቅ ቅናሽ ተደርጎባቸው ነው? ብለን ከጠየቅን መልሱ ለየቅል ሆኖ እናገኘዋለን። ይህን በዓል ብቻም ሳይሆን በአዘቦት ቀን ታላቅ ቅናሽ ተብለው የሚሸጡ ነገሮች ሁሉ እውነት ታላቅ ቅናሽ ተደርጎባቸው አይደለም። ታላቅ ቅናሽ የምትለው መሪ ቃል ዝም ብላ ገበያ መሳቢያ እንጂ እውነት እንዳልሆነ ዞር ዞር ብሎ ገበያውን መቃኘት ይቻላል።

> ታላቅ ቅናሽ የሚል የገበያ ጥሪ አይተን አንድ ቡቲክ ዘው ብለን ገብተን አንድ ሱሪ ለመግዛት ብንፈልግ የሚጠራው ዋጋ ሱሪው ታላቅ ቅናሽ ሳይደረግበት ስንት እንደነበር ስናሰላው ጆሮን ጭው ሊያደርግ ይችላል

ታላቅ ቅናሽ የሚል የገበያ ጥሪ አይተን አንድ ቡቲክ ዘው ብለን ገብተን አንድ ሱሪ ለመግዛት ብንፈልግ የሚጠራው ዋጋ ሱሪው ታላቅ ቅናሽ ሳይደረግበት ስንት እንደነበር ስናሰላው ጆሮን ጭው ሊያደርግ ይችላል። ሕዝቡም ታላቅ ቅናሽ የሚለው መሪ ቃል የነጋዴው የታላቅ ሽያጭ የገበያ ስትራቴጂ መሆኑ እየገባው የመጣ ይመስላል። ሆን ብሎ ታላቅ ቅናሽ የሚል ማስታወቂያ አይቶ ብቻ በማመን ወደ መሸጫ ሱቆች የሚሄድ ሰው ያን ያህል ነው። በእርግጥ ታላቅ ቅናሽ ብለው በመጠኑም ቢሆን ቀነስ አድርገው የሚሸጡ ነጋዴዎች የሉም ማለት አይደለም። እንዲህ አይነቶቹ ነጋዴዎች ታላቅ ቅናሽ እያሉ ታላቅ ሽያጭ ከሚያደርጉ ነጋዴዎች ጋር እኩል ላለመወቀስ “እውነተኛ ቅናሽ” ብለው በሌላ መንገድ የሚመጡት ወደው አይመስለኝም። ያው “እውነተኛ ቅናሽ” የሚለው በራሱ እውነት መሆኑን እርግጠኛ መሆን ባይቻልም።

አንዳንዶቹ ነጋዴዎች ደግሞ አሉ ከዚህም በተለየ ስልት ገበያ ለመሳብ ሌላ መንገድ የሚከተሉ። እነዚህ ነጋዴዎች በተለይም በቡቲኮቻቸው የሚሸጡት እቃ ላይ ዋጋውን በመለጠፍ ታላቅ ቅናሽ ከሚለው ማስታወቂያ በተሻለ ገዢን ለመሳብ የሚጥሩ። እነዚህ በአንፃሩ የተሻሉ ይመስላል። የነዚህ ችግር ግን የለጠፉት ዋጋ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ቁርአን ቃል አይለወጥም። ገዢ ተከራክሮ ዋጋ አስቀንሼ ገዛለሁ ማለት እዚህ አይሠራም።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንድ ሌላ ጉዳይ ላንሳ። በዓላትን ተከትሎ በትልልቅ ከተሞች ኤግዚቢሽንና ባዛሮች የተለመዱ ናቸው። በአነስተኛ ከተሞች ደግሞ ተጓዥ ባዛሮች በስፋት ይታወቃሉ። የበዓል ወቅትን ተከትሎ በየዓመቱ ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር ለመግዛት ከሚያዘወትሯቸው የገበያ ማዕከላትና ዝግጅቶች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተመራጭ የሆኑት ባዛሮች ይገኙበታል።

አንዳንድ ሰዎች የእቃዎች ዋጋ በባዛር ገበያ እንደሚቀንስ ያስባሉ። ሌሎቹም ደግሞ ውጭ ከሚሸጠው ምንም ዓይነት የዋጋ ልዩነት እንደሌለው ሲናገሩ ይደመጣሉ። የዋጋ ቅናሽ ባይኖርም የተለያዩ እቃዎችን ከባዛር ገበያ ለመሸመት ወደ ኤግዚቢሽን ማዕከል የሚመጣ የሰው ቁጥር ግን ቀላል የሚባል አይደለም።

ያም ሆኖ በነዚህ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች ላይ እቃዎች ላይ ይህ ነው የሚባል የዋጋ ቅናሽ እንደሌለ እግር ጥሎት የሄደ ሁሉ ማስተዋሉ አይቀርም። በመደበኛ ሱቅ 1000 ብር የሚገዛው የባህል ቀሚስ በባዛሩ ላይ 1200 ሲሸጥ ልናገኘው እንችላለን። ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶች በነጋዴዎች በኩል ይቀርባሉ። አንዳንድ አነስተኛ እቃ የሚሸጡ ነጋዴዎች ባዛሩ ላይ ለመሳተፍ የሚከፍሉትን ወጪያቸውን ለመሸፈን ዋጋ ይጨምራሉ። አንዳንዶች ደግሞ ራሳቸው ነጋዴዎች ሳይሆኑ የሽያጭ ሠራተኛ ሆነው እቃው ከሚሸጥበት ዋጋ ከፍ አድርገው በመሸጥ ትርፉን ወደ ኪሳቸው ለማስገባት ሲሉ እሳት የላሰ ምላሳቸውን ተጠቅመው ሸማቹን ያሳምናሉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የዋጋ ግሽበቱ የደረሰበት ደረጃ እና ሃገሪቷ ያለችበት የፀጥታ ሁኔታ እንደ ምክንያት ይነሳሉ።

በበዓል ወቅቶች በከተሞች የሚዘጋጁት የባዛር ገበያዎች ዋና ዓላማ በርካታና የተለያዩ እቃዎችንና ሸቀጦችን በቅናሽ ዋጋ በአንድ ስፍራ ለሸማቹ ማቅረብ እንደሆነ ይታሰባል። ነገር ግን አብዛኞቹ ባዛሮች ላይ የዋጋ ቅናሽ አለ በሚለው ላይ ሁሉም ሸማቾች አይስማሙም። ያም ሆነ ይህ ታላቅ ቅናሽ ብሎ የእውነትም ቅናሽ በሌለበት ከንቱ ማስታወቂያ የምንታለል ሰዎች ካለን በቅድሚያ የገበያ ጥናት ማድረግ ለሁላችንም ይበጃል ለማለት ያህል ነው።

## ነፃ ሃሳብ

# በአጉል እምነት ኢትዮጵያዊነት ከብሔር እንዳያንስ ለስሜታችን ልጓም እናብጅለት!

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ስለ ሀገር የተጠበቡ ጠቢባን ሀገርና ሰውነትን በአንድ መርፌና ክር ይሰፉታል። እውነት ነው ሀገርና ሰውነት ከዚህ የተሻለ እውነት የላቸውም። ሰውነት ከሀገር ጋር ሀገር ከሰውነት ጋር የተቆራኙ የአንድ ማንነት ሁለት መልኮች ናቸው። ሰው ከሌለበት ሀገር ትርጉም የለውም። ፍቅር ከሌለበት ሀገር ሙቀት የለውም። ሰላም ከሌለበት ሀገር ጣዕም የለውም። ሀገርን ሀገር ያደረጉት ሰው እና ከሰውነት ቀጥለው የሚመጡ የአብሮነት መንፈሶች ናቸው።

ከዚህ ጽንሰ ሀሳብ በመነሳት አብሮነታችን ለኢትዮጵያ ያለውን ዋጋ መቃኘት እንችላለን። ልክ እንደ ዓድዋ የአንድነታችን ዋጋ የሚገለጽበት ብዙ ሀገራዊ ኩነቶች አሉ። ልክ እንደ ህዳሴ ግድባችውን ብዙኃነታችን የሚያስፈልግበት ምዕራፍ አለ። እንደ ሀገር ተስፋ ሰንቀን እየኖርን ነው..የመልማትም ሆነ የማደግ ተስፋዎቻችን ፍሬ የሚያፈሩት በአንድነት ስንቆም ነው። ለዘመናት ከተዋረድንበት የድህነት ነቀርሳ ለመሻር በእኔ ውስጥ እናንተ፣ በእናንተ ውስጥ እኔ መብቀል አለብን።

በተናጠል የቆመች ሀገር የለችም። ተያይዘንና ተደጋግፈን ነው ከትላንት ዛሬን ያየነው። በእኔ ውስጥ እናንተ በእናንተ ውስጥ እኔ በቅዬ ነው ኢትዮጵያዊ የተባልነው። ይሄን እውነት ለመረዳት አሁን ያለችውን ኢትዮጵያ ማየቱ በቂ ነው። ኢትዮጵያ የቆመችው በብዙ እጆች ተደግፋ ነው። ኢትዮጵያ ያማረችው በብዙ መልኮች ተውባ ነው። ይሄ ውበት፣ ይሄ ድምቀት ደግሞ በጋራ የመቆም ውጤታችን ነው።

በችግሯ ሰዓት ሆ ብለን የምንነሳው የኢትዮጵያ ጉዳት የእኛም ጉዳት ስለሆነ ነው። እንደ ሕዝብ ተነካክተንና ተጠጋግተን ተሳስረንም እየኖርን የብቻ ሠርግና መርዶ የለንም። ደስታና ኃዘናችን የጋራችን ነው። በጋራ እየኖርን እኔ ላይ ካልደረሰ የምንለው ነገር የለም። ጉዳያችን ሰላም ከሆነ ሰላም ለማምጣት የአንድነት ሀሳብ ያስፈልገናል። ጉዳያችን ዲሞክራሲ ከሆነ ከመንግሥት ጋር ተቆራኝተን ዲሞክራሲን ሕያው ማድረግ ይጠበቅብናል።

ኢትዮጵያ ለአንድ ወገን የምንተዋት አይደለችም። መንግሥት ብቻውን ምንም አያደርጋትም። አንድ ሰው.. አንድ ቡድን ..አንድ ፓርቲ አይችላትም። በጋራ ካልሆነ፣ በአብሮነት ካልሆነ ጥያቄዎቻችንን መመለስ አንችልም። በመነጋገር ካልሆነ፣ በመተሳሰብ ካልሆነ ሕልሞቻችንን መውለድ አንችልም። አሁን ላይ በሰላም እጦት እየተሰቃየች ያለችው ለብቻ የተውናት ኢትዮጵያ ናት።

እንደ አብሮነታችን ሁሉ ሰላማችንን የምንመልሰው በአብሮነት ነው። በመልካሙ ጊዜ አብረን ቆመን በችግር ጊዜ የምንለያይ ከሆነ ሀገርና ሰውነት ያልኳችሁ የአብሮነት ቅኔ ልክ አይመጣም። ሀገር በእኛ ውስጥ፣ እኛም በሀገር ውስጥ ነው ልክ የምንሆነው። ኢትዮጵያ የሚል.. ከብሔርና ከእኔነት የራቀ የጋራ ስም አለን። በዚህ ስም ስንጠራ ለዘመናት ኖረናል። ይሄን ስም ከፊት አድርገን ብዙ መሰናክሎችን ተራምደናል። አሁንም ሰላማችን እንዲመለስ ከአፋችን ላይ የጠፋውን ይሄን ስም መመለስ አለብን። ውበታችን የሚደበዝዘው ስንራራቅ ነው። አንድነታችን የሚላላው ኢትዮጵያዊነትን ትተን አማራ ነኝ፣ ኦሮሞ ነኝ..ትግሬ ነኝ ስንል ነው።

ይብዛም ይነስም ዓለም ላይ የተነሱ ግጭቶች መነሻቸው እኔነት ነው። መነሻቸው ከሀገር በላቁ የብሔር ስሞች የመጣ ነው። እኛም ሀገር በአብዛኛው ያጋጠሙን የሰላም እጦቶች ምክንያታቸው ይኸው ነው። የሚያምርብን ዓድዋን የፈጠረ የአንድነት ስማችን ነው። የሚያምርብን ዓባይን የገደበ የኢትዮጵያዊነት መልካችን ነው። ዓድዋ የማን ታሪክ ነው?..የህዳሴ ግድብ የማን አሻራ ነው? መቼም የአማራና የኦሮሞ ወይም የትግራይ

እንደ አብሮነታችን ሁሉ ሰላማችንን የምንመልሰው በአብሮነት ነው። በመልካሙ ጊዜ አብረን ቆመን በችግር ጊዜ የምንለያይ ከሆነ ሀገርና ሰውነት ያልኳችሁ የአብሮነት ቅኔ ልክ አይመጣም

እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

ዓድዋም ሆነ የህዳሴ ግድብ ኢትዮጵያዊነት የፈጠሩት..የጋራ እጆቻችን ናቸው። ኅብረትና አንድነት የፈጠሩት የኢትዮጵያዊነት መልክ ነው። ከዚህ ውጪ ስም የለውም። ሰላምም..ልማትም እንዲህ ነው..የእኔ የአንተ እየተባባልን የምንፈጥረው ሰላም፣ የምናመጣ ለውጥና ብልጽግና የለም። የእኔ የአንተ እየተባባልን የምንፈጥራት የጋራ ኢትዮጵያ የለችም። በእኔ በአንተ መባባል ውስጥ ልዩነት እንጂ አንድነት የለም። "የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል " እንደሚባለው በተፎካከርን ቁጥር ኢትዮጵያን እያራቆትናት፤ በተፎካከርን ቁጥር ድህነትን እየተለማመድንው ነው እንሄዳለን ።

ለነገሩ ድህነትን ከተለማመድነው ቆየን.. ከመለማመድም አልፈን ድህነት ሲነሳ አብሮ ስማችን የሚነሳባቸው ብዙ አጋጣሚዎችን አስተናግደናል። ይሄ አስጸያፊ ማንነት ከሀገር በፊት ባስቀደምናቸው ድሪቶ ጉዳዮቻችን የተፈጠረ ነው ። ይሄ ነውር በፉክክር ሳንዘጋው ያሳሰርነው የኢትዮጵያ ጉዳይ የወለደው ነው። ከድህነትም ሆነ ከኋላ ቀርነት ለመውጣት አንድ አቋራጭ መንገድ ብቻ አለን እርሱም ኢትዮጵያን ማስቀደም ነው።

ከሀገር ትልቅ ነገር የለንም። ከሀገር የበለጠ ውብ ነገር አልተሰጠንም። ኢትዮጵያ ለሁላችንም እኩል፣ ለሁላችንም አንድ ዓይነት መልክ ያላት ነች። ፖለቲካችን ውስጥ የሚፈጠረው የሀሳብ ልዩነት ኢትዮጵያን የሚያደምቅ እንጂ የሚያደበዝዝ መሆን የለበትም። ማኅበራዊ መስተጋብራችን ውስጥ የሚፈጠሩ የሀሳብ ልዩነቶች በኃላፊነት ስሜት ለኢትዮጵያ ከመቆርቆር የመነጬ መሆን ይገባቸዋል።

እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያን ያደመቀ የፖለቲካ ሥርዓት አላየንም። እስካሁን ድረስ ኢትዮጵያን የጠቀመ የፖለቲከኞች ውሕደት አላየንም። ሁሉም ሥርዓት፣ ሁሉም ውሕደት ኢትዮጵያ እንዳለችበት የሚናገር ነው። ፍጻሜው ግን የሆነ ቡድንን፣ የሆነ ብሔርን፣ የሆነ ፓርቲን የሚጠቅም ሆኖ የሚጠናቀቅ ነው። ይሄ አካሄድ ፖለቲካችንን ነውጥ ፈጣሪ፣ ማኅበረሰባችንን ደግሞ ሰላም ፈላጊ አድርጎ እዛና እዚህ አስቀምጧቸዋል። ይሄ አካሄድ ኢትዮጵያዊነትን ሽሮ የብሔር አስተሳሰብን ፈጥሯል።

መቼም የትም ኢትዮጵያ ያለችበት ፖለቲካና ሀሳብ ነው የሚያስፈልገን። ሕዝብ የቀደመበት፣ ትውልድ የታሰበበት ሥርዓትና ውሕደት ነው የሚጠቅመን። ሰላሞቻችን የሚመጡት፣ ተስፋዎቻችን የሚሰምሩት በዚህ መንገድ ላይ ስንራመድ ብቻ ነው። በድምቀቷ ውስጥ እንዳለን ሁሉ በኢትዮጵያ መደበዝዝ ውስጥ ሁላችንም እንጸልማለን። ከጽልመት የሚያወጡን ደግሞ ከብሔር የራቁ የአንድነት ታሪኮች ናቸው። ልክ እንደ ዓድዋና፣ እንደ አምባላጌ፣ እንደ ካራማራና እንደ ኦጋዴን አይነት የጋራ ታሪኮች።

አንድ ነን..በየትኛውም አጉሊ መነጽር እዩት ከአንድነት ውጪ ሌላ ትርጉም የለንም። ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በአንድ ገመድ የታሰረ ብዙ ፍልጥ ነው። ያ ሁሉ ብዙ ዓይነት ፍልጥ በአንድ ልጥ ነው የታሠረው። ፍልጡ እኛ ነን..ፍልጡ ብዙኃነታችን ነው። ፍልጡ መልክ፣ ቋንቋ፣ ብሔራችን ነው። ፍልጡ ወግ ባሕል ሥርዓታችን ነው። ፍልጡ ታሪክ ትውፊታችን ነው። ይሄ ሁሉ ድብልቅልቅ ማንነት ደግሞ ኢትዮጵያዊ በሚባል በአንድ ልጥ ታስሯል።

ይሄ ነው ማንነታችን..ከዚህ ውጪ እኔና እናንተ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ትርጉም የለውም። ከሀገር ብሔርን ስናስበልጥ፣ ከአንድነት መለያየትን ስናስቀድም የታሰርንበትን የኢትዮጵያዊነት ልጥ እያላላን ነው። ስንፎካከር፣ በራስ ወዳድነት ስንቆም የታሰርንበትን የኢትዮጵያነት ልጥ እየገዘገዝን ነው። የታሰርንበት ገመድ ተፈታ ማለት ኢትዮጵያዊነት ተበተነ ማለት ነው። እንዳንበተን ተፋቅሮ መኖርን እንልመድ። ልጣችን እንዳይላላ በሰላምና በእርቅ መኖርን ባሕል እናድርግ።

እኔ እናንተን ነኝ..እናንተም እኔን ናችሁ። የሆነ ነገራችሁ እኔጋ አለ..የኔም የሆነ ነገሬ እናንተ ጋ አለ። ተወራርሰን..ተዋሕደን የቆምን ሕዝቦች ነን። ይሄ ማንነት ሰላምን የፈጠረ፣ አንድነትን የጸነሰ ማንነት ነው። ይሄ ማንነት ለዓለም ኩራት የሆነች፣ ለአፍሪካ መድኅን የሆነችን ኢትዮጵያ የፈጠረ ነው። እናም በእኛ ውስጥ.. እናም በእኔና በእናንተ ውስጥ የሚያምርብን ሰላምና አንድነት ብቻ ነው።

ሰላም እንደ እኔና እንደ እናንተ የሚያምርበት የለም። ፍቅር እንደ ኢትዮጵያዊነት የሚደምቅበት የለም። አንድነት እንደ ሀበሻ የሚዋብበት የለም። መለያየት በጣም ያስጠላል.. እኛ ላይ ደግሞ እጅግ በጣም ያስጠላል። ምክንያቱም ተዋደን የቆምን፣ ተፋቅረን ከዛ እዚህ የመጣን ሕዝቦች ስለሆንን።

ሀገር ከእኔና ከእናንተ ውጪ ትርጉም የላትም። የሀገር ሕልውና በእኛ ፍቅር ውስጥ ነው ያለው። የእኛ ሕልውና ደግሞ በሀገር ሉዓላዊነት ውስጥ የሚገለጥ ነው። እኛና ኢትዮጵያ ላንለያይ የተጨባበጥን፣ ላንለያይ የተዋሓድን ነን ። ይሄ ውሕደታችን ትላንት ላይ ባለታሪክ እንዳደረገን ዛሬም ያስፈልገናል። ይሄ መጨባበጣችን ትላንት ላይ ሰላም ፈጣሪዎች እንዳደረገን ዛሬም ሰላም ላጣነው ለእኛ ያስፈልገናል።

ሀገር የእንጀራ ሌማት ናት..ሰንበሌጥና ስንደዶ፣ አለላና አክርማ ያሳመሯት። ብዙ ዓይነት መልኮች፣ ብዙ ዓይነት ውበቶች ያቆነጇት። ሀገር የወርቅ ሙዳይ ናት..ደማቅ ቀለሞች የቀለሟት። እኛም የሀገራችን ውበቶች ነን። ኢትዮጵያ የቆነጀችው በእኔና በእናንተ በሌላውም ሰው ባሕልና ወግ፣ ልማድና ሥርዓት ነው።

የእኛ ባሕልና ወግ፣ ልማድና እምነት የኢትዮጵያ ውበቶች ናቸው። እንደ እንጀራ ሌማት በውበትና በደምግባት ያቆነጀናት እኛ ነን። ብዙኃነታችን ሀገራችንን ደግፎ ያቆመ የመሠረት ድንጋይ ነው። በብዙኃነታችን ውስጥ የሚፈጠር ማንኛውም ልዩነት ሀገራችንን የሚነቀንቅ ነው። የአንዳችን አለመኖር ኢትዮጵያን ያደበዝዛታል። የአንዳችን መጉደል ኢትዮጵያዊነትን ያጠይሙታል።

እነሆ ታላቅ እውነት..ሀገር ማለት እኔ፣ እናንተና ሌላውም ሰው ነው። እነሆ ታላቅ ጥያቄ..ሀገር ማለት እኔ አንተና ሌላው ሰው ከሆነ እኔ በአንተ ውስጥ፣ አንተ በኔ ውስጥ መኖር እንዴት አቃተን? ሀገር ማለት እኔ አንተና ሌላው ሰው ከሆነ በተወራረስናቸው ባሕልና ወግ፣ ልማድና ሥርዓት ፍቅርን መስበክ እንዴት ተሳነን? በእኔ ውስጥ አንተ በአንተ ውስጥ እኔ ከጎደልን እኮ ሙሉዎች አይደለንም።

እኔ ባለ ሀገር የሆንኩት በአንተ መኖር፣ በአንተ ወንድምነት ነው። እናንተም፣ ባለሀገር የሆናችሁት በእኔ መኖር፣ በእኔ ወንድምነት ነው። እኔና አንተ ከሌለን ኢትዮጵያ አትኖርም። በአጉል እምነት ኢትዮጵያዊነት ከብሔር እንዳያንስ ለስሜታችን ልጓም እናብጅለት። በአጉል እምነት ራስ ወዳድነታችን ከወንድማማችነታችን እንዳይገዝፍ ልከኛ እንሁን።

በተጓዝንው ስር የሰደደ የእኔነት ልክፍት ሰላማችንን ተነጥቀናል። እንደ ሀገር ጠውልገናል። እንደ ሕዝብ ብዙ ነገር አጥተናል። ትውልዱ የሚያርፍበትን የአዲስ ዘመን ስፍራ ነፍገነዋል። ተጠያቂዎች ነን። ሀሳብ ያስፈልገናል.. የአንድነት ሀሳብ፣ የእርቅና የሰላም ሀሳቦች ያስፈልጉናል።

ኢኮኖሚ

ግብርና

# የሐር ልማት -የአርሶ አደሩ ተጓዳኝ የገቢ ምንጭ

ስምስም መንግሥቱ

የኢትዮጵያ አርሶ አደር የእለት ኑሮውንም ሆነ የዓመት ጉርሱን የሚያገኘው ዓመት ጠብቆ ከሚያገኘው ምርት ነው። ለግብርና ልማቱ ከሚያስፈልገው በተጨማሪ ሠርግም ሆነ ማኅበር የሚደግሰው፣ ሕክምናውንም የሚያደርገው፣ ሌሎችንም ማኅበራዊ ጉዳዮችን የሚያከናውነው በግብርና ምርቱ ነው። ይህ በመሆኑም ምርቱን አቆይቶ በደህና ዋጋ ለመሸጥ ዕድል አያገኝም።

ጠንካራ አርሶ አደር ካልሆነና ሰፊ የእርሻ መሬት ከሌለው የዓመት ቀለቡን እንኳን ለመሸፈን ይቸገራል። አብዛኛው አርሶ አደርም በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ስለመሆኑ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ያሳያል። አርሶ አደሩ በዓመት ከሚያከናውነው የግብርና ሥራ ተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ሥራ የመሥራት ባሕል ባለማዳበሩ ለሥራ የደረሱ ልጆቹም ቢሆኑ ሥራ ፈጣሪ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል።

የምንገኝበት ዘመን ደግሞ በዓመት በማምረት ፍላጎትን ለማሟላት ቀርቶ ቀለብንም ለመቻል አስቸጋሪ የሆነበት ነው። ለዚህም ነው የዘርፉ ባለሙያዎች አርሶ አደሩ በቀደመው ዘመን ይዞት የመጣውን የሥራ ባሕል መቀየር እንዳለበት፣ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ልማቶች ላይም ትኩረት አድርጎ እንዲሠራ የሚመክሩትና አቅጣጫ የሚሰጡት።

መንግሥትም በዚህ ረገድ ልማትን ከሚደግፉ አጋሮች ጋር በመሆን አርሶ አደሩን እያበረታታ ይገኛል። በቅርቡ የተተገበረው የሌማት ትሩፋትም ለእዚህ በሁነኛ አብነት ሊጠቀስ ይችላል። አርሶ አደሩ ከሰብል ልማት ጎን ለጎን ከብት በማርባት፣ በወተት ልማት፣በንብ ማነብና በሌሎችም በሚያከናውናቸው ተጓዳኝ ገቢ ማስገኛዎች ተጠቃሚ ለመሆን ያስችለዋል።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሰፊ የሥራ ዘርፍ ያለው ግብርናው በመሆኑ አርሶ አደሩም ሆነ ልጆቹ ከዓመት ዓመት ያልተቋረጠ የግብርና ሥራ በማከናወን ተጓዳኝ በሆነ ልማት የሚሠማሩበት እድል እየተመቻቸ ይገኛል። ሰሞኑን በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ ዞን አዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ ተገኝተን ይህንኑ ጥረት ተመልክተናል።

በወረዳው አነስተኛ መሬት ያላቸው፣ገቢያቸው ዝቅተኛ የሆነና ከቤተሰብ ጋር የሚኖሩ በማኅበር የተደራጁ ወጣቶች ወረዳው ባመቻቸላቸው የእርሻ መሬት ላይ ስንዴ፣በቆሎ፣ቦሎቄ እያፈራረቁ ያለማሉ፤ አትክልትና ፍራፍሬ እያለሙም ናቸው።

ከዚህ በተጓዳኝ በተሰጣቸው የመሥሪያ ቦታ ላይ ደግሞ ለሐር ልማት የሚውል ጉሎ በመትከል ቅጠሉን ለሐር ትል በማዋል ወደ ሐር በመቀየር፣ ሸጠው ገቢ ያገኛሉ። የጉሎው ፍሬም ለገበያ ውሎ ተጨማሪ ገቢ ይሆናል። ወጣቶቹ በዚህ መንገድ ኑሮአቸውን ለመለወጥ ጥረት ሲያደርጉ ለመመልከት ችለናል።

እንዲህ ያለው የአካባቢው ወጣቶች ተጠቃሚነት እንዲጎለብት ደግሞ ከማስተርካርድ ፋውንዴሽን ጋር በጋራ በትብብር የሚሠራው ዓለምአቀፍ ስነ ነፍሳትና ሳይንስ ሥነምሕዳር ማዕከል(ኢ ሲ ፒኤ) የሥልጠና፣ የቁሳቁስና የክትትል ድጋፍ እያደረገላቸው ይገኛል። ይህ የተመቻቸው የገቢ ማስገኛ የልማት መርሐ ግብር ሴት አርሶ አደሮችን የበለጠ ተጠቃሚ እያደረገ እንደሆነም መገንዘብ ችለናል።

ከማኅበሩ ተጠቃሚዎች መካከል ያነጋገርናቸው ወይዘሮ ራዲያ ነሻህ እንደገለጹት፤ 36 ወንዶችና 64 ሴቶች ሆነው ነው በ2012ዓም በማኅበር ተደራጅተው ወደ ልማቱ የገቡት።ወረዳቸው በአጠቃላይ ለልማቱ የሰጣቸው ሰባት ሄክታር መሬት ሲሆን፣ከዚህ ውስጥ አራቱን ሄክታር ስንዴ፣በቆሎ፣ቦለቄ፣አትክልትና ፍራፍሬ እያፈራረቁ በማልማት ይጠቀማሉ።በቀሪው መሬት ላይ ደግሞ ለሐር ልማቱ የሚሆን ጉሎ መትከያ፣እንዲሁም የሐር ትል ልማት ለሚያከናውኑበትና የመሸጫ ቤት ሠርተውበታል። ተደራጅተው ወደ ሥራ የገቡበት ወቅት ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ የተስፋፋበት ጊዜ በመሆኑ የተጠናከረ ሥራ አልሠሩም። ከ2013 ዓ.ም ወዲህ ግን በስፋት በመንቀሳቀሳቸው ለውጤት የሚያበቃ ተስፋ አግኝተውበታል።

‹‹ከልማቱ የሚወድቅ ነገር የለም። ሁሉም ገቢ ነው›› የሚሉት ወይዘሮ ራዲያ እንደገለጹልን፤ ለሐር ትል የሚውለው የጉሎ ቅጠሉን ለትሉ ምግብነት ካዋሉ በኋላ ፍሬውን ለገበያ በማዋል ገቢ ያገኙበታል። ትሉን ወደ ሐር ከቀየሩ በኋላም ፈትለውና አዳውረው ነው ለገበያ የሚያውሉት። ከእርሻ መሬታቸው ያገኙት ምርት ተጨምሮ በአጠቃላይ በያዝነው በጀት ዓመት ከ230ሺ ብር በላይ ገቢ አግኝተዋል። ይህም ጠንክረው በመሥራታቸው ያገኙት ውጤት እንደሆነም ወይዘሮ ራዲያ ተናግረዋል። አምና 90 ሺህ ብር እንዳገኙ ነው ያስታወሱት።

ልማቱ በአጠቃላይ መነቃቃት እንደፈጠረላቸው ወይዘሮ ራዲያ ይገልጻሉ። እሳቸው እንደተናገሩት፤ በልማቱ የተሻለ ገቢ በማግኘታቸው በመበረታታት ወደፊት በስፋት ለማልማት ለመስኖ ውሃ መሳቢያ ሞተር(ፓምፕ) ገዝተዋል። ከወረዳ በብድር የወሰዱትንም የስንዴ ዘር መመለስ ችለዋል።

ጠንክሮ መሥራት ውጤታማ እንደሚያደርግ እንዳዩበትና ያለሥራ ያባከኑትን ጊዜ በቁጭት ይገልጻሉ። በትምህርታቸው 12ኛ ክፍል ደርሰዋል። ትምህርት ለመቀጠልም ሆነ ሥራ ተቀጥረው የመሥራት እድል አላገኙም፤ ትዳር መሥርተው እየኖሩ ናቸው።

ያላቸው የእርሻ መሬት አነስተኛ በመሆኑ የቤተሰብ ፍላጎት ለማሟላት አላስቻላቸውም። አሁን ላይ ግን ከሌሎች ጋር በመሆን በተጓዳኝ ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ መሆናቸው ለወደፊት ኑሮአቸው እንደሚሻሻል ተስፋ አድርገዋል። ቤተሰቦቻቸው ከግብርናው ጎን ለጎን እንዲህ ያለ ተጓዳኝ ሥራ ሠርተው ቢሆን፣ የአምራች ደሀ አይሆኑም ነበር ይላሉ። ወቅትን ጠብቀው አንድ የምርት አይነት ላይ በመወሰናቸው እንደተጎዱም ይናገራሉ።

እንደ ወይዘሮ ራዲያ፤አሁን እያከናወኑት ያሉት የሐር ልማትና የግብርና ሥራ ብዙ ድካም ይጠይቃል። በተለይም የሐር ልማቱ ለአካባቢው አዲስ በመሆኑ ብዙዎች ፍላጎት አላደረባቸውም። ተስፋም አላደረጉም። በዚህ ምክንያት በማኅበር ተደራጅተው ወደ ሥራው ከገቡት አንድ መቶ አባላት መካከል ወደ 30 የሚሆኑት አቋርጠዋል። ከ36 ወንዶች የቀሩት ሦስት ብቻ ናቸው።

ተስፋ ያልቆረጡት የቀሩት ተሞክሮ ለማግኘት አርባ ምንጭ ድረስ ሄደዋል። የግብርና ሥራውን የትዳር አጋሮቻቸው እንዲያግዟቸው በማድረግ ነው ተጠናክረው የቀጠሉት።

ፈትለውና አዳውረው ያዘጋጁትን ሐርም ለገበያ ለማቅረብ በአዲስ አበባ ከተማ የገበያ ትስስር እንደተፈጠረላቸው የነገሩን ወይዘሮ ራዲያ፤ የምርቱ ሁኔታ ቋሚ እንዳልሆነና በደንብ ምርት የሚገኘው በሙቀት ወቅት እንደሆነ ነው የገለጹት።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ቅዝቃዜ ለትሎቹ ምቹ አይደለም። በዚህም ምርቱ አንዳንዴ ይቀንሳል። አቅም እየፈጠሩ ሲሄዱና እርዳታም ማግኘት ከቻሉ በኤሌክትሪክ ኃይል በመታገዝ በዘመናዊ መሣሪያ ለመጠቀም እቅዱ አላቸው። ፈትለው ያዘጋጁትን ሐርም ወደ ልብስ የመቀየር እቅድ አላቸው። እቅዳቸውም ወደፋብሪካ ደረጃ የማሳደግ ነው። እንዲህ ያለውን ትልቅ ተስፋ ለመጣል አሁን ኢ ሲ ፒኤ በክህሎትና በተለያየ እገዛ እያደረገላቸው ያለው ድጋፍና ወረዳውም አስፈላጊ በሆነው ሁሉ ከጎናቸው በመሆኑ እንደሆነም አጫውተውናል።

> በአሁኑ ጊዜም አልሚዎቹ የትሉን እንቁላል ደረጃ ጠብቀው ወደ ሐር እስከሚቀየር ያለውን ሂደት ተከትለው የሚሰሩበትን ክህሎት በማግኘታቸው ራሳቸውን ችለው በመሥራት ውጤት ላይ ደርሰዋል፡፡ አንድ ኪሎ የሐር ጥጥ እስከ 400 ብር ያወጣል፤ ጥጡ ወደ ክር ሲቀየር ደግሞ በኪሎ እስከ 1400 ብር ያወጣል፤ በዚህም አልሚዎቹ ውጤታማ መሆን ይችላሉ

በዓለምአቀፍ ሥነ ነፍሳትና ሳይንስ ሥነምሕዳር ማዕከል(ኢ ሲ ፒኤ) የኦሮሚያ ክልል ሞይሽ ፕሮጀክት ኃላፊ አቶ ተሾመ ኩመላ፤አጠቃላይ የልማቱን እንቅስቃሴና ፤፤ለሐር አልሚዎቹ እየተደረገላቸው ስላለው ድጋፍ እንደገለጹት፤ ማዕከሉ ከመንግሥት ጋር በመሆን እያደረገ ባለው በዚህ ድጋፍ ሥራ በአምስት ዓመት ውስጥ በግብርናው ዘርፍ ለአንድ መቶ ሺ ወጣቶች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እያደረገ ባለው እንቅስቃሴ 25 በመቶ የሚሆነው የሥራ ዕድል ለመፍጠር የታቀደው በሐር ልማት ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ በግብርናው ዘርፍ ትልቅ አቅም እያለ ነገር ግን ያልተሠራበት የሐር ልማት እንደሆነ የጠቆሙት አቶ ተሾመ፤ይህን መሠረት በማድረግ ተቋማቸው ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በተከናወነ ጥናት ወደ ልማቱ ሥራ መገባቱን አመልክተዋል። የሐር ልማት ሞቃታማ አካባቢዎችን የሚፈልግ እንደሆነና ኢ ሲ ፒኤም በሞይሽ ፕሮግራሙ፤አንዱ የመረጠው አካባቢ በኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ አዳሚቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ መሆኑን አስረድተዋል።

እንደ አቶ ተሾመ ማብራሪያ፤ በወረዳው የልማቱ ሥራ ከተጀመረ ሦስተኛ ዓመቱን የያዘ ሲሆን፤ከወረዳው ግብርና፣ከሥራ ዕድል ፈጠራ ጽሕፈት ቤቶችና ከመልካሳ ግብርና ምርምር ጋር ነው የሚከናወነው። ወደ ልማቱ ማስገባት የተቻለውም 42 የወጣቶች ቡድኖችን ነው። እስካሁን ባለው እንቅስቃሴ ተጠናክረው የቀጠሉት 32 ቡድኖች ናቸው። እነሱም ውጤታማ መሆን ችለዋል።

በቡድኑ ውስጥ የሚገኙት ወጣቶችም ከ18 እስከ 34 እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ፣80 በመቶ ሴቶች የሚገኙበት ነው። ኢ ሲ ፒኤ የተግባርና የንድፈ ሀሳብ ሥልጠና በመስጠት፤ የሐር ትሎችን የሚያራቡበት ቤት በመገንባት፣ ትሎቹ የሚራቡባቸውን ግብዓት በማቅረብ፣ሐር የሚፈትሉበትና የሚያዳውሩበትን መሣሪያና የሚያራቧቸውንም ትሎች በማቅረብ እንዲሁም ለትሎቹ የሚሆን የጉሎ ዘር በመስጠት ነው ወደልማቱ ያስገባቸው። በማዕከሉ ባለሙያዎችም ያልተቋረጠ ክትትል ይደረግላቸዋል። በአሁኑ ጊዜም አልሚዎቹ የትሉን እንቁላል ደረጃ ጠብቀው ወደ ሐር እስከሚቀየር ያለውን ሂደት ተከትለው የሚሠሩበትን ክህሎት በማግኘታቸው ራሳቸውን ችለው በመሥራት ውጤት ላይ ደርሰዋል።አንድ ኪሎ የሐር ጥጥ እስከ 400 ብር ዋጋ ያለው እንደሆነ፣ወደ ክር ሲቀይሩ ደግሞ በኪሎ እስከ 1400ብር እንደሚያወጣ እና ይህም ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው አቶ ተሾመ አመልክተዋል።

ዓመቱን ሙሉ የሐር ልማት ላይ ብቻ ይቆያሉ ማለት እንዳልሆነ የጠቆሙት አቶ ተሾመ፤ ወረዳው ባመቻቸላቸው የእርሻ መሬት ላይ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ነጭ ቦሎቄ እንዲያመርቱም ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ገልጸዋል። ቦሎቄውን ከዘር አቅራቢ ድርጅት በመውሰድ እንደሚያመርቱና አንዴ ያመረቱት ቦሎቄም ውጤታማ እንዳደረጋቸው አመልክተዋል። በመቀጠልም ስንዴ እንዳለሙ ጠቁመዋል።

እስካሁን ያካሄዱት ልማትም ወደ ገንዘብ ሲቀየር ከፍተኛ እንደሆነና አንድ የመንግሥት ተቀጣሪ በወር ከሚያገኘው እንደማይተናነስም ገልጸዋል። ይህም በጅምር ውጤት የሚታይ እንጂ የበለጠ በሠሩ ቁጥር ውጤታማነታቸውም አብሮ ከፍ እንደሚል አስረድተዋል። በተጨማሪም በሥራ ባህል ውስጥ እንዲያልፉ መደረጉ በራሱ ውጤታማ እንደሆነ ነው የገለጹት።

በኢስፒኤ ሞይሽ ፕሮግራም በጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ አራት ቀበሌ ውስጥ ባለሙያ ተቀጥሮላቸው ድጋፍ እያገኙ እንደሆነና የበለጠ ውጤት እንደሚጠበቅም ገልፀዋል። በኦሮሚያ ክልል በሐር ልማት ለአንድ ሺ340 ወጣቶች የሥራ እድል እንደተፈጠረላቸውም አስታውቀዋል።

የልማቱ ተሳታፊዎች የቁጠባ ባሕልንና ራስን የመቻል ልምድ እንዲያዳብሩም ሥልጠና እንዲያገኙ መደረጉን የገለጹት አቶ ተሾመ፤ ወደ ልማቱ ከመግባታቸው በፊት የሥልጠና ክህሎት ሲሰጣቸው ከሚያገኙት የውሎ አበል ላይ እንዲቆጥቡ በማድረግ ጭምር የቁጠባን አስፈላጊነት ተገንዝበው አሁን ላይ ከልማት ሽያጭ የሚያገኙትን ገቢ እንዲቆጥቡ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን አመልክተዋል።

በዚህ የልማት ሥራ ውስጥ ስኬቶች እንዳሉ ሁሉ ተግዳሮቶችም ስለማይጠፉ የነበሩትን ክፍተቶችም አቶ ተሾመ ጠቁመዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ የሐር ልማት ለብዙዎች አዲስና አንድ የግብርና አካል አድርጎ አለማየት በመኖሩ ፈጥኖ ተቀባይነት ለማግኘት በጅምሩ ላይ ችግር ሆኖ ነበር። በሂደት ሲለመድ ግን እየቀነሰ ይሄዳል።

በተለይ ደግሞ የሐር ትል ቅዝቃዜ የማይችል በመሆኑ ፈታኝ ስለሚሆን ተስፋ መቁረጥ ያጋጥማል። ጥቅሙን እያዩ ከሄዱ በኋላ ግን ትሎቹን ቤታቸው ውስጥ በማድረግ ጭምር ችግሮችን ለመቋቋም ጥረት ያደረጉባቸው አጋጣሚዎች አሉ። ጊዜ ውስዶ ለመሥራት ትዕግሥት አለመኖርና ቶሎ ትርፋማ ለመሆን የመፈለግ ሁኔታዎችን ያጋጥማሉ።

መልካሳ ምርምር ማዕከል በሐር ልማቱ ላይ እያደረገ ስላለው እገዛም አቶ ተሾመ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ለሐር የሚሆነውን ትል እንቁላልና የተሻሻለ ዝርያ ያላቸውን በማቅረብ፣ ተመራማሪዎችም ሥራውን በመከታተልና ምርምር በማደረግ፣ለሥራው የሚያስፈልጉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅ እያገዘ ይገኛል። በተለይም ከሐር የሚሠራ አልባሳት በዓለም ገበያ ተፈላጊና በዋጋም ውድ እንደሆኑ ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት። በመሆኑም ልማቱ ተጠናክሮ ቢከናወን በልማቱ የሚሳተፉትን ይበልጥ ተጠቃሚ ከማድረግ በተጨማሪ ለሀገር የውጭ ምንዛሪ ግኝት ከፍተኛ ፋይዳ ይኖረዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት ለሰብዓዊነት

**ጽጌረዳ ጫንያለው**




እንደ ሀገር ያለው የተማሪዎች ሥነምግባር ጉዳይ አደጋ ውስጥ እንደገባ የምንመለከትበት ብዙ ማሳያ አለ። ለአብነት ሰዎችን ማክበር፣ኃላፊነት መውሰድ፤ ሀገርን መውደድና ለሀገር ብሎ መሥራት፤ ራስን ለመለወጥ መሞከር ላይ ያለንበት ደረጃ እጅግ የወረደ ነው። አንዳንዴ እነዚህ ነገሮች የሉም ሊያስብሉን የሚችሉ ነገሮችም ያጋጥሙናል። ምክንያቱ ታዲያ ምንድነው ከተባለ ባሕልን፣ ወግንና የሥራ ልምድን የሚሸረሽሩ ነገሮች መብዛታቸው ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ የትምህርት ሥርዓቱ ሥነምግባር ላይ በተጨባጭ አለመሥራቱ መሠረቱ የተበላሸ ትውልድ እንዲፈጠር አድርጓል።

መምህርና ተማሪው ተገፋፍቶ እንጂ ተከባብሮ እንደማይጓዝ ሲታይ ሀይ የሚል መጥፋቱ፣ ያልሠራውን ውጤት ካልሰጠኸኝ ብሎ ሲሳደብና ሲማታ ዝም መባሉ፤ወላጁም ቢሆን ለምን ልጄን ትመታለህ በሚል የሚጋጭበት ሁኔታ ዜጋውን መብቱን እንጂ ግዴታውን እንዳያውቅም አበረታቶታል። በሀገር ደረጃ ለእኔ ብቻ የሚል ዜጋን ፈጥሯል። ሀገሩን ትቶ የሌላ ሀገርን የሚናፍቅም ትውልድ እንዲበራከትም አድርጓል።

እና ምን ይሁን ከተባለ ይህንን የሚያስተካክል ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። ይህም በትምህርቱ ዘርፍ መሥራት ሲሆን፤ ትምህርት ሚኒስቴርና ይህ የሚመለከታቸው ተቋማት በመቀናጀት የተለያዩ ሥራዎችን ለማከናወን እየጣሩ እንደሆነ ከሰሞኑ የሰማነው ነገር ያረጋግጣል። በእርግጥ ከዚህም በፊት ትምህርት ሚኒስቴር ሥነምግባርን ሊያሻሽሉ የሚችሉ ትምህርቶችን በመቅረጽ ወደ ሥራ አስገብቷል። ሆኖም ትምህርቱ እውቀት ከማስጨበጥ ይልቅ ውጤት (ማርክ) ላይ ያተኮረ በመሆኑ የተማሪዎችን ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም። እንደውም ከግዴታ ይልቅ መብትን ብቻ የሚያረጋግጥ ሆኖባቸው ብዙዎች ወደአልተፈለገ መስመር እንዲገቡ መርቷቸዋል። እናም የትምህርቱ ችግር በአግባቡ እንዲፈተሽና በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ሌሎች ትምህርቶች እንዲቀየሱ አስችሏል።

እነዚህ ትምህርቶች የስነ ዜጋ ትምህርት የሚለው የዜግነት በሚል ተቀይሮ የሚይዘው ይዘትም ተለይቶ እንዲገባ ሆኗል። በተመሳሳይ የግብረገብነት ትምህርትም እንዲሁ በትምህርት ደረጃ ተካቶ እንዲሰጥ ተደርጓል። አሁን ደግሞ የሰብዓዊነት ትምህርት በእነዚህ ትምህርቶች ውስጥ ተካቶ እንዲሰጥ ከሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ጋር መፈራረም ተችሏል። እነዚህ ትምህርቶች መልካም ስነምግባርን ከመፍጠርም በላይ የነበሩ መልካም ወግና ባህሎቻችንን በማስቀጠል በኩል የማይተካ ሚና እንደሚኖራቸው በወቅቱ የሁለቱ ተቋማት ኃላፊዎች ሲናገሩ ነበር።

እውቀት ያለሥነምግባር ስኬታማ እንደማይሆን ተረድቶ ስነምግባርን ለማሻሻል የሚሠሩ ተግባራትን ማስፋት ከምንም በላይ እንደሚያስፈልግም መስማማት ላይ ተደርሶበታል። የትናንቱ ይብቃን በማለትም በቀለም ትምህርትነት ብቻ ሳይሆን በሕይወት እንዲኖሩት ለማድረግም እንሠራለን ነው የተባለው። ምክንያቱም ባለፉት ጊዜያት ይሰጥ የነበረውን የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ከለውጥ ይልቅ ነውጠኛ ተማሪ እንደፈጠረ በሚገባ ታይቷል። ስለሆነም የሥነምግባር ትምህርቱ ለተግባራዊ ለውጥ እንዲሆን የቁጥር ውጤት ከመሆኑ ባለፈ መሠራት እንዳለበትም ታምኖበታል።

ትምህርት ከቀለሙ ሻገር ብሎ የለውጥ መሠረት መሆን እንዳለበት የገለጹት የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ፤ ተግባር የለውጥ ምንጭ ነው። በተግባር የተደገፈ ትምህርት በስፋት ባለመሰጠቱ የተነሳ ብዙ ነገሮች እንደሀገር ችግር ሆነው አልፈዋል። ለዚህም ማሳያው የዘንድሮው የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ውጤት ነው። በሕይወትም በሥራም የሚለውጥ ነገር በተማሪዎቹ ላይ አልተሠራም። ለዚህ ደግሞ ተጠያቂው ሁሉም ሰው ነው። እንደሀገር የወደቅንበትም ስለሆነ ሁሉም ማስተካከልና ለለውጡ መሥራት አለበት። የሥነምግባር ትምህርት ደግሞ ለዚህ ችግራችን የመጀመሪያው መፍትሔ ይሆነናል ይላሉ።

የባሕሪይ ለውጥ ትምህርት ሰዎች መሠረታዊ የሥነ ምግባር እሴቶችን (መርሆዎችን) እንዲረዱ፤እንዲጠብቁና እንዲኖሩበት ያደርጋል። በዚህም በዕቅድ ተመርቶ የጠቅላላ ባሕሪይ ለውጥ ትምህርት ሆኖ በትምህርት ቤቶች የመልካም ሥነምግባር ማጎልበቻ ማዕከል ይሆናል። እንዴት ከተባለ ደግሞ የባሕሪይ ለውጥ ትምህርት በትምህርት ሥርዓተ ውስጥ ተካቶ መሰጠት ሲችል ነው። እናም የሥነ ምግባር ጉዳዮችን በመፈተሽ መልካም ባሕሪይን ማጎልበት ያስፈልጋል። በአዲሱ የሥርዓተ ትምህርት ሂደትም ይህ እየተደረገ እንደሆነም ያነሳሉ።

በመግባቢያ ስምምነቱ መሠረት ሁለቱም ተቋማት ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው የሥራ ድርሻ እንዳለ ያነሱት ፕሮፌሰር ብርሃኑ ፤ የትምህርት ሚኒስቴር የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትን አመቺ በሆኑ የትምህርት ዓይነቶች በተለይም በግብረ-ገብና በዜግነት ትምህርቶች በግልፅ እና ትርጉም ባለው ደረጃ መካተታቸውን ለማረጋገጥና በተጓዳኝ የትምህርት ዘርፎች እንዲሰጥ ማድረጉ ላይ እንደሚሠራ አስረድተዋል።

በተጨማሪም በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ሥራ ላይ ያሉ ሥርዓተ ትምህርቶችና የሥልጠና መጻሕፍት ይዘት በተሟላ መንገድ የሰብዓዊ መብቶችን ፅንሰ ሃሳብና መርሆችን እውቀት የሚያስጨብጥ መሆኑን ለማረጋገጥ እና በየዓመቱ ኮሚሽኑ የሚያካሂደውን ሀገር አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ምስለ ፍርድ ቤት (moot court) ውድድር በተመለከተ አስፈላጊውን ትብብር ለማድረግ እንደሚሠራ አረጋግጠዋል።

ሰላም ሊመጣ የሚችለው ሰብዓዊ መብቶች ሲከበሩ ነው። ለዚህም መብትና ግዴታውን መለየት የሚችል ማኅበረሰብ መፍጠር ይገባል። ይህንን ማድረግ የሚቻለው ደግሞ በተማሪዎች በኩል ሲሆን፤ ተማሪዎች የሰብዓዊ መብት ትምህርቶችን እውቀት ኑሮ እንዲያደርጉት መሥራት ያስፈልጋል። ስለሆነም በመንግሥት ደረጃ ይህንን ለማድረግ እንደ ትምህርት ሚኒስቴር ያላሰለሰ ተግባር ይከናወናልም ነው ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ።

የሰብዓዊ ትምህርት ተማሪዎች፤ መምህራን፤ ሠራተኞች፤ ወላጆችና መላው ኅብረተሰብ የሚሳተፍበት አዎንታዊ ከባቢን የሚፈጥር ትምህርት ነው። ቅሬታዎችን በፍትሐዊነት ለመፍታት የሚያስችል፤ ከሁከትና ከማንኛውም የፀጥታ ችግር ነጻ የሆነ የመማር ማስተማር ሥራን የሚፈጥር፤ ሰላም የሰፈነበት አካባቢን ብቻ ሳይሆን መንደርን ጭምር ለመፍጠር እድል የሚሰጥ ነው። ከዚያም ባሻገር ተማሪዎች በዚህ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ ማለፋቸው ለትልቅ ዓላማ መዘጋጀት እንዲችሉ፤ ሰውንም ሆነ ሀገር ወዳድ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለሰው ደራሽነትን እንዲያዳብሩ ያደርጋቸዋል ያሉት ደግሞ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽኑ ዶክተር ዳንኤል በቀለ ናቸው።

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን በዋናነት ከትምህርቱ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤ ለሰብዓዊ መብቶች ትምህርት ማስተማሪያ የሚሆኑ፣ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች የሚያገለግሉ የተለያዩ ደጋፊ ጽሑፎች የሚገኙበትን የመረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) ያዘጋጃል። ትምህርት ቤቶች በመደበኛውና በተጓዳኝ ሥርዓተ ትምህርቶች ሰብዓዊ መብቶችን በማስረፅ የዕለት ተዕለት የትምህርት ሂደቱ አካል አድርገው የሚሠሩ እንዲሆኑ ለመደገፍ ይሠራል። በየዓመቱ የሚካሂደውን ሀገር አቀፍ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ምስለ ፍርድ ቤት ውድድር አጠናክሮ እንደሚቀጥልም በስምምነቱ ወቅት ያሉት ሀሳብ ነበር።

የሰብዓዊ ትምህርቱ ዋነኛ ዓላማ የሰብዓዊ መብት እሴቶችና መርሆችን ተገንዝቦ በእለት ተለት ግንኙነቱና በባሕርይው የሚያንፀባርቅ ትውልድ መፍጠር፤ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብን በመከባበር፣ በመቻቻልና በመግባባት አንድ ደረጃ ከፍ ማድረግ ነው። ለሰላምና አብሮ ለመኖርም ሁነኛ መንገድን መክፈት ነው። ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ላይ ጠንከር ያለ ሥራ አለመሥራት ሀገራችን ያለችበትን የሰብዓዊ መብቶች ፈተና ማባባስ ነው ያሉት ዋና ኮሚሽነሩ፤ በሀገራችን ያለው መጠነ ሰፊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበረሰባዊ ቀውስ የሚታከመው በእነዚህ ሥራዎች እንደሆነ ይገልጻሉ። የሰብዓዊ መብት ፈተናን ለማለፍ ትውልዱን በዚህ ትምህርት ማነጽና በሕይወቱ እንዲኖረው ማድረግ እንደሚያስፈልግም አበክረው ይናገራሉ።

ትምህርቱ በቅርቡ ወደ ሥራ የሚገባና ሥራው መጠነ ሰፊ ተግባርን የሚጠቅም በአጭር ጊዜ ለውጡን ማየት የማይቻልበት ቢሆንም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠሩ ሥራዎች የዚህ ዓይነት ፀባይ ያላቸውና የረጅም ጊዜ ራዕይ የሚጠይቁ ናቸው ጅማሮው እውን እንደሚሆንም እምነት አላቸው።

ክብር ያለው፣ኃላፊነት የሚሰማው ዜጋን ለመፍጠር ሁነኛው መፍትሔ ተማሪዎችን ከታች ጀምሮ በሰብዓዊ ትምህርት ዙሪያ ቀርጾ ማሳደግ ሲቻል እንደሆነ የሚያነሱት ደግሞ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሰብዓዊ ትምህርት ክፍል ዳይሬክተር ዶክተር መቅደስ ታደለ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ ኃላፊነት ለራስ ባሕርይ ተጠያቂ በመሆን ታማኝነትን ማረጋገጥ አለበት። ይህ ደግሞ በቃልም በተግባርም ይተረጎማል። ስለዚህም በትምህርታቸው ውስጥ ለሌሎች ደህንነት መቆርቆርን፤ ፍትሐዊነትና ያለ አድሎ ማገልገልን እየተማሩት ብቻ ሳይሆን እየኖሩት እንዲሄዱ ይደረጋል። ይህ ደግሞ ኃላፊነት የሚሰማውና ደፋር ያደርጋቸዋል። ሕሊናቸውን ተከትለው የሚሠሩ ልጆችም እንዲሆኑ ዕድል ይሰጣቸዋል።

በተማሩት ትምህርት ለችግሮች ትክክለኛ መፍትሔ ሰጪ፣ፅናትንየተላበሱናተስፈኛእንዲሆኑምያስችላቸዋል። እንደ ሀገርም ቢሆን የራሱን መብት አስከብሮ የሌላውን መብት አክባሪ ዜጋ እንዲበራከት የሚያደርግ ነው። መብትና ግዴታውን ጠንቅቆ የሚያውቅ ዜጋን በስፋት እናገኝበታለን። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በቀላሉ ሁሉም ዜጎች ጋር መድረስ ያስፈልጋል። ለዚህ ዋናው መንገድ ትምህርት ነው። ከተማሪዎች እስከ መምህራን ከቤተሰብ እስከ ጎረቤት ድረስ መድረስ ይቻላል። የማኅበረሰቡን አዕምሮ በመቀየር በኩልም ሚናው ከፍ ያለ ነው።

ስምምነቱ የሰብዓዊ መብቶች እሴቶችን ወደ ማኅበረሰቡ ከማስረፅ አኳያ ትልቅ ሚና ይኖረዋል። ተደራሽነትን በመጨመር ረገድም በኢትዮጵያ ዘላቂና ውጤታማ በሆነ መንገድ የሰብዓዊ መብቶች ባሕልን ለማስፈን ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው። በተለይም ተማሪዎች ስለእኩልነት፣ ሰብዓዊ ክብር፣ ፍትሐዊነት፣ ሰላም፣ መከባበርና ኃላፊነትን መውሰድ እንዲሁም በእውቀት የዳበረ ልምድ ለማግኘት ብዙ አማራጮችን እንዲያዩና እንዲያገኙ ያስችላቸዋል። የሰብዓዊ መብቶች እሴቶች መገለጫ የሆኑ የባሕርይና የአመለካከት ለውጦችን እንዲያመጡም ያደርጋቸዋል ይላሉ ዶክተር መቅደስ።

የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና መግለጫ እንዳስቀመጠው፤ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ስልጠና በሁሉም የእድሜ ክልል ያሉ ሰዎችን የሚመለከት ሲሆን የእድሜ ልክ ሂደትም ነው። ስለዚህም ከመዋዕለ ሕፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ ባሉ የትምህርት ደረጃዎች ለሁሉም የማኅበረሰብ ክፍሎች መድረስ አለበት።

በሁለቱ ተቋማት መካከል የተደረገው ይህ የሰብዓዊ ትምህርት የመስጠት ስምምነት በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት ሥርዓቶች ውስጥ ተካቶ የሚሰጥ ነው። በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ እንዲጠናከርና እንዲስፋፉም ይደረጋል። የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት በተጓዳኝ የትምህርት መንገዶች በተለይም በክበቦች እና በሌሎች የማስተማሪያ ማዕቀፎች ውስጥ በማካተት ለተማሪዎች የሚደርስም ነው። በተጨማሪ ከሌሎች መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመተባበር መሥራት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን እንደያዘ በስምምነቱ ወቅት የተገለጸ ሲሆን፤ ቃል በተግባር ይዋል በማለት ለዛሬ የያዝነውን ሀሳብ አበቃን።

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ለማምረት የሚያስችል ሰፊ አቅምና ምቹ ሁኔታ ያላት አገር ናት››



ፎቶ፡-ገባቦ ገብሬ

*ዶክተር መሰለ መኮንን*

**የእርሻ ልማትና ሆርቲካልቸር ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ**

**አስቴር ኤልያስ**

የሆርቲካልቸር ዘርፍ በተፈለገው መጠን እና በጥራት የሚመረት ከሆነ አንደ አገር ለውጭ ገበያ በመቅረብ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝ ዋንኛ ምርት ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ለዜጎች የሥራ እድልን በመፍጠር ረገድ የሚጫወተው ሚና ላቅ ያለ መሆኑ አያጠያይቅም። በተለይ አትክልትና ፍራፍሬ ለአገር ውስጥ ገበያ በማቅረብ ተጠቃሚ ከማድረጉ በተጨማሪ እንደቤተሰብ ለምግብ ዋስትና መረጋገጥም ያለው ፋይዳ ከፍ ያለ ነው። ከዚህ ከሆርቲካልቸር ዘርፍ ጋር በተያያዘ እየተሠራ ያለው ሥራ እና እያስገኘ ያለው ውጤት ምን ይመስላል ሲል አዲስ ዘመን በግብርና ሚኒስቴር የእርሻ ልማትና ሆርቲካልቸር ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ከሆኑት ዶክተር መለሰ መኮንን ጋር ያካሔደውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ለአበባ፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ ያላት ምቹነት እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር መሰሰ፡-** አገራችን በተፈጥሮ ሀብት የታደለች ናት። ይህን ስንል ግን እንዲሁ ስለምንወዳት ብቻ ለማለት ሳይሆን እውነት ስለሆነ ነው። ለዚህ ምክንያቱ አንደኛ በሥነ ምሕዳር (በአግሮ ኢኮሎጂው) ብንወስድ ሁሉንም ዓይነት ሥነ ምሕዳር ያላት ሀገር ናት። በጣም ውርጭ ከሚባለው እስከ በረሃማ የአየር ዓይነት በዚህች አገር ላይ አለ። ይህ ማለት ሀገራችን ውስጥ የማይበቅል የሰብል ዓይነት የለም እንደማለት ነው። ምክንያቱም ለሁሉም ዓይነት ሰብል ምቹ ናትና።

ሁለተኛው ደግሞ ኢትዮጵያ ገና በጣም ሰፊ የሆነና ያልታረሰ ለም መሬት ባለቤት ናት። እየተጠቀምን ያለነው በአብዛኛው ደጋማ፣ ወይናደጋ እና በተወሰኑ ቆላማ በሆኑ አካባቢዎች ያለውን መሬት ብቻ ነው። በአብዛኛው እየተጠቀምን ያለነው ሰው የሰፈረበትን አካባቢ ነው። ወረድ ብሎ ለእርሻ ሥራ ምቹ የሆኑ በጣም ሰፋፊ አካባቢዎች ቢኖሩም እሱ ግን ከዓመት ዓመት ሳይታረስ እንዲሁ ጦሙን የሚያድር መሬት ነው።

በሰሜን ምዕራቡም ብንወስድ ሰፊ ያልተነካ መሬት አለ። ወደ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እንዲሁም ወደጋምቤላም መስመር ብንወስድ ሰፊ ያልተነካ መሬት አለን። ኦሮሚያ፣ አፋር እንዲሁም ሶማሌ ላይ ሰፊ ያልተነካና ለም የሆነ መሬት በተመሳሳይ አለን። ለዚህም ነው ሀገራችን በተፈጥሮ ሀብት የታደለችና ምቹ ናት የምንለው። በውሃ ሀብትም በኩል የገጸ ምድር እንዲሁም የገጸ ምድር ውሃ ከየትኛውም አካባቢ የተሻለ ያለን ነን። ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች አሉን። በበጋውም ሆነ በክረምቱ ወቅት በቂ የሆነ የከርሰ ምድር ውሃ አቅም ያላት አገር ናት። ከዚህ የተነሳ ትንንሽ ጉድጓዶች በመቆፈር ብቻ በመስኖ ማልማት የሚያስችል አቅም አለ።

ለምሳሌ ምሥራቅ አማራን ብንወስድ ከአላማጣ ጀምሮ እስከ ሸዋ ሮቢት ድረስ ያለው አካባቢ 50 ሺ ሔክታር አካባቢ መሬት በከርሰ ምድር ውሃ ብቻ መልማት የሚችል ነው። ጉድጓዶች ተቆፍረው ውሃው ወጥቶ የተወሰኑት እየለሙም ይገኛሉ። ስለዚህ ይህ አቅም አለ። ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ በርካታ ወንዞች ስላሉ መስኖ ላይ መሥራት ብንችል ለሆርቲካልቸር ሰብል መስኖ ልማት እጅግ በጣም ምቹ ነው። ስለዚህም ያልተነካ አቅም አለን ማለት ይቻላል። ትግራይን ብንወስድ በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ ይህ አቅም አለ። በኦሮሚያ ክልል አሁንም በመልማት ላይ ያለ ምርት አለ። አፋርም ብሎም ሶማሌ እንዲሁ በርካታ ለአዝርዕትም ለጥጥም ለሆርቲካልቸርም ምቹ የሆኑ አካባቢዎች አሉ። ከዚህ ጎን ለጎን እየለሙም ያሉ አካባቢዎች አሉ። ኢትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ለማምረት የሚያስችል ሰፊ አቅምና ምቹ ሁኔታ ያላት አገር ናት ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- እንደአገር ይህን ያህል ያልታረሰ መሬት እንዲሁም በቂ ውሃ እያለ የተፈለገውን ያህል ማልማት ያልተቻለው ለምንድን ነው?**

**ዶክተር መሰለ፡-** ይህ ሀብት እያለን ማልማት ያልቻልንበት አንዱ ምክንያት እስከ ዛሬ ድረስ ያለን የእርሻ እንቅስቃሴያችን እጅግ ኋላ ቀር በመሆኑ ነው። የተለመደው ከእጅ ወደአፍ ማምረት ነው። አምርቶ ለራስ ከመመገብ ባለፈ ገበያንም ሆነ ሌላውን መሠረት ያደረገ ነገር ላይ ያለንን አቅም አሟጥጦ በመጠቀሙ ረገድ የነበርንበት ሁኔታ እጅግ ኋላቀር ነው። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በልምድም በክህሎትም በተለይ ዘመናዊ የሆነ የሆርቲካልቸር ልምዳችን የአጭር ጊዜ ታሪክ ነው። ስለዚህም የእሱ ልምድ አለመኖር ነው።

አሁን አርሶ አደሮቻችን በየጊዜው ልምዱን እያገኙ ሲመጡ በአዝርዕቱ ወይም በሆርቲካቸርና ፍራፍሬ ሰብል እያሰፉ መምጣት ጀምረዋል። በተለይ ደግሞ ከውጭ በተለያዩ ተልዕኮ የሚመጡ አውሮፓውያኑም ሆኑ ሌሎች የውጭ ዜጎች ብዙ በሰፈሩባቸው አካባቢዎች አትክልትና ፍራፍሬ ማልማት ላይ እያስተማሩ ስለሆነ በርካታ ፍራፍሬዎችን በማልማት ረገድ የማይናቅ ሥራ ሠርተዋል፤ ከዚህ አንጻር ሲታይ ለምሳሌ ደቡብ የተሻለ አቅም ያለው ክልል ነው። ኦሮሚያ ደግሞ የተሻለ ልምድ ያለበት ክልል ነው። ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ደግሞ አማራ ክልል ወደማልማቱ ሥራ እየተቀላቀለ ይገኛል።

በሆርቲካልቸርም አርሶ አደሩ ከሚሠራው ውጪ እምብዛም የተሠማራ ባለሀብት አልነበረም። አሁን አሁን ግን የሀገር ውስጥም የውጭም ባለሀብት በአትክልትም ሆነ በፍራፍሬ ላይ ሰፊ ሥራ እየሠሩ ይገኛሉ። ቀደም ብሎ በነበረው ላይ አትክልትና ፍራፍሬ የሚያመርተው አካል ለራሱ ከመጠቀም በዘለለ ለገበያ የማቅረቡ ሁኔታና ገቢ የማግኘቱ ነገር ብዙ አልነበረም።

አሁን ግን ከጊዜ ወደጊዜ አንደኛ ለአገር ውስጥ ገበያም ማቅረብና የተሻለ ጥቅም ማግኘት ተጀምሯል። በተወሰኑ የፍራፍሬና የአትክልት ዓይነቶች ደግሞ ወደውጭ መላክ የተጀመረበት እድል ስላለ በአሁኑ ወቅት እየሰፋ በመምጣት ላይ ይገኛል። መንግሥት ይህን በማየት ሌሎች ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠረ ነው። ለምሳሌ አግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎችን መውሰድ ይቻላል። ቲማቲም በሰፊው ቢለማ ከፍጆታ አልፎ መቀመጥ አይችልም፤ በቀላሉ መበላሸት የሚችል ምርት ነው። ስለዚህ ቲማቲምን እሴት በመጨመር የሚያመርቱ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች እንዲኖሩ ማድረግ ያስፈልጋል። የሚመረተውን አቮካዶ ሁሉ ለፍጆታችን ተጠቅመን አንችልም፤ የድንች ምርትም ቢሆን በሰፊው ተመርቶ የተወሰነ ጊዜ ተጠቅመን ከዛ በኋላ የመበስበስ እድሉ ከፍተኛ ይሆናል። ስለዚህ አቮካዶንም ሆነ ድንች እሴት የሚጨምር (ፕሮሰስ የሚያደርግ) የአግሮ ፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም። ስለዚህ የአትክልትና ፍራፍሬ ዋናው ነገር ድኅረ ምርት አያያዝ ነው ማለት ነው፤ ለምሳሌ ድንችን በጥብስ (ቺፕስ) መልኩ መጠቀም መጀመራችን የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ነው። በዚህ መልኩ እውቀቱም ክህሎቱም በፊት ያልነበረ ሲሆን፣ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መምጣት ጀምሯል። ምቹ ሁኔታዎች እየታዩ ሲመጡ የአካባቢውን ሀብትና ጸጋ እንዲሁም አቅም በማየት አርሶ አደሩ፣ በልማት የተሠማሩ ተቋማትም ሆኑ ባለሀብቶችም የማልማት ሥራው ላይ በመሳተፋቸውና ሥራውም ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ መልካም ጅማሮ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በዘርፉ በተለይ በአበባ ልማት ላይ የሚሠማሩ የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጭ አገር ኢንቨስተሮች እንዳሉ ይታወቃሉ፤ ምን ያህል ውጤታማ ሆነዋል?**

**ዶክተር መሰለ፡-** በጣም ውጤታማ ሥራ እየሠሩ ናቸው ማለት ይቻላል። ውጤታማ ናቸው ብለን ከምንጠቅሳቸው ውስጥ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው በአበባ ልማቱ ላይ እየሠሩ ያለውን ሥራ አንዱ ነው። ሥራው እጅግ በጣም በአጭር ጊዜ ውስጥ ጥሩ ውጤት ያሳየ ነው። ሰፊ ልማት ማልማት የተቻለ ሲሆን፣ ከዚህም ልማት አገራችን አበባ ወደ ውጭ በመላክ በተሻለ ሁኔታ የውጭ ምንዛሪ እያገኘች መምጣቷ ተጠቃሽ ነው።

እንደሚታወቀው ቀደም ሲል ወደውጭ አገር የምንልከው ቡናን ነው። ለብዙ ዓመታት በቡና ተወስነን ቆይተናል፤ በአሁኑ ወቅት ቡና እንዳለ ሆኖ አበባን ወደውጭ መላክና የውጭ ምንዛሪ ማግኘት ተችሏል፤ ይህ ብቻ ሳይሆን የአበባ ልማቱ በመምጣቱ ብቻ ከውጭ ምንዛሪ ጎን ለጎን ለበርካታ ወጣቶች የሥራ እድል መክፈት ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ በአበባ ልማት ዕውቀትንና ክህሎትን ማግኘት የተቻለ ሲሆን፣ ቀደም ሲል ይህ ዓይነቱ ልምድ በሀገራችን አልነበረም። ይህንንም ልማት ለማልማት የውጭ ኢንቨስተሮች ባለሙያዎችን ይጠቀሙ የነበረው ከውጪ አምጥተው ነው። አሁን ከጊዜ ወደጊዜ ግን የዕውቀት ሽግግሩ ኖሮ ብዙዎች የአበባ እርሻዎች በውጭ ይመሩ የነበሩ ዛሬ በእኛ ባለሙያዎች መመራትና የእኛ ባለሙያዎች እየተተኩ መምጣት ተችሏል። በዚህም የእውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግሩም እየመጣ ይገኛል።

በፍራፍሬም እንደዚሁ የተወሰኑ ለምሳሌ ከአውሮፓ የኔዘርላንድስ የግል ኩባንያዎች እርሻ በመውሰድም የአትክልት ዘር በማምረትም ወደ ውጭ በመላክ ላይ ይገኛሉ። ከዚያም በሀገራችን እየተካሄደ ባለው የአበባ ልማት የውጭ ምንዛሪው ብሎም የቴክኖሎጂ ሽግግሩም የማግኘት እድል ተፈጥሯል። ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በተለይ በፍራፍሬና በአትክልቱ ዘርፍ መሬት እየወሰዱ ኢንቨስት የማድረጉና የመነቃቃቱ ሥራ እየተሠራ ነው። ባለሀብቶቻችን ብሩን ይዘውታል እንጂ ዕውቀት እና ክህሎቱ አልነበራቸውም። አሁን ከጊዜ ወደጊዜ የእኛም ባለሙያዎች ከዩኒቨርስቲ የሚወጡትም ሆኑ ባለሀብቶቻችን ልምድ እያገኙ በመምጣት ላይ ይገኛሉ።

**አዲስ ዘመን፡- የአበባ ልማቱ በሌሎች አገሮች ተፈላጊነቱ እንዴት ይገለጻል? አንዳንድ አካላት በአንዳንድ ባለሀብቶች ግዴለሽነት የተነሳ የአበባ መሬት በኬሚካል እየተበከለ ነው ይላሉ፤ እዚህ ላይ ምን አስተያየት?**

**ዶክተር መሰለ፡-** አንድ ልማት ሲመጣ ጠቀሜታ እንዳለው ሁሉ በአግባቡ ካልተጠቀምንበት ደግሞ የራሱ የሆነ ጉዳት ይኖረዋል። የአበባ ልማት ወደሀገራችን መምጣቱ ሰፊ የገበያ እድል እንዲያገኝ አስችሎታል። የእኛ አበቦች በአውሮፓ ገበያ በቀላሉ መግባት የሚችሉና ተፈላጊ በመሆናቸው የገበያ ችግር የለብንም።

ይህን ልማት በምንሠራበትና በምናስፋፋት ጊዜ ደግሞ አካባቢን የመበከል ሁኔታ እንዳይኖር አንደኛ የሚጠቀሟቸው ኬሚካሎች ከጊዜ ወደጊዜ መሬቱን እንዳይበክሉት የሚከታተል የእኛ የግብርና ኳራንቲ (የግብርና ባለስልጣን) አለ። አሁን በተሻለ መልኩ እያደራጀነው ነው። የሚገቡት ኬሚካሎች ለአካባቢ፣ ለሰው እንዲሁም ለእንስሳት ተጽዕኖ እንዳይኖራቸው ለማድረግ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይደረጋል። ሌላው ቀርቶ የአበባ እርሻዎች በሚመሠረቱበት ጊዜ አካባቢን

# ወቅታዊ

እንዳይበክሉ ማሟላት ያለባቸው ሁኔታዎችና መስፈርቶች አሉ። ይህም ገና ሲሰጣቸው የአካባቢ ተጽዕኖና ግምገማ ተደርጎ ነው። በእርግጥ ይህ ሁሉ ይተገበራል ወይ ብለን ብንጠይቅ የምንሠራ ሰዎች እንደመሆናችን የተወሰኑ ድክመቶች እንዳሉ ማየት ችለናል። ቀደም ብሎ ባሉት ላይ የነበሩ ችግሮች በመቀረፍ ላይ ናቸው። አሁን አዳዲስ እየገቡ ባሉ የአበባ እርሻዎች ላይ እየተሠራ ያለው በተሻለ መጠን ሲሆን፣ በአካባቢው ላይ ምንም አይነት ተጽዕኖ እንዳይኖራቸው ተደርጎ ነው። ይህ የሆነውም ካለፉት እንቅስቃሴያችን የተወሰዱ ተሞክሮዎች በመኖራቸው ነው።

ያለፉትም ቢሆኑ የሚቻለውን የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደ እንዲያስተካክሉ ብሎም አካባቢን እንዳይጎዱ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። ከዚህም የተነሳ በአሁኑ ጊዜ ልማቱ የሚገኘው የተሻለ ደረጃ ላይ ነው። ይሁንና የሚቀረን ነገር ስላለ አሁንም ገና ነው። አንድ ጊዜ በአካባቢ ላይ ተጽዕኖ እንዳያደርሱ ሆነው ተሠርተዋል፤ ተመሥርተዋል ብንልም በየጊዜው ግን ቁጥጥርና ክትትል መደረግ መቻል አለበት። ስህተቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ ከስር ከስር ክትትል እየተደረገ መስተካከል አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- አትክልትና ፍራፍሬም የውጭ ገበያ በማቅረብ ለአገራችን የውጭ ምንዛሪ ማግኛ መንገድ እንደሆነ ይነገራል፤ ከዚህ ዘርፍ ዋንኞቹ የትኞቹ ናቸው ?**

**ዶክተር መሰለ፡-** አትክልትና ፍራፍሬ ላይ ስንመጣ ለሥርዓተ ምግብ ዋስትና በጣም ጠቃሚ ናቸው። ለሀገር ውስጥ ገበያ ደግሞ በጣም ወሳኝ ናቸው። ከዚህም አልፎ ወደውጭ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሪን የሚያስገኙ ናቸው። በዋናነት ግን ሀገር ውስጥ ላሉ አግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ለግብዓትነት የሚውሉ ናቸው።

ከአትክልት የተወሰኑትን ከፍራፍሬም የተወሰኑትን ለማንሳት ያህል ለምሳሌ የሀገር ውስጥ ገበያን ብሎም ግሽበትን በማረጋጋት በኩል እንዲሁም ለሥርዓተ ምግብ ዋስትናነት ከምንጠቀምበት አንዱ ሽንኩርት ነው፤ ሽንኩርት በጠፋ ቁጥር ምን ያህል ግሽበት ላይ አስተዋፅዖ እንዳለው ይታወቃል። ስለዚህ ሽንኩርት ለሀገር ውስጥ ፍጆታና ለሀገር ውስጥ ገበያ እጅግ ወሳኝ ነው።

ሌላው ውስጥ ፍጆታም ሆነ ለአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ግብዓት ከሚሆነው አንዱ ቲማቲም ነው። ቲማቲምን በሰፊው ማምረት ብንችል እዚሁ ሀገር ውስጥ በአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ፕሮሰስ ተደርጎ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ የሚቀርብበት እድል አለ። በሦስተኛነት ለመጨመር ያህል ድንችን ማንሳት ይቻላል፤ ድንች ለምግብ ዋስትና፣ ለሥርዓተ ምግብ ዋስትና እንዲሁም ለአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ በጣም ወሳኝ ነው። ስታርች ከድንች ይሠራል። ድንችን ፕሮሰስ አድርገው ስታርችን ከድንች የሚሠሩ የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች አሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ በርበሬም አንዱ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ ቅመማቅመም ብለን ከምናመርተው ውስጥ ነው። በርበሬ በቅመማቅመምነቱ ለሀገር ውስጥ ገበያ ብሎም ለውጭም ሀገር ገበያ መሆን የሚችል እድል ያለው ምርት ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ፍራፍሬ ዘንድ ስንመጣ ሙዝ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ ለመቅረብ ሰፊ አቅም ያለው ምርት ነው። በተመሳሳይ ማንጎም ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ ብሎም ለአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ መሆን የሚችል አቅም አለው። አሁን ደግሞ በቅርብ በጣም ትልቅ ሥራ እየሠራንበት ያለው አቮካዶ ነው፤ በአቮካዶ በኩል ለሀገር ውስጥ ለአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ የሚሆኑ የተለያዩ ዝርያዎች አሉን። በተጨማሪም ለውጭ ገበያ ብለን የምናመርታቸው አሉን። ላለፉት ሦስት ዓመታት ዘንድሮን ጨምሮ አቮካዶ ወደውጭ ገበያ በመላክ ላይ እንገኛለን። ከኦሮሚያ፣ ከአማራ አሁን ደግሞ ከደቡብ ክልል እያመረትን ነው። ከዚህ አኳያ አቮካዶ ትልቅ አቅም ያለው ምርት ነው ማለት ይቻላል። በፓፓያ ዙሪያም ትልቅ አቅም ያለን ሲሆን፣ በመመረት ላይ ነው። ይህን ሥራ በኩታ ገጠም በማድረግ በየጊዜው እያሰፋን ችግኞችም እየተዘጋጁ በየዓመቱ ሰፊ የተከላ ሥራ በመካሄድ ላይ ነው። ከዚህ አኳያ ሥራዎችም እየተሠሩ የሚገኙት በልዩ ጥንቃቄ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ አትክልቱም ሆኑ ፍራፍሬዎቹ በጥራት ተመርተው በአስተሻሸጋቸውም የገዥዎቻቸውን ቀልብ ስበው የመቅረባቸው ጉዳይ ላይ ምን ያህል ተመራጭ አድርጓቸዋል? ጥራቱን በማስጠበቁ በኩል ተግዳሮት ካለ ለመፍትሔው ምን እየተሠራ ነው?**



**ዶክተር መሰለ፡-** በአዝርዕትም በአትክልትና ፍራፍሬም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ስናይ የራሳቸው የሆነ ስታንዳርድ አላቸው። በዛ ስታንዳርድ መሠረት ካልሆኑ ከሄዱበት የውጭ አገር ገበያ ወዲያውኑ ይመለሳሉ፤ ከዛ በፊት ግን ወደውጭ ገበያ መጓዝ የሚችሉት እዚህ ጥራታቸው ታይቶና ተፈትሾ የተቀመጠውን ስታንዳርድ ያሟላሉ ተብሎ ሲረጋገጥ ነው። እኛ ባረጋገጥነው ብቻ ስለማይሆን ደግሞ ከዚህ ልከን እዛ በድጋሚ ይፈተሻሉ፤ በፍተሻቸው ወቅት እንከን የሚያገኙባቸው ከሆነ ይመልሱታል፤ መመለሱ ብቻም አይደለም። ለቀጣይ የሚኖረንን የውጭ ገበያ ሰንሰለታችንን የሚያበላሽ ይሆናል፤ ይህም የሚያበላሸው የሀገርን ገጽታ ነው፤ ስለዚህ ለምሳሌ አቮካዶን ወደ ውጭ ገበያ ስንልክ ከእርሻ ጀምሮ የምንከተለው የጥራት ሒደት አለ፤ ከዛፉ ቆርጠን የምናመጣበት የራሱ ቴክኒክ አለው። በዚህ ረገድ ሰፊ ስልጠና ይሰጣል፤ ምርቱን የምንቆርጥበት ሆነ ከዛፉ ቆርጠን የምናጓጉዝበት የራሱ መሣሪያ አለ። ምርቱ ቀዝቃዛ መጋዘን ከገባ በኋላ ደግሞ ምርቱን እንደየመጠኑ መለየት ደግሞ ሌላው ሥራ ነው። በመጠንና በደረጃም የመለየት ሥራ በጥንቃቄ ይካሄዳል። ለእነዚህ የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች አሉ። ማሽነሪዎቹ ምርቱን በመጠን በጥራት ደረጃ ይለዩታል። ይህ አካሄድ ዓለም አቀፍ ስታንዳርድን የተከተለ ነው።

የሚታሸጉበት እቃ በራሱ የራሱ ስታንዳርድ ያለው ነው። በአብዛኛው ለምርቶቹ የሚሆን ማሸጊያ እቃ እኛ አናመርትም። የሚመጣው ከውጭ ነው። ከካርቱን ጀምሮ የሚመጣው ከኬኒያና ከሌሎች አገሮች ነው። በዚህ መልኩ በቀዝቃዛ መጋዘን ውስጥ ሆኖ በቅብብሎሽ የሚጓጓዘው በቀዝቃዛ ተሽከርካሪ ውስጥ ነው።። በመርከብም ሆነ አውሮፕላን ለምርቱ ምቹ በሆነ የቅዝቃዜ ደረጃ ነው። ይህን የሚፈትሹና የሚያረጋግጡ ተቋማት ደግሞ አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በሆርቲ ካልቸር ዘርፍ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ በመቶኛ ሲሰላ ምን ያህል ነው ማለት ይቻላል?**

**ዶክተር መሰለ፡-** አጠቃላይ በግብርና ዘርፍ ማየት ከተቻለ በዚህ ዓመት ከ80 በመቶ ያላነሰውን የውጭ ምንዛሪ ድርሻ ያስገኘው ግብርና ነው። ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ትልቁን ድርሻ የሚይዙት ቡና፣ አበባ እና አትክልትና ፍራፍሬ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- በአትክልትና ፍራፍሬ በኩል በሰፋፊ እርሻዎች ላይ በሰፊው እንዲመረት በጠቅላይ ሚኒስትሩም በኩል ፍላጎቱ ከፍያለ ነው፤ ባለሀብቶችም ከዚህ አንጻር ሥራ እንደጀመሩ ይታወቃል፤ ይህ ምን ያህል ተስፋ ሰጪ ነው ተብሎ ይታሰባል?**

**የዛ የቤተሰብ ማዕድ በዓይነት፣ በመጠን እንዲሁም በይዘት የተሟላ ሆኖ ቤተሰቡን አጥግቦ ለሌላውም የሚተርፍ እንደ ሀገርም ይህን አሟልተን ለውጭ ገበያም እንድንተርፍ ነው። በሚደረገው ሒደት ሰዎች ወተት ላይ፣ እንቁላልና ዶሮ ላይ ወይም ማር ላይ ይመስላቸዋል። እሱ አንዱ ነው እንጂ በአትክልትና ፍራፍሬም በተመሳሳይ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት አለበት። በአዝርዕትም በተመሳሳይ ነው**

**ዶክተር መሰለ፡-** አትክልትና ፍራፍሬ በሀገር ውስጥ ገበያ ለምግብ ዋስትና እና ሥርዓተ ምግብና ዋስትና ካለው አስተዋፅዖ ትልቅ ድርሻ ያለው ነው፤ ከሚፈጥረው የሥራ እድል እንዲሁም ለአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት ከመሆኑ አኳያ አስተዋፅዖ ከፍ ያለ ነው። ብሎም ለውጭ ገበያ ተመራጭ እንደመሆኑ በአሁኑ ሰዓት የሀገር ውስጥም የውጭም ኢንቨስተሮችን ትኩረት ስቧል። በርካታ ወጣቶች ወደዘርፉ በመግባት ላይ ናቸው። በርካታ ወጣት ባለሀብቶችም ጭምር ዘርፉን በመቀላቀል ላይ ናቸው። ትልልቅ ባለሀብት ናቸው የምንላቸውም በዘርፉ ላይ እየሠሩ ነው።

ለዚህ ማሳያ ሌላ ቦታ መሄድ ሳይስፈልግ እዚሁ ምሥራቅ ሸዋ ላይ መቂ አካባቢን ብቻ ማየቱ በቂ ነው። በጣም በርካታ ወጣት ባለሀብት በዘርፉ ተሰማርቶ አትክልትና ፍራፍሬ እያለማ ይገኛል። ስለዚህ በጣም ተስፋ ሰጪና ሳቢ ዘርፍ ሆኗል። በመሆኑም በየዓመቱ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞች ቴክኒኩን ጠብቀው በመዘጋጀት ላይ ናቸው። ይህም በኩታ ገጠም እየሰፋ እየተሠራ የሚገኝ ነው። በአነስተኛ አርሶ አደሩም ደረጃ በኢንቬስተር ደረጃ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ባለሀብትም ሰፊ ፍላጎት እንደመኖሩ ሰፊ ሥራዎችም እየተሠሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የሆርቲካልቸር ዘርፍ ከሌማት ትሩፋት ፕሮጀክት ጋር ያለው ትስስር እንዴት ይገለጻል?**

**ዶክተር መሰለ፡-** ከሌማት ትሩፋት ጋር አያይዘሽ ያነሳሽው ጥያቄ ጥሩ አጋጣሚ ነው ብዬ አስባለሁ። ጥያቄውንም ስላነሳሽልኝ በጣም ደስ ብሎኛል። እንደ ሀገር ስትራቴጂክ ግቦች አሉን። በግብርና ሚኒስቴር አራት መሠረታዊ የሆኑ ግቦች አሉን። የመጀመሪያው ግብ በሀገር ደረጃና በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትና እና የሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ገቢ ምርትን መተካት እና ለአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆን ምርት በሀገር ውስጥ ማምረት ነው። ለውጭ ገበያ የሚሆኑ ምርቶችን አሊያም ሰብሎችን ማምረትና አይነታቸውንም መጠናቸውንም ማብዛት ነው። አራተኛው ግብና ዋንኛ የሆነው በገጠር ላሉ ወጣቶች እና ሴቶች የሥራ እድል ፈጠራ ነው። እነዚህን ግቦች ለማሳካት የአስር ዓመት ስትራቴጂክ ፕላን አለን፤ በርካታ አቅጣጫዎች አሉን። ከእነዚህም መካከል አንዱ በቅርቡ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይፋ የተደረገው የሌማት ትሩፋት ነው።

የሌማት ትሩፋት ማለት በአጭሩ በቤተሰብ ደረጃ ብሎም በአገር ደረጃ የምግብና የሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ማለት ነው። የምግብና የሥርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ማለት በአንድ ሌማት ወይም በአንድ ማዕድ ላይ በቤተሰብ ደረጃ የምንመገበው ምግብ በዓይነት፣ በመጠንና በይዘት የተመጣጠነ ይሁን ነው። ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ፕሮጀክቱን ያስጀመሩት ይህን መነሻ አድርገው ነው። ያ ማለት በአዝርዕት የሚመረቱ ምርቶች ያስፈልጉናል፤ በአትክልት እና ፍራፍሬ የሚመረቱ ምርቶች እንዲሁም በእንስሳት ተዋፅዖዎችም ያስፈልጉናል ማለት ነው። ስለዚህ እንጀራው፣ ዳቦው፣ ሽንኩርቱ፣ ሥጋው፣ ማሩም፣ ወተቱም ሆነ እንቁላሉ እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬው ያስፈልገናል።

የዛ የቤተሰብ ማዕድ በዓይነት፣ በመጠን እንዲሁም በይዘት የተሟላ ሆኖ ቤተሰቡን አጥግቦ ለሌላውም የሚተርፍ እንደ ሀገርም ይህን አሟልተን ለውጭ ገበያም እንድንተርፍ ነው። በሚደረገው ሒደት ሰዎች ወተት ላይ፣ እንቁላልና ዶሮ ላይ ወይም ማር ላይ ይመስላቸዋል። እሱ አንዱ ነው እንጂ በአትክልትና ፍራፍሬም በተመሳሳይ ትኩረት ተሰጥቶ መሠራት አለበት። በአዝርዕትም በተመሳሳይ ነው፤ እነዚህን ሁሉ ማድረግ ካልቻልን አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ ስለሚሆን የተሟላ ሌማት ወይም የተሟላ ማዕድ አይኖረንም። ስለዚህ ይህን አሟልተን መሥራት መቻል አለብን ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር መሰለ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## ሰሜን ኮሪያ አህጉር አቋራጭ ሚሳኤል አስወነጨፈች

ሰሜን ኮሪያ ባላንጣዎቿን ለማስጠንቀቅ ያሏትን አህጉር አቋራጭ ተወንጫፊ ሚሳኤሎች አስተማማኝነት ለመፈተሽ በሚል ድንገተኛ ሙከራ ቅዳሜ ዕለት ማድረጓን የአገሪቱ መገናኛ ብዙኃን ዘገቡ።

የተተኮሰው ሚሳኤል ለ67 ደቂቃዎች እና ከ900 ኪሎ ሜትሮች በላይ ከተጓዘ በኋላ ከጃፓን ባሕር ላይ ወድቋል።

ሙከራው ሰሜን ኮሪያ አሜሪካንን እና ደቡብ ኮሪያን የመሳሰሉ ጠላት ኃይሎችን ለመቋቋም የሚያስችል አቅም ሚሳኤሉ እንዳለው ያሳየ መሆኑን አገሪቱ ገልጻለች።

ይህ የሚሳኤል ሙከራ የተካሄደው ደቡብ ኮሪያ እና አሜሪካ፣ ከሰሜን ኮሪያ በኩል እየጨመረ የመጣውን የኑክሌር ስጋት ለመቋቋም በሚል በሚቀጥለው ወር ለማካሄድ ካቀዱት የጋራ ወታደራዊ ልምምድ ቀደም ብሎ ነው።

የሰሜን ኮሪያ ባለሥልጣናት እንዲህ ያለው ወታደራዊ ልምምድ ወረራ ለመፈጸም የሚደረግ ዝግጅት ነው ብለው እንደሚያስቡ እና ለዚህ የጦር እንቅስቃሴ ደግሞ "ታይቶ የማይታወቅ ጠንካራ" አጸፋን አገራቸው ትሰጣለች ብለዋል።


የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን እህት ኪም ኦ-ጆንግም ይህንን የአገራቸውን አቋም በማጠናከር፣ ማንኛውም በሰሜን ኮሪያ ላይ የሚፈጸም ጠብ ጫሪ ተግባር "ጠንካራና ግዙፍ" ምላሽ ይጠብቀዋል በማለት ቅዳሜ ጠዋት ተናግረው፣ አሜሪካ በአገራቸው ላይ የደቀነችውን "ስጋት" እንድታስወግድ አሳስበዋል።

ጨምረው ግን የደቡብ ኮሪያዋ ዋና ከተማ ሴውል የሰሜን ኮሪያ ሚሳኤሎች ኢላማ እንደማትሆን ገልጸዋል።

ባለፈው አርብ ሰሜን ኮሪያ በርካታ ቁጥር ያላቸውን አህጉር አቋራጭ ተወንጫፊ ሚሳኤሎች የተካተቱበት ወታደራዊ ኃይሏን የሚያሳይ ግዙፍ ትርኢት አቅርባ ነበር።

የቅዳሜ ዕለቱ የሚሳኤል ሙከራ ጃፓን የምጣኔ ሃብት ልዩ ቀጣና ብላ በምትጠራው አካባቢ መውደቁን የጃፓን ጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ ኪሺዳ አረጋግጠዋል።

እነዚህ የሰሜን ኮሪያ አህጉር አቋራጭ ሚሳኤሎች በሰሜን ኮሪያ ዙሪያ ካሉ አገራት ባሻገር ረጅም ርቀት በመጓዝ የአሜሪካ ግዛቶችን ጭምር የመምታት አቅም ስላላቸው አሳሳቢ ሆነዋል።



የጃፓን የመከላከያ ሚኒስትር ሃማዳ ያሱካዙ ሚሳኤሉ 14,000 ኪሎ ሜትሮች መጓዝ ስለሚችል በርቀት ላይ ያሉ አካባቢዎችን ሊመታ ይችላል ማለታቸውን የዘገበው ቢቢሲ ነው።

"ሰሜን ኮሪያ በተከታታይ እየፈጸመቻቸው ያሉ ተግባራት የጃፓንን እንዲሁም የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ሰላም እና መረጋጋት ስጋት ላይ የጣለ በመሆኑ ፈጽሞ ይቅር የሚባል አይደለም" ብለዋል የመከላከያ ሚኒስትሩ።

ይህንን የሰሜን ኮሪያን ድርጊት "ግድየለሽ ባህሪይ" በማለት ያወገዙት ደግሞ ጀርመን ውስጥ ስብሰባ ላይ የሚገኙት የቡድን ሰባት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ናቸው።

ባወጡት መግለጫ ላይም የሚሳኤል ሙከራው "አካባቢያዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሰላም እና ደኅንነትን" አደጋ ላይ የሚጥል በመሆኑ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት በሰሜን ኮሪያ ላይ ተጨማሪ ጠንካራ እርምጃ መውሰድ ያስፈልገዋል ብለዋል።

የደቡብ ኮሪያ ጦር እንዳመለከተው ሚሳኤሉ የተወነጨፈው ከዋና ከተማዋ ፒዮንግያንግ በስተ ሰሜን ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ ከሚገኝበት ሱናን ከተባለ ስፍራ ነው። በተጨማሪም ይህ ቦታ በቅርቡ የተደረጉ አህጉር አቋራጭ የሚሳኤል ሙከራዎች የተካሄዱበት መሆኑ ተገልጿል።

የሰሜን ኮሪያ የተወንጫፊ እና የኑክሌር ጦር መሳሪያ ፕሮግራሞች በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ዕገዳ የተጣለባቸው ቢሆንም፣ ይህ ግን ፒዮንግያንግ የጦር መሳሪያ ግንባታዋን ከመቀጠል እና ያላትን ወታደራዊ አቅም ለማሳየት ትርኢቶችን ከማካሄድ አላገዳትም።

ከሁለት ሳምንት በፊት የአገሪቱ መሪ ኪም ጆን-ኡን በታደሙበት ባልተለመደ ሁኔታ እኩለ ሌሊት ላይ በተካሄደ ወታደራዊ ትርኢት፣ ሰሜን ኮሪያ እስካሁን ከታዩት በበለጠ ያሏትን አህጉር አቋራጭ ተወንጫፊ ሚሳኤሎችን አሳይታለች።

## ማክሮን በሩሲያ ጉዳይ አነጋጋሪ አስተያየት ሰጡ



የፈረንሳዩ ፕሬዚዳንት ኢማኑኤል ማክሮን ሩሲያ በዩክሬን መሸነፍ እንዳለባት ቢያምኑም መጨፍለቋን ግን እንደማይፈልጉ ተናገሩ።

ፕሬዚዳንት ማክሮን ምዕራባውያን ሃገራት ለዩክሬን የሚያደርጉትን ወታደራዊ ድጋፍ እንዲጨምሩ አሳስበው ሃገራቸው ለተራዘመ ጦርነት መዘጋጀቷንም ለፈረንሳዩ ሚዲያ ገልጸዋል።

"ሩሲያ በዩክሬን እንድትሸነፍ እንዲሁም ዩክሬን ራሷን እንድትከላከል እፈልጋለሁ" ብለዋል። ነገር ግን ጦርነቱ ወደ ሩሲያ ተዛምቶ ሃገሪቱን መጨፍለቅ እና መደምሰስ ይገባል የሚሉ እሳቤዎችን ተቃውመዋል።

ፕሬዚዳንት ማክሮንን ጨምሮ በርካታ መሪዎች በሙኒክ የጸጥታ ጉባኤ ላይ ወደ ዩክሬን የሚደረገውን የጦር መሳሪያ አቅርቦትን ማፋጠን እንዲሁም በሞስኮ ላይ ጠንከር ያለ ማዕቀብም ለመጣል ቃል ገብተዋል።

"አንዳንዶች እንደሚያስቡት ሩሲያን በገዛ መሬቷ ላይ በማጥቃት ሙሉ በሙሉ መደምሰስ ወይም መጨፍለቅ አለብን የሚሉትን አላምንበትም" ሲሉ ማክሮን ለጆርናል ዱ ዲማንቼ ለተሰኘው የፈረንሳዩ ጋዜጣ ተናግረዋል።

"እነዚህ ታዛቢዎች ከሁሉም በላይ ሩሲያን የመጨፍለቅ ፍላጎት አላቸው። ይህ መቼም የፈረንሳይ አቋም ሆኖ አያውቅም፤ ለወደፊቱም ፍጹም አይሆንም" ማለታቸውም ሰፍሯል።

አርብ ዕለት በሙኒክ በነበረው ጉባኤ ላይ ንግግር ያደረጉት ፕሬዚዳንት ማክሮን፤ ከሞስኮ ጋር ለመወያየት ጊዜው አሁን አይደለም ሲሉም ተደምጠዋል። ሆኖም የሰላም ውይይትና፣ ድርድሮች የመጨረሻው ግብ መሆናቸውንም ከመጥቀስ ወደ ኋላ አላሉም።

ፕሬዚዳንቱ በምዕራባውያን አጋሮች የሚደገፉት የዩክሬን ወታደራዊ ጥረቶች "ሩሲያን ወደ ድርድር ጠረጴዛው ለመመለስ እና ዘላቂ ሰላም ለመገንባት" ብቸኛው መንገድ እንደሆነም ነው የጠቆሙት።

በሩሲያ ውስጥ የመንግሥት ለውጥ ማድረግ የሚለውን እሳቤ ያጣጣሉት ፕሬዚዳንት ማክሮን በዓለም ዙሪያ ተመሳሳይ ጥረቶች እንዳልተሳኩ አስታውሰዋል።

ምንም እንኳን ፕሬዚዳንት ማክሮን በውይይት ላይ በጎ አስተያየታቸውን ቢሰጡም ድርድር ለዩክሬን መሪዎች ሩቅ መሆኑ ተነግሯል።

አርብ ዕለት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዲሚትሮ ኩሌባ ሩሲያን ወደ ሙኒክ ላለመጋበዝ የተላለፈውን ውሳኔ በበጎ ተቀብለውታል።

ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ ከሩስያ አቻቸው ቭላድሚር ፑቲን ጋር ሊወያዩ እንደማይችሉ ገልጸው "በሃገራቱ መካከል መተማመን የለም" ሲሉ ማረጋገጣቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ ከቢቢሲ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ከሩሲያ ጋር የሰላም ስምምነት ላይ ለመድረስ የዩክሬንን ግዛት አሳልፎ መስጠት የሚለውን ሃሳብ ውድቅ አድርገዋል።

ፕሬዚዳንት ማክሮን ከዚህ ቀደም በዩክሬን ላይ በሰጡት የተለያዩ አስተያየቶች ከአንዳንድ የኔቶ አጋሮች ትችቶችን እንዲያስተናግዱ ምክንያት ሆኗል።

ባለፈው ዓመት ሩሲያ "በዩክሬን በፈጸመችው ወረራ መዋረድ (መሸማቀቅ) ሊሰማት አይገባም" ብለው ነበር።

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር**
**በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

# የቅድመ አንደኛ ትምህርት በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት

**በለጥሻቸው ልዑልሰገድ**

ልጆች የነገ የሀገር ተስፋ፤ ወደፊት የሚባለው የተስፋ ቃል የሚሰነቅባቸው ሀገርን ያለችበትን የእድገት ጉዞ ተረክበው ያስቀጥላሉ ተብለው ከግምት ውስጥ የሚገቡ ብርሃኖች ናቸው:: ታዲያ ይህንን የሀገር ተስፋነታቸውን እውን ለማድረግና የሚረከቧትን ሀገር በሙሉ ኃይላቸው የሚያገለግሏት ለማድረግ ከልጅነታቸው ጀምሮ በዕውቀት ተገንብተው ሊያድጉ ግድ ይላል:: ይህንን እውቀት ደግሞ በሥርዓት በተደራጀ የትምህርት ካሪኩለም በማስደገፍ ዕድሜያቸውን በሚመጥን መልኩ እንዲማሩ ሊደረግ ይገባል:: ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ትምህርት ሚኒስቴር የቅድመ መደበኛ ትምህርት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየሠራ ይገኛል::

ከዚህ ቀደም የነበረውን የትምህርት ሥርዓት ስንመለከት የቅድመ አንደኛ ትምህርት በነበረው አጠቃላይ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የተካተተ አልነበርም የሚሉት በትምህርት ሚኒስቴር የማኅበራዊ ሳይንስ ሥርዓተ ትምህርት ዴስክ ኃላፊ አቶ ዑመር ኢማም ናቸው:: ይህ የቅድመ አንደኛ ትምህርት ከዚህ በፊት በነበረው የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የቅድመ መደበኛ የትምህርት እርከን ስር የተመደበ ነበር:: መንግሥት መደበኛ የሆነውን የትምህርት እርከን፤ የመማሪያ ሥርዓተ ትምህርት ያዘጋጃል፣ የተዘጋጁ የትምህርት ቁሳቁሶችን በማሳተም ለተማሪዎች እንዲደርስ ያደርጋል፣ የተማሪ ድጎማ በጀትና ሌሎች የመማር ማስተማር ሂደቱን ሊያግዙ የሚችሉ ግብዓቶችን ያሟላል:: የቅድመ መደበኛ የትምህርት እርከን ግን በዚህ ሂደት ውስጥ የተካተተ አልነበረም::

ዜጎች የደረሱበት የትምህርት ፍላጎት እየጨመር በመጣ ቁጥር ወላጆች ልጆቻቸው መደበኛውን ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት የቅድመ መደበኛ ትምህርት



**አቶ ዑመር ኢማም**

እንዲማሩ ያላቸው ፍላጎት ከፍ አለ:: በተለይም በከተማ አካባቢ ፍላጎቱ እያደገ ሲመጣ የግል የትምህርት ተቋማት ይህንን እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ አድርገው በትኩረት ሲሠሩበት ነበር:: ያም በመሆኑ ወጥነት ያለው የትምህርት ሥርዓት ባለመኖሩ ትምህርት ሚኒስቴር ዓለም አቀፍ ሳይንስን ተከትሎ የቅድመ መደበኛ ትምህርት የመምህራን መመሪያ ሊሆን የሚችል አምስት ጭብጦች ላይ ያተኮረ የተቀናጀ መርሐ ግብር አዘጋጅቶ የቅድመ መደበኛ ትምህርት የመምህራን እየተማሩ ሊያስተምሩ የሚችሉበትን መመሪያ አዘጋጅተን በመስጠት ሲመሩበት ቆይተዋል በማለት ያስረዳሉ::

ኃላፊው እንደሚናገሩት፤ ቀደም ብሎ በነበረው የፍኖተ ካርታ ጥናት የዓለም አቀፍ ተሞክሮ የልጆች የብስለት ደረጃ ከአራት ዓመታቸው ጀምሮ ቢሆንም አምስትና ስድስት ዓመታቸው ላይ ግን ልጆች ያላቸው የትምህርት አቀባበል ለአጠቃላይ ትምህርቱ በጣም አጋዥ የሆነና የብስለት ደረጃቸውም ሊጨምር የሚችለው በዚያ ዕድሜ ላይ በመሆኑ በዚያ ደረጃ መማር የሚችሉትን ይዘት በመምረጥ መማር እንዳለባቸው ያሳያል:: ከዚህ በመነሳት ቅድመ መደበኛ ተብሎ ይጠራ የነበረው የትምህርት እርከን የመደበኛው አካል እንዲሆን ምክረ ሃሳብ ቀርቦ ወይይት ተደረገበት:: ሀሳቡ ጠቃሚና እውነትነት ያለው መሆኑ ታምኖበት ትምህርት ሚኒስቴር ባደረገው የትምህርት ሥርዓት ለውጥ ዕድሜያቸው አምስት ዓመትና ስድስት ዓመት የሆናቸው ሕፃናት የመደበኛው የትምህርት ሥርዓት አካል ተደርገው ከዚህ ቀደም የቅድመ መደበኛ ትምህርት በመባል የሚታወቀው የትምህርት እርከን ቅድመ አንደኛ የትምህርት እርከን እንዲሆን ተደርጎ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራበት ይገኛል::

ይህ ማለት ከዚህ በኋላ በሚኖረው የትምህርት ሥርዓት ቅድመ አንደኛ የትምህርት የአጠቃላይ ትምህርት አካል ተደርጓል ማለት ነው:: በመሆኑም መንግሥት እንደማንኛውም የትምህርት እርከን ተኩረት ተሰጥቶት በጀት ተመድቦለት የልጆች ማስተማሪያ ግብዓት እንዲዘጋጅ ተደርጎ፣ የመማሪያ መጽሐፍት ሕትመትና ስርጭት እንዲካሄድ ተደርጎ፣ በአሁኑ የትምህርት ለውጥ በስድስት አንኳር የመማሪያ ዐውዶች ራሱን የቻለ ለአምስት ዓመት እና ለስድስት ዓመት ልጆች ተብሎ የተከፋፈለ የተማሪ መማሪያ እና የመምርህራን ማስተማሪያ መፃህፍት ተዘጋጅተዋል:: በዚህ መሰረት በዚህ አመት ወደተግባር በመግባት የሙከራ ትግበራ እየተካሄደ ይገኛል፤ በቀጣይ አመት በሁሉም ክልሎች ሙሉ ለሙሉ ወደ ትግበራ ይገባል::

እንደሚታወቀው ከዚህ በፊት መንግሥት ለዘርፉ ትኩረት ባልሰጠበት ወቅት የግል ትምህርት ቤቶች በስፋት ይህንን አገልግሎት ሲሰጡ ነበር የሚሉት አቶ ዑመር፤ ከዚህ በኋላ በሚኖረው የትምህርት ሥርዓት መንግሥት ቅድመ አንደኛ የትምህርትን አንደኛው የአጠቃላይ ትምህርት እርከን ማድረጉ ከዚህ ቀደም የቅድመ አንደኛ ትምህርት ሲሰጡ የነበሩ የግል ትምህርት ቤቶችም ሆኑ ከዚህ በኋላ ይህ የትምህርት ሥርዓት ተግባራዊ የሚደረግባቸው ሁሉም የመንግሥት ትምህርት ቤቶች በእኩል ደረጃ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል:: በመንግሥት የሚወጡ የትምህርት ካሪኩለሞችን ሁሉም የትምህርት ተቋማት በተመሳሳይ መልኩ ተግባራዊ የሚያደርጉት ይሆናል:: ትምህርት ቤቶች የራሳቸው የማስተማሪያ መጽሐፍትን መጠቀም የማይፈቀድ ሲሆን ትምህርት ሚኒስቴር ለሁሉም ተመሳሳይና ወጥነት ያለው የማስተማሪያ መጽሐፍትን ያዘጋጀ በመሆኑ ሁሉም ትምህርት ቤቶች እነዚህን የመማሪያ መጽሐፍት ብቻ እንዲጠቀሙ ይደረጋል::

ወደፊት በሚኖረው አተገባበር፤ ለቅድመ አንደኛ ደረጃ በሚዘጋጁ የመማሪያ መጽሐፍት ላይ የተለየ ጭብጥ መጨመር አይቻልም:: የግል ትምህርት ቤቶችም የሚጠቀሙት ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች ጋር ተመሳሳይ መማሪያ መጽሐፍትን ነው:: ይህንን ከክልል የትምህርት ቢሮዎች እና ከትምህርት ጥራትና አግባብነት ምዘና ኤጀንሲዎች ጋር ተወያይተንበታል፤ እነሱም ከግል ትምህርት ቤቶች ጋር ውይይት አድርገው ስምምነት ላይ ተደርሷል በሚቀጥለው ዓመት በዚህ አሠራር ይቀጥላሉ:: የአጋዥ መጽሐፍትን በተመለከተ አሁን ባለንበት ደረጃ በዚህ የትምህርት እርከን ላይ የሚዘጋጁ የማስተማሪያና የመማሪያ መጽሐፍት የሚጎደላቸው ይዘት መኖሩ ተጠንቶ እስካልተረጋገጠ ድረስ ምንም አይነት የአጋዥ መጽሐፍት ታትመው ለገበያ አይቀርቡም በማለት ያብራራሉ::

# ስፖርት



# በዓለም አገር አቋራጭ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ ሁለተኛ ሆና አጠናቀቀች

ብርሃን ፈይሳ

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድን አዲሱን የውድድር ዓመት በሃገር አቋራጭ ውድድር ከዓለም ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ በድል ጀምሯል፡፡ በዕፅዋት የተከፋፈሉ መተላለፊያዎች፣ ረግረጋማ፣ ዳገታማ፣ ቁልቁለታማ፣ አቧራማ፣ ሜዳማ ስፍራዎች እንዲሁም በሰው ሠራሽ መሰናክሎች ፈታኝ በሆነው ሀገር አቋራጭ ውድድር የአትሌቶች ጽናት በእጅጉ ይፈተናል፡፡

ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች ባለፈው ቅዳሜ በተካሄደው ሻምፒዮና ግን በግል 1 የወርቅ፣ 3 የብር እና 1 የነሃስ ሜዳሊያ እንዲሁም በድብልቅ ሪሌ 1 የብር ሜዳሊያ አስመዝግበዋል፡፡ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በሚታወቁበት የቡድን ሥራም 1 የወርቅ እና 3 የብር ሜዳሊያዎች የተገኙ ሲሆን፤ በዚህ ውድድር በጥቅሉ 10 ሜዳሊያዎችን ማስመዝገብ ችለዋል፡፡ ይኸውም ኢትዮጵያ በውድድሩ ከተካፈሉ የዓለም ሃገራት በወርቅ ሜዳሊያ ቁጥር ብቻ ተበልጣ ሁለተኛ ላይ እንድትቀመጥ አድርጓታል፡፡ ዩጋንዳ፣ አሜሪካ እና አውስትራሊያ ደግሞ ተከታዮቹ ሃገራት ሆነዋል፡፡

የ44ኛው የዓለም ሃገር አቋራጭ ሻምፒዮና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ተሳትፎውን የጀመረው በብር ሜዳሊያ ነው፡፡ ንጋት ላይ በተጀመረው የድብልቅ ሪሌ 8 ኪሎ ሜትር ውድድር ተሳታፊ የነበሩት አዳነ ካህሳይ፣ ጌትነት ዋለ፣ ሐዊ አበራ እና ብርቄ አበራ ተካፋይ ነበሩ፡፡ በውጤቱም ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች በኬንያ ተቀድመው አዘጋጇን አውስትራሊያን በማስከተል ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ የብር ሜዳሊያውን ማጥለቅ ችለዋል፡፡

በቀጣይ በተካሄደው ከ20 ዓመት በታች የሴቶች ውድድር ኢትዮጵያ ሁለት ሜዳሊያዎችን ማስቆጠር ችላለች፡፡ በዚህ ውድድር አሸናፊ በመሆን የወርቅ ሜዳሊያውን ያጠለቀችው አትሌት ሠናይት ጌታቸው ስትሆን የገባችበት ሰዓትም 20፡53 ሆኖ ተመዝግቦላታል፡ ሌላኛዋ አትሌት መዲና ኢሳ ደግሞ ከሰባት ሰከንዶች መዘግየት በኋላ ኬንያዊያን አትሌቶችን በማስከተል ሁለተኛ ሆና መግባት ችላለች፡፡ ከውድድሩ በኋላም አሸናፊዋ አትሌት ሠናይት ‹‹ከቡድን አጋሮቼ ጋር በመሆን በጥሩ የቡድን ስሜት ዝግጅት ስናደርግ ቆይተናል። ይህንኑ በውድድሩ ላይ በመተግበራችንም አሸናፊ ልሆን ችያለሁ›› ስትል ምስጋናዋን አብረዋት ለሮጡ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ሰጥታለች፡፡ የ17 ዓመቷ ወጣት አትሌት በጃንሜዳ ኢንተርናሽናል ሃገር አቋራጭ ውድድር ሦስተኛ በመሆን ነበር ሩጫዋን የፈጸመችው፡፡




አትሌት ሠናይት ጌታቸው በግል ብቸኛውን የወርቅ ሜዳሊያ አስመዝግባለች፣

ከ20 ዓመት በታች የወንዶች ውድድርም በግል ሁለተኛው የነሐስ ሜዳሊያ ተመዝግቧል፡፡ በውድድሩ ኢትዮጵያውያኑ ወጣት አትሌቶች አስደናቂ የቡድን ሥራ በመሥራት ለኬንያ እና ኡጋንዳ አትሌቶች ፈተና መሆናቸው አልቀረም፡፡ ይሁንና ኬንያውያኑ (እስማኤል ኪፕኪሩይ እና ሬይኖልድ ቺሩዮት) አጨራረስ ላይ ባሳዩት ብቃት አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ የድል ባለቤት ሲሆኑ፤ ኢትዮጵያዊው አትሌት ቦኪ ዲሪባ የነሐስ ሜዳሊያ ሊሆን ችሏል፡፡ አሸናፊ ለመሆን ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ የቆየው ቦኪ ከአሸናፊው አትሌት በሁለት ሰከንዶች ብቻ ተበልጦ 24 ደቂቃ ከ31 ሰከንድ የሆነ ሰዓት ሊያስመዘግብ ችሏል፡፡ በቡድን ደግሞ የብር ሜዳሊያ ተገኝቷል፡፡

የምስራቅ አፍሪካውያን ውድድር ይመስል በነበረው የአዋቂ ሴቶች የ10 ኪሎ ሜትር ውድድር ከመነሻው አንስቶ ፉክክሩ በኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ዩጋንዳ፣ እና ኬንያ አትሌቶች መካከል ነበር ጠንካራ ፉክክር ሲታይ የቆየው። በዚህ ውድድር ለአሸናፊነት እጅግ ተጠባቂ የነበረችው አትሌት ለተሰንበት ግደይ ቀድሞ ከወጣው የምሥራቅ አፍሪካዊያን ቡድን መጨረሻ ሆና በእርጋታ ስትከተላቸው መቆየቷን ተከትሎ ውድድሩ በቀጥታ በሚያስተላልፉት ባለሙያዎች ጭምር በራስ ከመተማመን ስሜት የመነጨ ስለመሆኑ በአድናቆት ሲነገርላት ቆይቷል፡፡ ርቀቱ ከተጋመሰ በኋላ ግን እንደተጠበቀው ለተሰንበት ከቡድን አጋሯ ጽጌ ገብረሰላማ ጋር በመሆን ወደፊት በመውጣትና ከኬንያውያን ተቀናቃኞቿንም በማስከተል የአሸናፊነት መስመሩ ጋር ለመድረስ ጥቂት እርምጃዎች ሲቀሯት ያልተጠበቀ ሁኔታ አጋጠማት፡፡ ብርቱዋ አትሌት አሸናፊነቷን ባረጋገጠችበት ቅጽበት ቁርጭምጭሚቷ አካባቢ በደረሰባት የእግር መታጠፍ የመውደቅ አደጋ ስለደረሰባት አራተኛ ደረጃን ይዛ ማጠናቀቋ የግድ ሆኗል።

በዚህም መሠረት የአዋቂ ሴቶች 10 ኪሎ ሜትር ሩጫ አሸናፊ ኬንያዊቷ ባትሪስ ቺቤት ልትሆን ችላለች። ለነሐስ ስትጠበቅ የቆየችው ሌላኛዋ ኢትዮጵያዊት አትሌት ጽጌ ገብረሰላማ ሁለተኛ በመሆን የብር ሜዳሊያውን ስታጠልቅ፣ ኬንያዊቷ አግነስ ጄቤት ደግሞ ተከትላት ገብታለች፡፡ ልብ ሰባሪ በሆነው አሳዛኝ ገጠመኝ በመድረኩ ሦስተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ያጣችው ለተሰንበት ግደይ በሰከንዶች እድሜ በመዘግየቷ የዲፕሎማ ተሸላሚ ሆናለች፡፡

በመጨረሻ በተካሄደው የአዋቂ ወንዶች 10 ኪሎ ሜትር ውድድር ደግሞ ኡጋንዳዊው ጃኮብ ኪፕሊሞ ቀዳሚው አትሌት ሲሆን፤ በሪሁ አረጋዊ አራተኛውን የብር ሜዳሊያ ለሃገሩ ማስገኘት ችሏል፡፡ የ5ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ የዓለም ክብረወሰን (12፡49) ባለቤቱ አትሌት ርቀቱን ለማጠናቀቅ የፈጀበት ሰዓት 29 ደቂቃ ከ26 ሰከንድ ሆኗል፡፡ ይኸውም ከአሸናፊው አትሌት በዘጠኝ ደቂቃ ብቻ የዘገየ ነው፡፡ እኤአ 2019 ላይ በዴንማርክ አህሩስ በተካሄደው ሻምፒዮና የወርቅ ሜዳሊያው ባለቤት የነበረው ኡጋንዳዊው አትሌት ጆሽዋ ቺፕቴጊ ደግሞ በዚህ ውድድር ሦስተኛ በመሆን የነሐስ ሜዳሊያውን ወስዷል፡፡ በሁለቱም ጾታዎች የአዋቂ ዘርፍ የቡድን ብር ሜዳሊያም ተመዝግቧል፡፡


# የጨረታ ማስታወቂያ

## የግዥው መለያ ቁጥር አአከመባ/ግብዓት/ቡ-2/025/2015

የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን በ2015 በጀት ዓመት ከዚህ በታች በሰንጠረዥ የተገለጹትን የተለያዩ አይነት የአርማታ ብረት ግዥ በብሄራዊ ግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| ተ/ቁ | ዕቃው ዓይነት | መለኪያ | ብዛት | ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ | የጨረታ መዝጊያ ቀንና ሰዓት | የጨረታ መከፈቻ ቀንና ሰዓት | የጨረታ ማስከበሪያ በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አርማታ ብረት ባለ ø 8 ሚ.ሜ | ኪ.ግ | 44,312.5 | 60 ቀን | የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋት 4፡00 ሰዓት | የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋት 4፡30 ሰዓት | 500,000.00 (አምስት መቶ ሺህ) |
| 2 | አርማታ ብረት ባለ ø 10 ሚ.ሜ | ኪ.ግ | 208,122.5 | | | | |
| 3 | አርማታ ብረት ባለ ø 12 ሚ.ሜ | ኪ.ግ | 488,285.30 | | | | |
| 4 | አርማታ ብረት ባለ ø 14 ሚ.ሜ | ኪ.ግ | 54,437.7 | | | | |
| 5 | አርማታ ብረት ባለ ø 16 ሚ.ሜ | ኪ.ግ | 144,994.4 | | | | |
| 6 | አርማታ ብረት ባለ ø 20 ሚ.ሜ | ኪ.ግ | 231,593.3 | | | | |
| 7 | አርማታ ብረት ባለ ø 24 ሚ.ሜ | ኪ.ግ | 327,934.6 | | | | |
| 8 | አርማታ ብረት ባለ ø 30 ሚ.ሜ | ኪ.ግ | 296,591.4 | | | | |
| 9 | አርማታ ብረት ባለ ø 32 ሚ.ሜ | ኪ.ግ | 25,670.0 | | | | |

### ስለሆነም፡-

1. ተጫራቾች አግባብነት ያለው ለዘመኑ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ፣የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፤የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፊኬት፣ የግብር ከፋይ ሰርተፊኬት፤ እና በጨረታ መወዳደር የሚያስችል የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ታክስ ክሊራንስ ሰርተፍኬት ማቅረብ እንዲሁም በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ወይንም ድረ ገፅ www.PPA.gov.et መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡
2. ተጫራቾች የጨረታውን ሠነድ የማይመለስ ብር 300.00 /ሶስት መቶ ብር/ በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በስራ ሰዓት ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት እስከ 6፡30 ሰዓት እና ከሰዓት ከ7፡30 ሰዓት 11፡00 ሰዓት ከባለሥልጣኑ መ/ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 135 መውሰድ ይችላሉ፡፡
3. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ዋስትናው ከታወቀ ባንክ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ጋራንቲ ወይም በCertified Payment Order (CPO) ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከባንክ የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (Bid Bond) ለ 90 ቀናት ፀንቶ የሚቆይ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. ማንኛውም ተጫራች የመጫረቻ ሰነዱን በቴክኒካል እና በፋይናንሻል በመለያየት በኤንቨሎፕ በማሸግና በኤንቨሎፖቹም ላይ ቴክኒካል ኦሪጅናልና ኮፒ እንዲሁም ፋይናንሻል ኦሪጅናልና ኮፒ ብሎ በመፃፍ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ከላይ በሰንጠረዡ የጨረታ መዝጊያ ተብሎ እስከ ተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በባለሥልጣኑ መ/ቤት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 109 በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በሚገኙበት ከላይ በሰንጠረዡ የጨረታ መክፈቻ ተብሎ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት ይከፈታል፡፡
6. ናሙና ማቅረቢያ ጊዜ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ ጨረታው ከሚከፈትበት አንድ ቀን ቀድሞ እስከ ቀኑ 11፡00 ሰዓት ድረስ መካኒሳ ጀርመን አደባባይ አካባቢ በሚገኘው የባለስልጣን መ/ቤቱ ዕቃ ግ/ቤት ማቅረብ አለባቸው፡፡
7. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

አድራሻ፡- ሳርቤት ፑክሸን አደባባይ

ስልክ ቁጥር +251 113 72 28 15 /25

# የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን